Food and Agriculture
Organization of the
United Nations

የመሬት ይዞታ አስተዳደር
ሙያዊ መምሪያ ቁጥር
7

# የመሬት ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከተ የኢንቬስተሮች ሙያዊ መምሪያ

ይህ መመሪያ የመሬት ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከተ የኢንቬስተሮች ሙያዊ መምሪያ በሚል ተዘጋጅቶ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው፡፡



የመሬት ይዞታ አስተዳደር ሙያዊ መምሪያ ቁጥር 7

# የመሬ ትይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከተ የኢንቬስተሮች ሙያዊ መምሪያ


ፀሐፊ፡-

ዳርየል ቭሁገን

ፅሁፍ አቅራቢዎች፡-

በርንድ ሻንዘንባእቸር

አንድሩ ሂልቶን, ዴቪድ ፓልመር, ፖል ሙንሮ-ፋኦር እና ፍራንሲስካ ሮማኖ

*የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የግብርና ድርጅት (ምግድ)*



የተባበሩት መንግሥታት የምግብና የግብርና ድርጅት
አዲስ አበባ 2019 ዓ.ም

‘In collaboration with FAO the TG7 have been translated from English to Amharic by the EU-BMZ co-financed GIZ- Support to Responsible Agricultural Investment (S2RAI) Project’.

The information and views set out in this publication are those of the author(s) and do not necessarily reflect the official opinion of the European Union and the BMZ.

በዓለም የምግብ ድርጅት ፈቃድ መሰረት ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በአውሮፓ ህብረት እና የጀርመን የልማት ተራድኦ ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ፤ በግብርና ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፕሮጀክት አማካይነት የተተረጎመ፤ ሲሆን በመመሪያው ላይ የተገለጹ ሀሳቦች የአውሮፓ ህብረትን ወይም የጀርመን ልማት ተራድኦ ድርጅት አቋም አያመለክቱም፡፡

ይህ ህትመት የታለመው በአገር አቀፍ የምግብ ዋስትና ማእቀፍ ውስጥ የመሬት፣ የአሳ ሀብት እና የደን ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ መመሪያዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለመደገፍ ነው፡፡ በመሆኑም ህትመቱ በአለም የምግብ ዋስትና ኮሚቴ ድጋፍ የተሰጣቸውን መመሪያዎችንም ሆነ መንግስታትም በትግበራ ላይ ያላቸውን ሚና ለመቃረን ታስቦ የተዘጋጀ አይደለም፡፡

ይህ ህትመት የተዘጋጀው በተባበሩት መንግስታት የምግብና የግብርና ድርጅት (ምግድ) እና በጣሊያን መንግስትና በጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር እና የዓለም አቀፍ ትብብር በተደረገ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በህትመቱ ውስጥ የቀረቡት ሀሳቦች የፀሐፊዎቹን እንጂ የምግድን ይፋዊ ፓሊሲዎች ወይም አመለካከት አይወክሉም፡፡

የህትመቱ ንድፍ እና የፅሁፎቹ ይዘት በምንም አይነት መልኩ የየትኛውንም አገር የሕግ ወይም የእድገት ደርጃ፣ የግዛት፣ የከተማ፣ አካባቢ እና ባለስልጣናትን ወይም ድንበሮችን ወይም ወሰኖችን የተመለከተ የምግድን አቋም አይገልፁም፡፡ በዚህ ህትመት ላይ አንዳንድ ኩባንያዎች ወይም  የፋብሪካ ምርቶች የአእምሯዊ ንብረት መብት ይሰጣቸውም አይሰጣቸው መጠቀሳቸው በምንም መልኩ በምግድ ከሌሎች ተመሳሳይ ኩባንያዎች ወይም ምርቶች የተለየ ተቀባይነት ወይም ይሁንታ ማግኘታቸውን አያመለክትም፡፡

ISBN 978-92-5-131436-4

© FAO, 2019

በዚህ ህትመት ውስጥ የቀረቡትን መረጃዎች መጠቀምን፣ በድጋሚ ማሳተምን ወይም ማሰራጨትን ምግድ ያበረታታል፡፡ እስካልተጠቀሰ ድረስ፣ መረጃዎቹን መገልበጥ ወይም ለግል ጥናት፣ ለምርምር ለማስተማሪያ አላማዎች ወይ ምግድ ነክ ላልሆኑ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች፤ ለምግድ ተገቢ እውቅና እስከተሰጠው፣ የኮፒ-ራይት ባለቤትነቱ እስከታወቀና ምግድ ለተወሰኑ ተጠቃሚዎች፣ አመለካከቶች፣ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ምርጫ አለው የሚል እንድምታ እስካልተሰጠ ድረስ መጠቀም ይቻላል፡፡ ህትመቱን ለመተርጎም፣ ለማሻሻል እና ለድጋሚ ሽያጭ ወይም ለሌሎች የንግድ ጥቅሞች ለማዋል የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሙሉ በ www.fao.org/contact-us/licence-request ወይም copyright@fao.org  በኩል መቅረብ ይችላሉ፡፡

የምግድ ሕትመቶችን በምግድ የመረጃ መረብ ላይ ማየት ይቻላል (www.fao.org/Publications) እና Publications-sales@ fao.org መግዛት ይቻላል፡፡

# ምስጋና

ይህ ሙያዊ መምሪያ፣ ማለትም ምክንያታዊ የመሬት አስተደደር፡- ለኢንቬስተሮች ሙያዊ መምሪያ፣ የተዘጋጀው በ Darryl Vhugen እና በ Bernd Schanzen Baecher በተደረገ አስትዋፅኦ እና፣ እንደዚሁም በ Andrew Hilton፣ David Palmer፣ Paul Munro-Faure እና Francesca Romano አመራር ስር ነው፡፡

ይህ ሙያዊ መምሪያ በተለያዩ የንግድ ዘርፍ እና ህዝባዊ ድርጅቶች ተወካዩች የተገኙ በርካታና ጠቃሚ ግብዓቶች ይዘት ያንፀበርቀል፡፡ ግብዓቶቹ በፅሁፍ የተሰጡት በሁለት የምክክር ክፍለ ግዜያት ነው፡- አንደኛው፣ የግል ዘርፍ ኢንቬስተሮች ተካፋይ የሆኑበት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ፣ የተለያዩ ህዝባዊ ድርጅቶች የተሳተፉበት ነው፡፡ ፀሀፊዎቹ ስለተሰጠው ግብዓት ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ ለየት ያለ ምስጋና ደግሞ በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ ምክረ ሀሳብ ለሰጡን የምግድ የስራ ባልደረቦች፡- Margret Vidar፣ Martha Osorio፣ Pascal Liu፣ Jesper Karlsson፣ Yannick Fiedler፣ Rodrigon Castaneda፣ Annamaria Pastore፣ Alessandra Basilico እና Elizabeth Beall ይድረሳቸው እንላለን፡፡

የህትመቱ የአርትዖት ስራ የተከናወነው በ Shannon Russell ሲሆን አቀራረቡ ደግሞ በ Luca Feliziani ነው፡፡

የተባበሩት መንግስታት የምግብ እና ግብርና ድርጅት (ምግድ) የኢጣሊያን መንግስት እና የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የአለም ዓቀፍ ትብብር ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ዝግጅቱ ድረስ ላደረጉት የገንዘብ ድጋፍ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

# መቅድም

በግብርና ስራ ላይ የሚውል ኢንቨስትመንት በምግብ ራስን አለመቻልንና ድህነትን ለመቀነስ  እጅጉን አስፈላጊ ነው፡፡ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በታዳጊ አገሮች ውስጥ የእርሻ ቦታ ተፈላጊነት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል፡፡ በዚህ አኳያ መሬት አጉዋጊ መስህብነት ያለው ቋሚ ንብረት ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ በማህበራዊ ዘርፍ ረገድ በመሬት ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ቅይጥ ውጤቶችን አምጥተዋል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ኢንቨስትመንቶች የአንዱን አካባቢ ማህበረሰቦች ተጠቃሚ የማድረግ አቅም አላቸው፡፡ ይህም አነስተኛ አቅም ያላቸው ገበሬዎች የካፒታል፣ የቴክኖሎጂ፣ የእውቀትና የግብይት ቦታዎች አቅራቦት እንዲኖራቸው በማድረግ ነው፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን የላቀ ኢኮኖሚያዊ እምርታ እና የግብርና ምርታማነትን የመሳሰሉ ጠቀሜታዎችን ማግኘት ያስችላሉ፡፡ ቢሆንም እነዚህ ኘሮጅክቶች ብዙ ግዜ የአካባቢውን ነዋሪዎች መብቶቻቸውን እንዲያጡና መሬታቸውንና በመሰል የተፈጥሮ ሃብቶችም መጠቀም እንዳይችሉ በማድረግ ለተጐጂነት ይዳርጉዋቸዋል፡፡ እንደዚሁም በምግብ ዋስትናና በገጠር ነዋሪዎች እኗኗር ላይ ተፅእኖዎች አሳድረዋባቸዋል፡፡

ባመዛኙ በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ በግብርና ስራ ላይ እንቬስትመንት የሚካሄደው ደካማ የመሬት ባለቤትነት አስተዳደር እና ድህነት በከፍተኛ ደረጃ በተንሰራፋባቸው አካባቢዎች ነው፡፡ በአገር አቀፍ የምግብ ዋስትና ማእቀፍ ውስጥ የመሬት፣ የአሳ ሀብት እና የደን ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ መመሪያዎች (መመሪያዎቹ) በተባበሩት መንግሥታት የዓለም ምግብ ዋስትና ኮሚቴ በግንቦት 2004 ዓ.ም ይሁንታ አግኝተዋል፤ መመሪያዎቹ የተፃፉትም እነዚህንና ሌሎች አገሮችም ጭምር የመሬት ባለቤትነት አስተዳደራቸውን ለማሻሻል እንዲረዱ ታስቦ ነው፡፡ የመመሪያዎቹ አብይ አላማ የምግብ ዋስትና እጦትን እና ድህነትን መቀነስ ነው፡፡

መመሪያዎቹ በዋንኛነት ትኩርት ያደረጉት መንግስታት ላይ ቢሆንም ለግሉ ዘርፍም ሊተገበሩ የሚችሉ ጠቃሚ ቁም ነገሮችን በተጨማሪነት አካተዋል፡፡ ኢንቬስተሮች ኘሮጀክቶቻቸው ህጋዊ የመሬት ባለቤትነትንና ሰብዓዊ መብቶችን ለመተግበር እንዲችሉ ድጋፍ መስጠት ላይም ልዩ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ መመሪያዎቹ በከፍተኛ ደረጃ በመሬት፣ በደኖች እና በአሳ ሀብቶች ስራ ላይ ለሚውል ኢንቬስትመንት በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ ምርጥ የስራ ተሞክሮዎች ማሳያ ተደርገው ተወስደዋል፡፡

ከመመሪያዎቹ ጋር በሚጣጣም መልኩ እንቬስትመንቶቻቸውን የሚተገብሩ ክፍሎችን ሊያገጥም የሚችል አደጋን በመቀነስ ምክንያታዊና ተጐጂነትን ያገናዘበ ውጤት የማሳደግ እድል ይኖራቸዋል፡፡ እንደነዚህ ያሉ እንቬስትመንቶች ስኬታማ ሊሆኑ የሚችሉት እያንዳንዱ ኢንቬስተሩ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ እና መንግስት ተጠቃሚ መሆን ከቻሉ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሙያዊ መምሪያ የሚሞክረው ኢንቬስተሮች የራሳቸውን ሚና በአግባቡ በመጫዎት ተፈላጊውን ውጤት ማግኘት በሚያስችሉዋቸው መንገዶች መመሪያዎቹን በተግባር መዋል እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡

# ምህፃረ ቃላት

| | |
|---|---|
| አ ን ኢ ፈ፡- | የአፍሪካ ንግድና ኢንቬስትመንት ፈንድ |
| ሴ ሚ አ ማ ስ፡- | በሴቶች ላይ የሚደርሱ አድሏዊነቶችን የማስወገድ ስምምነት |
| ተ መ ዓ ም ዋ ኮ፡- | የተባበሩት መንግስታት የዓለም የምግብ ዋስትና ኮሚቴ |
| ኩማ ሃ፡- | የኩባንያ ማሕበራዊ ኃላፊነት |
| ሲፖመዓስ | የሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ስምምነት |
| ዓ ፋ ድ ፡- | የዓለም የፋይናንስ ድርጅት |
| ተ መ ም ግ ድ | የተባበሩት መንግስታት የምግብና የግብርና ድርጅት |
| ነ ቅ ዕ ፈ፡- | ነፃ፣ ቅድመ እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ |
| አ ስ ድ፡- | አለም አቀፍ የሥራ ድርጅት |
| መ ያ ድ ፡- | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች |
| ተ መ ሰ መ ከ መ ጽ ቤ፡- | የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ መልዕክተኛ ጽህፈት ቤት |
| ግ እ | የግል እሴት |
| ባ ማ ማ አ ስ ፡- | የባዮማቴሪያል የማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዐት |
| ዘ ዘ ዘ  አ ስ፡- | የዘንባባ ዘይት የዘልቂታዊነት  አሰጣጥ ስርዓት |
| አ ማ ተ ግ፡- | የአካባቢያዊና የማህበረሰባዊ ተፅዕኖ ግምገማ |
| ተ መ ን ል ጉ፡- | የተባበሩት መንግስታት ንግድና ልማት ጉባኤ |

# ማውጫ


ምስጋና . . . . . . . . . . . . . . III
መቅድም . . . . . . . . . . . . . . IV
ምህፃረ ቃላት . . . . . . . . . . . . . V
ጭምቅ ሃሳብ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . VIII

**1.** መግቢያ **1**

ሀ. መነሻ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
ለ. መሰረታዊ ምክንያት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4
ሐ. አበይት ተደራሲያን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .7
መ. የመንግስት ሚና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8
ሠ. ስለመጠን እጅግ በጥቂቱ . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

**2.** መሬት ይዞታ መብቶች **11**

ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . . 13
ለ. አደጋው ምንድን ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 14
ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . . 16
1. ለመብቶች እውቅና መስጠት . . . . . . . . . . . . . . . 16
2. በመሬት መብቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን መገምገም . . . . . . . . 17
3. ጉዳትን ለማስወገድ ፕሮጀክቱን ማሻሻል . . . . . . . . . . . . . 20

**3.** ምክክር፣ተሳትፎና ድርድር **27**

ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
ለ. አደጋው ምንድነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 29
ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . . 31
1. ምክክር መደረግ ያለበት ጊዜ . . . . . . . . . . . . . . . 31
2. የምክክር ተሳታፊ አካላት . . . . . . . . . . . . . . . . 31
3. ምክክር የመከወኛ ዘዴ . . . . . . . . . . . . . . . . 32
4. ነፃ፣ቅድመ እና በዕውቅት ላይ የተመሠረተ ፈቃድ (ነቅዕፈ) . . . . . . . . . . 34

**4.** ቅሬታዎች እና ክርክር አፈታት **37**

ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . . 39
ለ. አደጋው ምንድነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 39
ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . . 40

**5.** ግልፀኝነትና ሙስና **43**

ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . . 45
ለ. አደጋው ምንድ ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 46
ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . . 47
1. ሙስና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 47
2. ግልፀኝነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 48

**6.** የምግብ ዋስትና፣ ሰብዓዊ ሙብቶች ፣አካባቢና ዘለቄታዊነት **51**

ሀ. የምግብ ዋስትና . . . . . . . . . . . . . . . . . . 53
1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . 53
2. አደጋው ምንድ ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 53
3. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና ማቃለል ይቻላል? . . . . . . . . . . . 54
ለ. ሰብዓዊሙብቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . 55
1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . 55
2. አደጋው ምንድ ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 56
3. ጉዳትን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . 58
ሐ. አካባቢና ዘለቄታዊነት . . . . . . . . . . . . . . . . 59
1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . 59
2. አደጋው ምንድ ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 59
3. ጉዳትን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . 60

**7.** አንገብጋቢ የትግበራ ፈተናዎች **63**

ሀ. የአቅም ግንባታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 65
1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . 65
2. አደጋው ምንድ ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 65
3. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . 66
ለ. ቁጥጥር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 68
1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ? . . . . . . . . . . . . . . . . 68
2. አደጋው ምንድ ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . 68
3. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል? . . . . . . . . . . . 69

የቁልፍ መልዕክቶች ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . . . . 71
የግርጌ ማስታወሻዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . 73

# ጭምቀ ኃሳብ

በአገር አቀፍ የምግብ ዋስትና ማእቀፍ ውስጥ የመሬት፣ የአሳ ሀብት እና የደን ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከቱ በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የተነደፍት መመሪያዎች ከዚህ በኋላ “መመሪዎቹ” የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህ መመሪዎች በተባበሩት መንግሥታት (በተባበሩት መንግስታት የዓለም የምግብ ዋስትና ኮሚቴ) ተቀባይነት ያገኙ ሲሆኑ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት፡- መንግስት እና የግሉን ዘርፍ ተዋናዮችን እና የአካባቢው ማህበረተሰቦች ከላይ በተጠቀሰው ማዕቀፍ ውስጥ በመንቀሳቀስ የመሬት፣ የዓሳ ሐብትና የደኖች አጠቃቀማቸውን ማሻሻልና ብሎም በመሬት፣ በዓሳ ሀብትና በደኖች ማህበራዊ ሀላፊነት የተሞላበትና ዘላቂነት ያላቸው ኢንቨስትመንቶችን ስኬታማ ማድረግ እንዲችሉ ነው (ምግድ 2004 ዓ.ም ሀ)፡ ፡ መመሪያዎቹ በቀዳሚነት ለመንግስታት ግልጋሎት እና ከውስጣቸው ደሞ የተወሰኑት በግሉ ዘርፍ በተናጠል አስፈላጊ ናቸው ተብለው የተካተቱ ናቸው፡፡

“ *የንግድ ድርጅቶችን ጨምሮ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋንያን ሰብአዊ መብቶችን እና ሕጋዊ ይዞታዎችን የማክበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በተለይ የንግድ ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችና የሌሎችን ሕጋዊ የይዞታ መብቶችን ላለመጣስ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ተገቢ የሆነ በሰዎች እና በሰው ልጆች መብት ላይ ሊጋረጥ የሚችል ያልተጠበቀ አደጋን መከላከል እና መተንበይ የሚያስችል ሥርዓትን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ (አንቀጽ 3.2)*

ይህ ሙያዊ መምሪያ ከመመሪያዎቹ በተጉዋዳኝነት የሚያተኩረው የመሬት ባለቤትነት መብቶችን በሚመለከቱ ጉዳዩች ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከመመሪያዎቹ በተለየ ሁኔታ የመምሪያው ትኩረት በእርሻ መሬት የተወሰነ ነው፡፡ ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ እንደ ካፒታልን የማሳደግ፣ የንግድ ስራ እቅዶችን ዝግጅት ወይም ጥሩ አካባቢያዊ አስተዳደር ማስፈን ያሉ ሌሎች በርካታና የተለያዩ ጉዳዩችን ግን አይዳስስም፡፡ እነዚህ ሁነቶች ከመመሪያዎቹ ዳራ ውጪ ናቸው፡፡እዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ምክረ ኃሣቦችን አበክረው የሚከተሉ ኢንቨስትመንቶች ከመሬት ባለቤትነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የመብት ጥያቄቻችና ክርክሮች ሊያጋጥሙ የመቻላቸውን እድል የመነመነ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ዳሩ ግን ይህንን መምሪያ መከተል በራሱ ማንኛቸውንም ጉዳዩች እና ችግሮች ለማስወገድ ዋስትና ሊሆን ይችላል ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም መምሪያዎቹ ዋስትና የሚሰጥ የአሰራር አካል ተደርገው መወሰድ የለባቸውም፡፡

አንድ ከፍተኛ የንግድ ተቋም አመራር እንደታዘበው ከሆነ ግብርናን መሰረት ያደረጉ ኢንቬስትመንቶች “የነዋሪዎችን ፍላጐቶችን እና ከባቢያዊ ገፀ-ምድሮችን የሚመለከቱ ጉዳዩችን ወደ ጐን የሚተው ኢንቨስተመንቶች ስነምግባራዊ ተቀባይነት የማይኖራቸውና ከአጭር ግዜ አትራፊነት ባሻገር መመልከት የማይችሉ ናቸው (ቦውማን 2005 ዓ.ም)፡፡ በአንፃሩ እንደ እነዚህ አይነቶቹ ኢንቬስትመንቶች ስኬታማ የመሆን ከፍተኛ እድል ሊኖራቸው የሚችለው እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል፡- ኢንቬስተሩ፣ የአካባቢው ማህበረተሰብና መንግስት ጭምር ተጠቃሚ መሆን ከቻሉ ነው፡፡ ለዚህም መመሪያዎቹ ሁሉም አሸናፊ መሆን የሚያስችላቸውን መድረክ ይፈጥሩላቸዋል፡፡ይህ ሙያዊ መምሪያ የታሰበው ኢንቬስተሮች ተፈላጊውን ውጤት ለማምጣት የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ለማገዝ ነው፡፡

# የአደጋ ተጋላጭነት መንስኤዎች

ለአንቬስተሮች ተገቢ ኢንቨስትመንት በመሬት ላይ መዋል የሚጀምረው በቅድመ የአደጋ ተጋላጭነት ዳሰሳ ነው፡፡ እንደ ስሞለር እና ሌሎች (2006 ዓ.ም) አባባል ይህ ክንውን ለከፍተኛ አደጋ ተጋላጭነት መስኤዎች ግምገማ ማካሄድን ብሎም ይበልጥ በተገቢ ትጋት ሁሉን -አቀፍ የሆነ ሂደትን ማካሄድን ይጨምራል፡፡ የቅድመ

ዳሰሳውና የተገቢ ትንተና ውጤቶች በበቂ ሁኔታ አወንታዊ መሆን ከቻሉ ሂደቱ በምክክር፣ በድርድር፣ በስምምነት እና አላስፈለጊ ነገሮችን በማጥራት እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በእርግጥ የተግባራዊነትና የማጥራት ሂደቶች አስፈላጊነታቸው አናሳ ባይሆንም ይህ መምሪያ በዋነኝነት አፅዕኖት የሚሰጠው በቅድመ ዳሰሳ፣ ተገቢ ትጋት፣ ምክክር፣ ድርድር እና ስምምነትን የተመለከቱ ሂደቶች ላይ ነው፡፡ ለዚህም መንሰኤው ከመሬት ተጠቃሚነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ትላልቅ ጉዳዩችን የሚያስነሱ በመሆናቸው ነው፡፡

የቅድመ ዳሰሳ በሚደረግብት ወቅት የከፍተኛ ተጎጂነት ክስተቶች መኖር ኢንቨስተሩ ኃላፊነት የሚሰማው ከሆነ በኢንቬስትመነቱ እንዳይገፋበት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ እነዚህ መንስኤዎች በሳጥን አንድ ውስጥ ተዘርዝረዋል፡፡

ሳጥን 1፡-
የአደጋ ከፍተኛ መንስኤዎች

- መሬትን በተመለከተ ሊፈቱ የማይችሉ በርካታ የቆዩ ወይም የቅርብ ግዜ የመብት ጥያቄዎች ወይም የይገባኛል ክርክሮች አሉ፡፡
- መንግስት መሬቱን ቀደም ባለ ጊዜ በማሰለቀቁ ወይም ኘሮጀክቱ መሬቱን ለልማት ስራ ለማዋል መሬቱን እንዲለቀቅ በመጠየቁ ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል፡፡
- የኘሮጀክቱ አቀራረፅ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች የመሬት ይዞታ መብቶች በከፍተኛ መጠን እንዲተላለፉ በመፈለጉ ምክንያት፣ ብዙ ሰዎች ያለፍላጎታቸው ወይም በፍቃዳቸውም ሊሆን ይችላል ሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡
- ኘሮጀክቱ ምናልባትም ሊካሄድ የታሰበበት አካባቢ ከፍተኛ የሙስና ችግር ያለበትና ሊካሄድ ከታሰበው ኘሮጀክት ጋር በተያያዘ በሚገባ ሊቃለሉ የማይችሉ የሙስና ተግባራት ተስተውለዋል፡፡
- ኘሮጀክቱ በሚካሄዱበት አካባቢ ተከታታይ የሆነ ግጭት አለ፡፡
- ደካማ የመሬት አስተዳደር ባለባቸው አካባቢዎች ኦፕሬተሩ ወይም በቀጥታ የሚሣተፈው ኢንቬስተር የሚከተሉትን ነገሮች ያላካሄደና ወደፊትም የማያካሂድ ነው፡-
    - አሣታፊ የሆነ የባለድርሻ አካላት ምዝገባ፤
    - ሁሉን አቀፍ የአካባቢያዊና የማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (አማተግ) በመሬት ይዞታ መብቶች፣ በምግብ ዋስትናና በሰብዓዊ መብቶች ላይ ጭምር፤ ወይም
    - አካታችየሆነ የማህበረሰብ የምክክር ሂደት፤
- የአማተግ በተካሄደበት ቦታ፣ ግምገማው የሚከተሉትን ያሣያል፡-
    - በምግብ ዋስትና ላይ አጥጋቢ በሆነ መጠን ሊቃለሉ የማይችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን፤
    - ሊወገዱ የማይችሉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፤
- የማህበረሰቡ ነባር ህዝቦች ነፃ፣ ቅድመ፣ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃዳቸውን (ነቅእፈ) አልሰጡም፡፡
- ኘሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ በኘሮጀክቱ ሊወድሙ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ የብዝሃ ህይወት እና ማህበረሰባዊ እሴቶች የሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡

አስቀድሞ የሚካሄደው ቅኝት በተጨማሪነት ጥቂት ወይም በርካታ አሉታዊ አካባቢያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖን ማስከተል የሚችሉ መንስኤዎችን እና/ወይም መቃለል ወይም መቀልበስ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን ነቅሶ ማውጣት ወይም ማሳየት ይችላል፡፡[1] በሳጥን ሁለት የተዘረዘሩት ለተጎጂነት አጋላጭነት አናሳ መንስኤዎች የሚኖሩት ኘሮጀክትን ለማካሄድ የሚያሰላስል ኢንቬስተር በትግበራ ወቅት ብልሃት በተሞላበትና በጥንቃቄ ዳግም በመገምገም መንቀሳቀስ እና አደጋዎች ሊቀነሱባቸው የሚችሉባቸውን መንገዶች በመፈለግ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ እንደዛ ማድረግ የማይቻል ከሆነ ኢንቬስተሩ በኢንቬስትመንቱ መግፋት አይኖርበትም፡፡

[1] የኢኳተረ መርህ (2013) ሰጋቶችን በሶስት ደረጃዎች ይከፍላል፤ ከፈተኛ የሰጋት ደረጃ ሀ ሲሆን እስከ ሐ ይደርሳል፤ ይህ የሰጋት ትንተና ለባለሀብቶች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፤ መርሁን ይመለከቱ፤ መመሪያወ የደንና የዓሣ በግብርና ኢንቨሰትመንትንም ይመለከታል፤

**ሳጥን 2፡- መካከለኛ የጉዳት መንስኤዎች**

- ኘሮጀክቱ የሚካሄድበት ቦታ በጣም ሰፊና በኘሮጀክቱ መላ የቆይታ ጊዜ ለምርት ስራ ከሚያስፈልገው በላይ በመሆኑ ትርፍ ለማጋበስ የታሰበ ነው የሚል ስጋት ያሣድራል፡፡
- ኘሮጀክቱ የሚገኘው በፊት ግጭት የነበረበት አካባቢ ነው፡፡
- የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በአካባቢው እንደነበሩ ተዘግቧል፡፡
- ነባር ህዝቦች ኘሮጀክቱ በሚገኝበት ቦታ ወይም አቅራቢ ይኖራሉ፡፡
- ኘሮጀክቱ የሚካሄደው የመሬት ይዞታ መብቶች ምናልባትም ተመዝግበው ያልተያዙበት እና/ወይም በልማዳዊ ህግ የሚስተናገዱበት እና ኦኘሬተሩ ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች ያሏቸውን ባለይዞታዎች ለመለየት አሣታፊ የመለያ ስራ ማካሄድ የሚጠበቅበት አካባቢ ነው፡፡
- ኢንቬስተሩ ያነጣጠረበት በጋራ የተያዘ መሬት ማንም የማይጠቀምበት ወይም የማይኖርበት ነው ተብሎ በስህተት የተመደበ ነው፡፡
- የአካባቢ ማህበረሰብ በኘሮጀክት እቅድ ምዕራፍ ላይ ተሣታፊ አልነበረም፡፡
- ተጐጂ ወገኖች ስኬታማ፣ ባህላዊ አግባብነት ባለው፣ ፆታዎች አቀፍና ግልፀኝነት ባለው የምክክር ሂደት ገና ተሣታፊ አልሆኑም፡፡
- እራሳቸውን ወክለው መገኘት የማይችሉ የአካባቢው ማህበረሰቦች ብቃት ባላቸው አማካሪዎች ወይም አፈ-ቀላጤዎች መወከል አልቻሉም፡፡
- ሊካሄድ የታሰበው ኘሮጀክት የአካባቢያዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (አማተግ)፣ ፆታ-ተኮር የሆነ በመሬት ይዞታ፣ በምግብ ዋስትና በሰብአዊ መብቶች ላይ ሊኖሩ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ግምገማ ገና አልተጠናቀቀም፡፡
- ኘሮጀክቱ ካልተከለሰ፣ የአመተግ ኘሮጀክቱ በመሬት መብቶች፣ በምግብ ዋስትናና በሰብአዊ መብቶች ወይም በአካባቢ ላይ ከበድ ያሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ሊያሣይ ይችላል፡፡
- መደበኛ እና ልማዳዊ የመሬት ይዞታ መብቶች በምን አግባብ እንደሚተላለፉ በተመለከተ የተሟላ በፅሁፍ የተያዘ ስምምነት ላይ ገና አልተደረሰም፡፡
- ኘሮጀክቱ የሚኖረው ግንኙነት የፓለቲካ ተሣትፎ ካለው ግለሰብ (ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የፖለቲካ ስልጣን ያለው፣ ወይም ለጉቦ ወይም ለሙስና በጣም ተጋላጭ ነው ተብሎ የሚገመት ዘመድ) ጋር ነው፡፡

# 1

# መግቢያ

# 1. መግቢያ

## ሀ. መነሻ

በግብርና ስራ ላይ የሚውሉ ኢንቬስትመንቶች በታዳጊ ሀገሮች ገጠርማ አካባቢዎች ድህነትን ለመቀነስ ከሚያስችሉ መንገዶች ውስጥ እጅግ በጣም ውጤታማ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በዓለም ውስጥ ከሚገኙት ምንዱባኖች ብዙሀኑ የሚኖሩት በነዚያ አካባቢዎች ሲሆን ኑሮዋቸውም የተመሰረተው በግብርና ስራ ላይ ነው፡፡ ድህነትን እና በምግብ ራስ አለመቻልን ለመቀነስ መጠነ ሰፊ የግብርና ምርት እምርታ ማድረግ የግድ ይላል፤ እንደዚሁም የምግብ ፍላጎት በፍጥነት በማደግ ላይ በሚገኙ የከተማ አካባቢዎች በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በምግድ (2006 ዓ.ም ሀ) ዘገባ መሰረት ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ የእርሻ ቦታ የማግኘት ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እያዳገ እንዲሄድ ካደረጉት መንስኤዎች አንደኛው ይኸው እውነታ ነው፡፡

በግብርና ስራ ላይ የሚውሉ ኢንቬስትመንቶች አነስተኛ አቅም ያላቸው ገበሬዎች ለካፒታል፣ ለቴክኖሎጂ፣ ለእውቀትና ለገቢያዎች ከፍተኛ ተደራሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ በእንደነዚያ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ተጠቀሚ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ተጠቀሚ ሀገሮች እንደ ከፍተኛ ገቢዎችን፣ ኢኮኖሚያዊ እድገትን፣ የስራ ፈጠራን፣ የግብርና ምርት አመራረረትን እና ከውጭ ንግድ ገቢዎችን ማግኘት የመሳሰሉ ግዙፍ /macro/ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎችን ማግኘት ይችላሉ፡፡ በአንፃሩም የመሬት መብቶች እና አስተዳደር ደካማ በሆኑባቸው አገሮች በእርሻ ምርት ላይ የሚደረጉ ኢንቬስትመቶች፣ አልፎ አልፎ ለገጠር መሬት ባለቤቶች መብቶች መገፈፍና እንዲያውም በራሳቸው መሬትና በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች መጠቀም እንዳይችሉ አድርገዋቸዋል፡፡

መሬት ዋጋ ካላቸው የእሴቶች ምድብ ይለያል፡፡ በዓለም ውስጥ የሚገኘው መሬት በዓመዛኙ ከኑሮ መሠረትነት፣ በባህል፣ ከማህበራዊ አወቃቀሮች እና ልማዶች ብሎም ከምግብ ውህና መጠለያ አቅራቦት መኖር ጋር በፅኑ የተቆራኘ ነው፡፡ መሬት የህልውናቸው መሰረት ለሆናቸው ሰዎች አልፎ አልፎ ትልቅ ባህላዊ ትርጉም አለው፡፡ ኃላፊነት የተላበሱ ኢንቬስተሮች በነሱ ኢንቬስትመንት መንስኤነት ጉዳት ለሚደርስባቸው ሰዎች መሬት የቱን ያህል አሰፈላጊ ነገር እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን የተለያዩ ቅንብር ያላቸው የገጠር ማህበረሰብ ክፍሎች በዚሁ ሳብያ በተለያዩ መንግዶች ተጎጂ ሊሆኑ የመቻላቸውን እውነታ ኢንቬስተሮች መዘንጋት የለባቸውም፡፡

በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ በአገር አቀፍ የምግብ ዋስትና ማእቀፍ ውስጥ የመሬት፣ የአሳ ሀብት እና የደን ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከቱ መመሪያዎች (ከዚህ በኋላ 'መመሪያዎች' የሚባሉቱ) የተነደፉትና በግንቦት 2004 ዓ.ም በአንድ ድምፅ የፀደቁት የተባባሩት መንግስታት (ተመ) አካል በሆነውና በዓለም ምግብ ዋስት ኮሚቴ (ዓምዋኮ)ነው (ምግድ 2004ለ ዓ.ም)፡፡ የመመሪያዎቹ ዋነኛው አላማ የሚከተለው ነው፡፡

> የመሬት፣ የአሳ እና የደን ይዞታ አስተዳደርን ማሻሻል ነው። ምንም እንኳን ሁሉንም የማህበረሰቡን ክፍሎች ለመጥቀም የታቀዱ ቢሆኑም የተለየ ትኩረት የሚያደርግባቸው ወገኖች ግን በተለይ በማህበረሰቡ የተረሱ እና የችግሮች ሁሉ ገፈት ቀማሽ የሆኑት ናቸው፡፡ ይህንን ለማሳካት የምግብ ዋስትናንና ደረጃ በደረጃ በቂ ምግብ የማግኘት መብትን፣ የድህነት ቅነሳን፣ ዘላቂ መተዳደሪያን፣ ማህበራዊ መረጋጋትን፣ የመጠለያ ችግር መቅረፍን፣ የገጠር ልማትን፣ የአካባቢ ጥበቃን እንዲሁም ዘላቂ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ ይውላሉ (አንቀፅ 1.1) ፡፡ ”

መመሪያዎቹ በዋነኛነት መንግስታት እንዲጠቀሙባቸው የታሰቡ ቢሆንም የተወሰኑትን የመመሪያዎቹ ክፍል እንደ ኢንቬስተሮች እና የንግድ ድረጅቶች ያሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋንያን ጭምር ይገለገሉባቸዋል የሚል እሳቤ አለ (አንቀጽ 3.2)፡፡ መመሪያዎቹ በመሬት፣ በደኖችና በዓሣ ሀብት ላይ ለማደረግ ኢንቨስትመንት እንደ የምርጥ ስራ ተሞክሮዎች ተምሣሌትነት አለም አቀፍ እውቅና የተሰጣቸው ናቸው፡፡ (ይህ መምሪያ የሚዳስሰው በግብርና ላይ የሚደረጉ ኢንቬስትመንቶችን ብቻ ነው)[2]፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ መምሪያው መመሪያዎቹን ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስትመንት ሟሟላት የሚገባቸው አነስተኛ መስፈርቶች አድርጐ ይመለከታቸዋል፡፡ በመሆኑም መምሪያው ከመመሪያዎቹ ባሻገር ያሉ የተነጎጂነትን መጠን ለመቀነስና የካባቢውን ማህበረሰቦች መብቶች ማስከበርን የተመለከቱ በርካታ ምክረ ሃሣቦች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ እዚህ ላይ መጤን የሚገባው ነገር ቢኖር ይህ መምሪያ በየትኛውም አካባቢ የሚሰሩ ኢንቬስትመንቶች በመሬት አጠቃቀም ዙሪያ ለሚነሱ ችግሮች በሙሉ ምላሽ ይሰጣል የሚል ብዥታ አለመኖሩን ነው፡፡ በአንፃሩ ግን መምሪያው የሚያደርገው ነገር ቢኖር መመሪያዎቹ ምን እንደሚሉ ማብራራት እና እንዴት የንግድ ድርጅቶች ከመሬት ባለቤትነት ጋር የሚገናኙ መሰረታዊ የሆኑ ገንዘብ፣ ህጋዊ፣ ተግባራዊ እና መልካም ስም ነክ የሆኑ ጉዳዩችን ሊጎዱ የሚችሉ መንስኤዎችን መረዳትና መቆጣጠር እንደሚችሉ ነው፡፡የመጨረሻው ግብም ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸውና የተጎጂነት መጠንን ያገናዘቡና ምክንያታዊ ውጤት የሚሰጡ እንቬስትመንቶች እንዲኖሩ ማድረግ ላይ ነው፡፡

## ለ. መሰረታዊ ምክንያት

በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ በመሬት ላይ ኢንቬስት የሚያደረጉ ኢንቬስተሮት በተገቢ መልኩ በመንቀሳቀስ የነሱ ገንዘብ፣ ህጋዊ፣ ተግባራዊ እና መልካም ስም-ነክ የሆኑ የተጎጂነት መንስኤዎች በተሻለ ሁኔታ መረዳትና መቆጣጠር እንዲችሉ መመሪያዎቹ ሊረዷቸው ይችላሉ፡፡ መመሪያዎቹና ተጉዋዳኝ ግብአቶች ከፍተኛ እይታና ተግባራዊ ምክር እንዲኖር፣ የአደጋ ተጋላጭነት መንስኤዎችን ማቋቋም እንደሚቻልና አወንታዊ የገንዘብ ትርፍ እንዲኖርና የአካባቢውን ማህበረሰቦች ተጠቃሚ የመሆን እድል ሊያሳድጉ ይችላሉ፡፡ በመሬት ባለቤትነትና በሰብአዊ መብቶች መካከል ከፍተኛ ትስስሮች መኖራቸው አሌ አይባልም፡፡ በመመሪያዎቹ መሰረት መንቀሳቀስ በተራው የነዚህን መብቶች መከበር እውን ለማድረግ ይረዳል ማለት ጭምር ነው (ኦ ኤች ሲ ኤች አር 2006፤ ምዕራፍ)፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በግብርና ኢንቬስትመንተ ዙሪያ የሚወጡ ህጐች በየግዜው እየተለዋወጡ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ለአስርት አመታት ብዙ ሀገሮች በገንዘብ ድግፍ እጥረት፣ የሰው ሀብት አቅምና የፓለቲካ ፈቃደኘነት መጓደል ሳቢያ የደካማ የመሬት ባለቤትነት አስተዳደር ችግሮች ተጠቂ ሆነው ቆይተዋል፡፡ የዚህ ድክመት ማህበራዊ ተፅዕኖ በመሬት ዙሪያ ካለው እያደገ ከሚሄድ ፍላጎት ጋር ተያይዞ እየጨመረ ሄዷል፡፡ የመመሪያዎቹ በበርከታ ባለድርሻ አካላት ተቀባይነት ማግኘት መንግስታት፣ የሲቪክ ማህበረሰቦች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ)፣ ተጠቃሚዎች፣ የንግድ ድርጅቶች እና ሌሎችን ጨምሮ የመሬት ባለቤትነት መብቶችን መጠበቅና የተሻሻለ አስተዳደር፡- እንደ የአቅም ግንባታ ጥረቶች አስፈላጊነት- ያሉት ፍሬ ማፍራት መጀመራቸው አንዱ ማሳያ ነው፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ የመሬት ባለቤትነት ያላቸው ወገኖች፡- መንግስታት፣ የአባቢው ማህበረሰቦች፣ ግለሰቦች- መሬታቸው ስላለው ዋጋ ያላቸው ግንዛቤ ከግዜ ወደ ግዜ እያደገ ሄዷል፡፡ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች የግብይት አስተዳደሮች በለጋሽ ሀገሮች ድጋፍ መመሪያዎቹን በብሄራዊ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ለማካተት በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በእነዚያ አካባቢዎች ስኬታማ ለመሆን የሚፈልጉ ኢንቬስተሮች መመሪያዎቹን በአግባቡ መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡

---

2 የሙያዊ መመሪያው፤ መንግስትን የግብርና ኢንቨስትመንት ለመከታተል ያግዛል፤ ሌላውን ወደ ህግ ይመራል፤ መመሪያው ቁልፍ የሆኑ ተግባራተ የዓሣ፤ የደን የጾታ እና ነፃ፣ ቅድመ እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ ያጠቃልላል፤

ይህ አድገት እያሳየ የመጣ ክስተት በሌሎች እንደ ሰብአዊ መብቶች፣[3] የስራ መብቶች እና የአካባቢ ጥበቃዎች ካሉ በማህበራዊ ጉዳዩች ዙሪያ ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በርካታ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች መንግስታት የንግድ ስራቸውን ያካሂዱበት የነበረውን ዘይቤ በመለወጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህል የአፍሪካ ህብረትና ሌሎችን ጭምር በቅርቡ የመመሪዎቹን መርሆች በአፍሪካ ውስጥ ሠፋፊ መሬቶችን መሰረት ላደረጉ ኢንቬስትመንቶች በቅርቡ ተቀብለዋቸዋል (2006 ዓ.ም)፡፡ ኃላፊነት የተላበሱ ስለሚባሉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ምንነት የነበረው አረዳድ በጅጉ የተለወጠና በሂደትም በላቀ ደረጃ እየተለዋወጠ መሄዱ አይቀሬ ነው፡፡ ይህም ሰላማዊና ይበልጥ የተረጋጋ የስራ አካባቢን ለኢንቬስተሮችና ለድርጅቶች ለማስፈን መመሪያዎቹን በመሬት ባለቤትነት ህጎች ውስጥ ማካተትና መተግበር ከሀገሮች ይጠበቃል፡፡ ይሁን እንጂ መሰናክሎች በጨመሩ ቁጥር ኢንቬስተሮች ተግባሮቻቸውን እና አሰራሮቻቸውን እንደ ሁኔታው መለዋወጥና ማሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡

ብዙዎቹ የንግድ እንቅስቃሴዎች ስለሂደቱ ግንዛቤ ስላላቸው እንቅስቃሴያቸውን ከዚሁ አኳያ በመቃኘት ላይ ይገኛሉ፡፡ የንግድ ማህበረተሰብ ኃላፊነት በተላበሱ በግብርናና በምግብ ስርዓቶች መርሆዎች (መርሆዎች) በመቅረጽ ሂደቶች ውስጥ ተሳትፈዋል፡፡ ከመርሆዎቹ ውስጥ መርህ 5 የመመሪያዎቹ የመሬት ይዞታ መብትን የሚመለከቱትን በግልፅ ያካትታል እንዲሁም ባለንብረቶች እና የንግድ ተቋማትንም በዚሁ አግባብ እንዲንቀሳቀሱ ያበረታታል (ምግድ 2006 ዓ.ም ሐ)፡፡

## 10ሩ መርሆች በጨረፍታ

1 ለምግብ ዋስትናና ለአመጋገብ ስርዓት አስተዋፅዖ ማድረግ

2 ዘለቄታዊነት ላለውና ሁሉን አቀፍ ለሆነ የኢኮኖሚያዊ እድገትና ለድህነት መወገድ አስተዋፅዖ ማድረግ

3 ለፆታዎች አኩልነት መስፈንና ለሴቶች የስራ ዕድል መፈጠር አስትዋፅኦ ማድረግ

4 ወጣቶችን ማሳተፍና ማብቃት

5 የመሬት ይዞታ፣ የዓሣ ሀብት፣ የደኖች እና ውሃ የማግኘት መብቶችን ማክበር

6 የተፈጥሮ ሃብቶችን መንከባከብና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስተዳደር፣ የሚያገግሙበትን መንገድ ማሳደግና የተፈጥሮ አደጋዎችን መቀነስ

7 ባህላዊ ቅርሶችንና ባህላዊ እውቀትን ማክበርና ልዩነትንና ፈጠራን መደገፍ

8 ሰላማዊና ጤናማ የግብርና ስራንና የምግብ ስርዓቶችን ማስተዋወቅ

9 አሣታፊና የግልፀኝነት አስተዳደር መዋቅሮችን፣ አሰራሮችንና የቅሬታ አፈታት ዘዴዎችን ማካተት

10 ተፅዕኖዎችን መገምገምና ምላሽ መስጠት እናም የተጠያቂነት አሰራርን ማራመድ

እንደ ኔስሌ፣ ኮካ ኮላ፣ ፔፕሲ ኮላ፣ ካርጊል እና ሌሎች ያሉ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ኃላፊነት የጎደላቸው የመሬት ባለቤትነት አሰራሮች ሳቢያ የሚከሰቱ የገንዘብ እና የመልካም ስም ተጐጂነቶችን እየተገነዘቡ በመምጣታቸው እና በአንፃሩም ኃላፊነት በተሞላው መንገድ የሚደረግ እንቅስቃሴ ጠቀሜታነት በመረዳታቸው ለመመሪያዎቹ ግልፅ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ እንደ ባዮማቴሪያልስ፣ ፓልም አይል፣ ስኳር እና ሌሎች ሸቀጦች ላይ የሚተገበሩ የተወሰኑ መስፈርቶች እና የእውቅና አሰጣጥ ስርአቶች አሉ (ባማማአስ 2005፣ ዘዘዘማአስ 2005 ዓ.ም)፡፡

[3] በከፊል እንደተንጸባረቀው ፤ የተባባሩት መንግሰታት መመሪያ በንግድና በሰብዓዊ መብት ሁሉም በስምምነት የተቀበሉት ድንጋጌ በተባባሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ካውንስል በ2011፤ ለበለጠ መረጃ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ መልዕክተኛ ጽህፈት ቤት, 2011) ይመልከቱ፤

በትልልቅ ተቋማት ላይ ኢንቬስት የሚያደርጉ ኢንቬስተሮች በእርሻ ላይ የሚደረግ ኢንቬስትመንት ኃለፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለማካሄድ በሚያስችሉ መመሪያዎች አኳያ መመራትን፣ በስራ ላይ ለዋሉ የመሬት መብቶች ከበሬታ መስጠትን ጨምሮ፣ ይቀበላሉ (UNGC 2006ዓ.ም)፡፡ የዓለም የፋይናንስ ድርጅት (ዓፋድ ፡-) የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግላቸው የግብርና ፕሮጀክቶች ኃላፊነት በተሞላበትና ዘለቄታዊ በሆነ ሁኔታ መከናወን ይችሉ ዘንድ ለመርሆቹ ያለውን ተገዥነት አሳውቋል፤ ብዙ ግዙፍ ባንኮችና ተቋማዊ አበዳሪዎች የዐምድ መርሆዎችን ይተገብራሉ (አንዳንድ ግዜ ትልልቅ ፕሮጀክቶች በኢኩዌተር መርሆዎች መሰረት በሚያበድሩ የግል አበዳሪዎች አማካኝ)፡፡

እንደዚሁም ሁሉ ኃላፊነት በተላበሰ መልኩ ኢንቬስት ማድረግ ፕሮጀክቱ ማህበረሰባዊ የመንቀሳቀሻ የምስክር ወረቀት ሊያስገኝለት ይችላል፡፡ ማህበረሰባዊ እውቅና ባገኘ ነገር ላይ ኢንቬስት የሚያደርግ የንግድ ድርጅት ለኢንቬስትመንቱ ተግባራዊ ማረጋገጫ አለው እንደማለት ነው፡፡ ኢንቬስተሮች የዚህ አይነቱ ማህበረሰባዊ ማረጋገጫ ማግኘት የሚችሉት ኢንቬስት ሊያደርጉባቸው ባሰቡዋቸው ድርጅቶች ወይም መሬት ላይ የተመሰረቱ ፕሮጀክቶች ሊያጋጥሙዋቸው የሚችሉ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተጎጂነትን የሚዳስሱና ተገቢ የትግበራ መረጃዎችን መከተልና መተግበር ሲችሉ ነው (አክስፋም 2006)፡፡

እዚህ ላይ ኃላፊነት የተሞላበት ኢንቬስትመንት ከተለምዷዊው ድረጅታዊ ማህበራዊ ሐላፊነት (የማሀ) ከሚጠይቁ አሰራሮች ባሻገር አርቆ መመልከት የሚጠይቅ መሆኑን ማጤን የግድ ይላል፡፡ ኢንቬስትመንት በሚካሄድበት ማህበረሰብ ውስጥ ቤት ወይም የህክምና ግልጋሎት መስጫ መገንባት ብቻ በራሱ በቂ አይሆንም፡፡ በዚህ መምሪያ ውስጥ እንደተገለፀው እውነተኛ ኢንቬስትመንቶች ከዚህ የላቀ ነገር ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይኸውም ክንውኖቹ ማህበራዊና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን የሚያስወግዱ ብቻ ሳይሆኑ ተጐጂ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር የጋራ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ጭምር መፍጠር የሚችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገሮች ውስጥ ትርፋማ ለማድረግ አቅም ያላቸው ከመሬት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ኢንቬስትመንቶችን እውን ማድረግ ብዙውን ግዜ ከፍተኛ የግብይይት ወጪዎችን ይጠይቃል፡፡ የማህበራዊና አካባቢያዊ ግምግማዎች ማካሄድ (በዚሁ ህትመት ውስጥ በኋላ ላይ እንደሚብራራው) በመሬት፣ በምግብ ዋስትናና በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚኖሩ ተፅዕኖዎችን ጭምር ግምገማና እንደዚሁም ከአካባቢው ማህበረተሰቦች ጋር አመርቂ ምክክር ማድረግ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡

ዳሩ ግን ስህተት በሆነ መንገድ መተግበር የባሰ ወጪን የሚያስከትል ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሣሌ ያህል አንድ ኢንቬስትመንት የአካባቢውን ህዝብ የሚያፈናቅልና እንዲደኸዩም የሚያደርግ ከሆነ ህዝቡ ትግበራውን የማዳከሚያ መንገድ መፈለጋቸው አይቀሬ ነው፡፡ በቅርቡ የተካሄደ አንድ ጥናት በኢንቨስትመንት ዙሪያ ከመሬት መብቶች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች ምንያህል ዋጋ ሊያስከፍሉ እንደሚችሉ መረጃ አቅርቧል፡፡ በአንዳንድ ጫፍ በሚደርሱ ሁኔታዎች ወጪዎቹ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮች ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም ኢንቬስትመንትን በኃላፊነት ማካሄድ ከገንዘብ አንፃር ትርጉም ያለው ይሆናል፡፡ እንደ መንዴን ፕሮጀክት ((2005 ዓ.ም፡3) ከሆነ "በእርግጥም በመሬት የባለቤትነት መብቶች ተጎጂነትን አስመልክቶ የሚገኘው መረጃ አዋጪ የሆኑ የኢንቬስትመንት ግቦችን መምረጥ ያስችላሉ፡፡ ከኢንቬስተሮች ቁልፍ ነገር ጥያቄዎችን ማንሳትና የተጎጅነት አያያዝ ዘዴቻችን መቀየስ መቻል ነው፡፡ በመመሪያዎቹ ላይ በመመርኮዝ ይህ መምሪያ ምን አይነት ጥያቆዎች መነሳት እንዳለባቸው ምን አይነት የተጎጂነት አያያዝ ዘዴዎች መጠቀም እንደሚያስፈልግ ምክር ይለግሣል፡፡

## ሐ. አበይት ተደራሲያን

የዚህ ሙያዊ መምሪያ አበይት ተደራሲያን ገንዘብ የሚያቀርቡ ድርጅቶች ወይም ለኢንቨስትመንት የሚውለውን ገንዘብ የሚያስተዳድሩ እና/ወይም መሬት ላይ የሚውሉ ንብረቶችን የሚያንቀሳቅሱቱ ናቸው፡፡ በመላው ህትመት ውስጥ የዚህ አይነቱ ቡድን 'ኢንቬስተሮች' የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፤ በተቃራኒው ፕሮጀክቱን በትግበራ ወቅት የሚመራው ቡድን "ኦፕሬተር" ተብሎ ይጠራል፡፡(አንዳንድ ግዜ ኢንቬስተሮቹ እራሳቸው ኦፕሬተሮችም ሊሆኑ ይችላሉ)፡፡ እዚህ መምሪያ ውስጥ የተካተቱት ምክረ-ሀሳቦች በአለም አቀፋዊና ሀገራዊ ኢንቬስተሮች በእኩል ደረጃ ያገለግላሉ፡፡ ሁሉም ኃላፊነት በተላበሰ ኢንቨስትመንትና በተገቢ ትግበራ ሂደት ውስጥ ውጤታማ ለመሆን የሚያስችለውን አዋጪ መንገድ ለመፈለግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

አነስተኛ ይዞታ ያላቸው ክፍሎች የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ የኑሮ ደረጃን በማሻሻል ረገድ ወሳኝ ሚና ያላቸው መሆኑ ሳይዘነጋ፤ መምሪያው የሚያነጣጥረው የመሬት አጠቃቀም መብቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የማሣደር አቅም ባላቸው-አወንታዊ አሉታዊ-ትላልቅ የንግድ ተቋማትን እና ምክንያታዊ አሰራሮችን ለመደገፍ ከፍተኛ ኢንቬስትመንት የሚመድቡ ክፍሎች ላይ ነው፡፡[4]

ይህ መምሪያ የሚያነጣጥረው ቀጥሎ በተጠቀሱት የኢንቬስተሮች ምድብ ላይ ነው

- <u>የንብረት ባለቤቶች-</u> እንደ የአነስተኛ የሆቴል ባለቤት፡ኢንሹራንስ ካምፓኒ፡የቤተሰብ ቢሮ፡የግል ባለሀብቶች፡ለልማት የሚሰጥ ሀብት እና የግል ፋውንዴሽን በቀጥታ መሬትን መሰረት ባደረገ ልማት ላይ የሚውል ወይንም በሀብት አስተዳዳሪውች የሚተገበር፡፡
- <u>የመሬት ሀብት አስተዳዳሪዎች -</u> በህዝብ የሚታወቁ ኩባንያዎች ሲሆኑ ዋናው አላማቸው መሬት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስና የመሬት ሀብትን ማስተዳደር ነው፡፡
- <u>ንብረት አስተዳዳሪዎች -</u> ባለንብረቶችን ወክለው ንብረትን የሚያስተዳድሩ ተቋማት ናቸው - ከንብረቱ ጋር የተያያዘ ገንዘብን የማግኘት እና ንብረቱን ለማስተዳደር የሚያስፈልግ የገንዘብ ፍሰትን የማመቻቸት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ እነዚህም ተቋማት ለህዝብ የማይሸጡ አነስተኛ የግል ፈንዶችን፥ በብድር የተገኘ ገንዘብ ፈሰስ የሚያደርጉ ፈንዶችን እና ሌሎች በኩባንያዎች ውስጥ ያሉ የግል ፈንዶችን አይነት መዋቅር ያላቸው የኢንቨስትመንት ማሳለጫዎችን ይጨምራሉ፡፡
- <u>የመንግስት ኩባንያዎች ወይም ፈንዶች-</u> ለአገራቸው ጠቃሚ የሆኑ ሸቀጦችን የሚያገኙባቸውን መንገዶች ለማመቻቸት ይሰራሉ፡፡
- <u>ድንበር ዘለል ኩባንያዎች -</u> ታላላቅ የምግብ እንዲሁም የመጠጥ እና ሌሎች መሰል ኩባንያዎች ሲሆኑ አቅርቦትን እና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ መሬት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ የስትራቴጂያቸው አንዱ አካል ነው፡፡
- <u>የገንዘብ አገልግሎት ዘርፍ -</u> የእርሻ መሬት ላይ መዋዕለ ንዋይ ለሚያፈሱ ደንበኞች የገንዘብ አቅርቦትን የሚያመቻቹ ባንኮችን ይጨምራል፡፡
- <u>በሁለትዮሽ ወይም ከዚያ በላይ ሆነው በጥምር የሚንቀሳቀሱ የልማት ባንኮች -</u> አለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽንን እንዲሁም ክልላዊ እና ብሄራዊ የልማት ባንኮችን ይጨምራል፡፡
- <u>የሸቀጥ ነጋዴዎች -</u> እነዚህ ተቋማት የመሬት ይዞታ ችግሮች ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለንግድ የሆነ ገንዘብ እስከመስጠት እና ሄጂንግ ኢንስትሩመንትን እንደ ስራቸው አካል እስከመውሰድ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

[4] በአነስተኛ እርሻ ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገበትን፤ ከፍተኛ ደረጃ የባለሙያዎች የምግብ ዋስትና ምግብ ጥናት ኮሚቴ ሮም 2013 ይመልከቱ፤

ቀጥተኛ ያልሆኑ ኢንቬስተሮች ከንብረቱ ጥቂት ራቅ ባለ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ምናልባትም ሌላ ፈንድ ላይ ኢንቬስት እያደረጉ፥ ያ ፈንድ ደግሞ በተራው መሬት ላይ ኢንቬስት የሚያደርግ ከሆነ ይህንን መምሪያ በመጠቀም መገምገም እና ከቀጥተኛ ኢንቬስተሮች ጋር መደራደር ይችላሉ፡፡ ይህ መምሪያ በተጨማሪም ቀጥተኛ ያልሆኑ ኢንቬስተሮች ኢንቬስትመንቱን ለማስኬድ ማከናወን ያለባቸው ተገቢ ትጋትን በቀላሉ እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ መምሪያው ቀጥተኛ ኢንቬስተሮችን ወይም ስራውን የሚያስኬደውን አካል በነርሱ ስር ያልሆነ አካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተጽእኖዎችን የሚገመግም አካል መመደብ አለባችሁ በተቀመጠው የግምገማ ስርአት መዋዕለ ንዋይ ከመፍሰሱ በፊት ቢል፥ ቀጥተኛ ያልሆኑ ኢንቬስተሮች ግን ኢንቬስት ሊደረግበት የታሰበው አካል ይህንን እንደ መመዘኛ የሚወስድ ፖሊሲ አለው ወይ ብለው መጠየቅ እንደሚችሉ ያውቃሉ ማለት ነው፡፡[5]

በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ ሌሎች ድንበር ዘለል ወይም የሸቀጣ ሸቀጥ ነጋዴዎች የግብርና ውጤቶችን የሚገዙ ነገር ግን መሬት ላይ ኢንቬስት የማያደርጉ ይህንን ቴክኒካዊ መምሪያ ጠቃሚ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በዋነኛነት ለነርሱ የተዘጋጀ አይደለም፡፡

## መ. ስለመጠን እጅግ በጥቂቱ

በዚህ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ ምክረ-ሐሳቦች በመሬት ላይ ለሚመሰረቱ ኢንቬስትመንቶች በሚያስፈልገው የመሬት ስፋትና የካፒታል መጠን ከቦታ ወደ ቦታ ይለያያሉ፡፡ በትናንሽ ፕሮጀክቶች ላይ ኢንቬስት ለማድረግ የማያሰላስሉና ከዚያም ወደ ትግበራ የሚገቡ ኢንቬስተሮች አብዛኛውን ግዜ በትላልቅ ኢንቬስትመንቶች ሊያደርጉ የሚችሉትን ተገቢ ትጋት በተጎኗኝነት አያያዘ እንቅስቃሴዎች መጠን ማድረግ አይቻላቸውም፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮች የሚጠይቁ ፕሮጀክቶች ምናልባትም በበርካታ ባለሙያዎች እገዛና ከፍተኛ ወጪን በሚጠይቅ ሒደት (ዓ ፋ ድ  የሚጠይቀውን አይነት) በመጠቀም መተግበር ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ትናንሽ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ግን ኢንቬስተሩን ወይም ኦፕሬተሩን ሊያጋጥም የሚችለውን የአደጋ ተጋላጭነት ግምገማ በአነስተኛ የባለሙያ እገዛ ባነስ የገንዘብ አቅም የግድ ማካሄድ ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ግዜ ሁሉ፣ ከሁኔታዎች ጋር ራስን ማስተካከል የሚቻልባቸውን ሁኔታዎችን አጉልቶ ከማሣየት በተጨማሪ ትንንሽ ፕሮጀክቶች የገንዘብ እጥረት ባለበት ሁኔታ ውስጥም እንኳን እንዴት ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ኢንቬስት በማድረግ ተፈላጊውን ነገር ማድረግ እንደሚችሉ በመምሪያው ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ባመዛኙ ይህ ዘዴ መንግስታዊ ካልሆኑ አገር በቀለ ድርጅቶች (መያድ) ጋር አብሮ መስራትን ይጠይቃል፡፡

ይሁን እንጂ ግብይቶች እያደጉ በመጡበት ሁኔታ ውስጥ በእርሻ መሬት ላይ የሚውሉ ኢንቬስትመንቶቻቸውን የተመለከተ ግምገማ ለማድረግ እና ለማስተዳደር ይችሉ ዘንድ ይህን መምሪያ ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

## ሠ. የመንግስት ሚና

መንግስታት የመሬት ይዞታ መብቶችን፣ የምግብ ዋስትናን፣ ሰብዓዊ መብቶችንና አካባቢን የመንከባከብ አስፈላጊነት እውቅና በመስጠትና ብሎም በመጠበቅ ረገድ እጅግ በጣም ጠቃሚ ሚና መጫወት እንደሚችሉ መመሪያዎቹም ያስገነዝባሉ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ መንግስታት ኢንቬስትመቶችን እና ኢንቬስተሮችን በመቆጣጠር ረገድ ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡ በብዙ አካባቢዎች መንግስት የኢንቬስትመንት ውል ፈፃሚዎች ውስጥ አንድ አካል ነው፡፡ የተባበሩት መንግስታት የምግብና የግብርና ድርጅት (ተመምግድ) ‘የግብርና ኢንቨስትመነት ሲካሄድ የመሬት ይዞታ መብቶች አጠባበቅ’ በሚል እርዕስ አንድ ሙያዊ መምሪያ በ2007 ዓ.ም

[5] የኢኳተር መርህ ተግባራዊ የሚሆነው ከተወሰነ የገንዘብ መጠን በላይ በሚያንቀሳቅሱት ተቋማት ላይ ያተኮረ ነው፤

አዘጋጅቶ ነበር፡፡ ይህ መምሪያ ኢንቬስትመንትን የማስተዋወቅ፣ የማጽደቅ እና የመከታተል ሀላፊነት ያለባቸው የመንግስት ባለስልጣናት እንዴት ስራዎቻቸውን ከመመሪያዎቹ ጋር በሚጣጣም መልኩ ማከናወን እንደሚችሉ ምክር ይለግሣል፡፡ ኢንቬስተሮች የመንግስትን ድርሻ በበለጠ መረዳት ከፈለጉ ሌላኛው መምሪያ መመልከት ይችላሉ፡፡

በእርግጥ የግሉ ዘርፍ የመንግስትን ሚና መጫወት አይችልም፤ መጫወትም አይገባውም፡፡ ቢሆንም መንግስት የኢንቨስትመንት ቁጥጥርና የመሬት አስተዳደር ሀላፊነቶችን በሚገባ ለመወጣት ፈቀደኛ ሣይሆንና ሳይችል ሲቀር ኢንቨስተሮችና የንግድ ድርድቶች የመንግስትን ተግባራት እገዛ ሊያደርጉና በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ በሚሚያነት ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ይህ መምሪያ ኢንቬስተሮች እና ኦፕሬተሮች መንግስት ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶችን በሚያከብር እና የኢንቬስተሮችን ተጎጂነት ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ መንግስትን ሊደግፉ እና ሊያጠናክሩ የሚችሉባቸውን መንገዶች ይጠቁማል፡፡ ከዚሁ ጐን ለጐን ኢንቨስተሮች ሁልግዜም ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ህግጋትን ተከትለው መስራት ያለባቸው ስለመሆኑ መምሪያው ያስገነዝባል(አንቀፅ 2.2)፡፡ በመመሪያዎቹ ውስጥ እንደተገለፀው በህግ ከሚጠየቀው ግዴታ ባሻገር መሄድ የግድ የሚሆንባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ስለመናራቸው እንደዚሁ ያስገነዝባል፡፡

# 2

# የመሬት ይዞታ መብቶች

## ወካይ ምልክቶችን እንዴት መጠቀም ይቻላል?

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

በርካታ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች መኖር ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በኢንቬስትመንቱ መግፋት እንደሌለበት ሊያነሳሰው ይገባል፡፡

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በተገቢ ትጋት ምዕራፍ ላይ ፕሮጀክቱን በድጋሚ በመፈተሽና አደጋዎችን የማቃለያ መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# 2. የመሬት ይዞታ መብቶች

## ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

በመመሪያዎቹ ስር እንደተገለፀው የንግድ ድርጅቶችና ኢንቬስተሮች '...ሕጋዊ ይዞታዎችን የማክበር ኃላፊነት አለባቸው።' እንደዚሁም 'የሌሎችን ሕጋዊ የይዞታ መብቶችን ላለመጣስ በተገቢው መንገድ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል'። ይህን ለማድረግ ደግሞ ኢንቬስተሮች 'በህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዳይደርሱና ከደረሱም ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ተገቢ የተጎጂነት አያያዝ ስርአቶችን ጭምር ማካተት' ይኖርባቸዋል። እነርሱ እራሳቸው ወይም ኦፕሬተሮቻቸው 'ሊሣተፉ በሚችሉባቸው ቦታዎች በይዞታ መብቶች ላይ የሚደርሱ ማናቸውንም እውነተኛና መከሰት የሚችሉ ተፅዕኖዎችን መለየትና መገምገም ይኖርባቸዋል'(አንቀፅ 3.2)።

መመሪያዎቹ በተጨማሪ እንደሚያመለክቱት ከሆነ 'ኃላፊነት የተላበሱ ኢንቬስትመንቶች ምንም አይነት ጉዳት ማድረስ የሌለባቸው ከመሆኑም በላይ ይዞታዎችን ህጋዊ የባለቤትነት መብቶችን የሚያሳጡ ነገሮችንና አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን መከላከልና በሎም ሰብአዊ መብቶችን ማክበር አለባቸው'(አንቀፅ 12.4)። በተጨማሪም ኢንቬስተሮች 'ብሔራዊ ሕግጋትን ማህበርና የሌሎችን የባለቤትነት መብቶችንና የህግ የባላይነትን የማወቅና የማክበር ኃላፊነታቸውን መገንዘብ ያለባቸው ስለመሆኑ' ምክር ይለግሳሉ (አንቀፅ 12.12)።

የመመሪያዎቹ መሰረታዊ የሆነው ግብ የፆታዎች እኩልነት ነው። ሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ የህዝብና የግሎቹን ጨምሮ፣ የሴቶችንና የወንዶችን የባለቤትነት መብቶችን በእኩል ደረጃ ማረጋገጥ እንዳለባቸው አፅንኦት ተሰጥቶታል። ከዚህ አኳያ መንግስታት 'የሴቶችና የወንዶች እኩል መብቶች፣ ሁሉንም የሰብአዊ መብቶችን እስከ መጠቀም ድረስ እንዲያረጋግጡ ይበረታታሉ' (3 ለ 4)። እንደዚሁም 'ህጋዊና ፓሊሲያዊ መዓቀፎች ለሴቶች በቂ ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችሏቸውን እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማረጋገጥና የሴቶችን የይዞታ መብቶች የተመለከቱ ህጐች መተግበራቸውንና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው' (አንቀፅ 5.4፤ እንደዚሁም ክፍል 4.6፣ 7.1፣ 7.4፣ 9.6፣ 11.6ን ይመልከቱ)። የግብርና ኢቬስትመንት ውሎች የሚመለከቱ ወገኖች 'የድርድሩ ሂደት ከበሬታ የተሞላበት መሆኑን እና ለፆታዊ ነክ ጉዳዩች ትኩረት የሚሰጥ ስለመሆኑ' እርግጠኛ መሆን እንዳለባቸው መመሪያዎቹ ያስገነዝባሉ (አንቀፅ 12.11)።

በግብርና ስራ ላይ የሚውሉ ኢንቬስትመንቶች ብዙውን ግዜ በሴቶች ላይ ለየት ያሉና ከፍተኛ ተፅዕኖዎች ያሳድራሉ። ወንዶች አብዛኛውን ግዜ ከኢንቬስትመንቶች መጠቀም በሚያስችል በተሻለ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ሲሆን ሴቶች ግን በአንፃሩ በአሉታዊ መልኩ ሊጎዱ የሚችሉ ናቸው። ስለሴቶች ባለቤት የመሆን መብት ሰፊ ውይይት እንዲካሄድ የሚፈልጉና መመሪያዎቹ 'ለሴቶችና ለመንዶች መሬትን ማስተደደር፡- ኃላፊነት የተላበሰ በፆታ እኩልነት ላይ የመሬት ይዞታ አስተዳደር እንዲኖር ለመደገፍ' በሚል ስያሜ በምግድ (ምግድ 2005ዓ.ም) የተዘጋጀውን ህትመት መመልከት ይኖርባቸዋል። ይህም የሴቶች የይዞታ መብቶች ግልፅ መደረጋቸውንና መከበራቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ በዝርዝር የቀረበ ምክርን ይዟል።

## ለ. አደጋው ምንድን ነው?

ህጋዊ የመሬት ነክ መብቶችን በሚጐዳ ነገሮች ሳብያ የሚከሰቱ ጉዳቶችን ለመርዳት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ 'ቴኒዩር' የሚለው ቃል ከመሬት አንፃር በሚኖረው ትርጉም መጀመር ተመራጭ ይሆናል፡፡ ከዚያም የትኞቹ የ'ቴኒዩር' መብቶች ህጋዊ ተደርገው እንደሚወሰዱ ይዳስሳል፡፡ ብዙ ጊዜ ከሚጠቀሱት የመሬት 'ቴኒዩር' ትርጉሞች ውስጥ አንዱ በምግድ (1994 ዓ.ም) መሰረት "በሰዎች መካከል፣ እንደ ግለሰቦችም ይሁን ወይም እንደ ቡድኖች፣ በህጋዊም ይሁን በልማዳዊ መንገድ የሚገለፅ ግንኙነት ነው፡፡ በመሰረቱ የመሬት ባለቤትነት የሚለው ፅንሰ ሐሣብ ሰዎች መሬትን ለመጠቀም፣ ለመቆጣጠርና ሌሎች የማስተላለፍ መብቶቻቸውን የሚወስኑና የሚያስተዳድሩ መብቶችን እና ተቋማትን ይመለከታል፡፡

ጉዳዩን በጣም አቃሎ ማየት ሊኖረው የሚችለው አደጋ ሳይዘነጋ፣ በአጠቃላይ አነጋገር 'የመሬት መብቶች' በሁለት ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህም(1) በግልፅ በህግ የተደነገጉ (እንደ ህገ መንግስቶች፣ ብሄራዊ ህጐችና ደንቦች ያሉትን) እና (2) በልምድ የሚታወቁ መደበኛ ያልሆኑ ወይም ልማዳዊ ህጐች፤ ግን ዳግም የህግ እውቅና በግልፅ የሌላቸው ሊሆኑ የሚችሉና ዳሩ ግን ማህበረሰባዊ እውቅ ያላቸውና የሚሰራባቸው የመሬት መብቶች ናቸው፡፡ የመሬት መብቶች በህብረት ወይም በጋራ ሊያዙ ይችላሉ፡፡ የዚህ መምሪያ አብዛኛዎቹ ተጠቃሚዎች መደበኛ ሲሆኑ የመሬት መብቶች እንግዳ ባይሆኑም ኢ-መደበኛ ለሆኑ ወይም ልማዳዊ ስለሆኑ ሕጐች የሚኖራቸው ግንዛቤ አነስተኛ ሊሆን ይችላል፡፡

ልማዳዊ የመሬት መብቶች ብዙ ግዜ የሚተገበሩት በቡድኖች ልማዶች ላይ በመመስረትና አብዛኛውን ግዜም የአንድ ህዝብ ንኡስ ክፍሎች ተለይተው የሚታወቁ ናቸው፡፡ ምንም እንኳዋን እንደ ሞዛንቢክ ባሉ ሀገሮች ውስን መደበኛው ህግ ለልማዳዊ ህግ በግልፅ እውቅና የሚሰጥ ቢሆንም፣ እነዚህ ህጐች ብዙ ግዜ ያልተፃፉና ምናልባትም ከቡድኖቹ ውጪ ባሉ ሰዎች የማይታወቁና በመደበኛው ህግም እውቅና የሌላቸው ናቸው (ታነርና ቢቸሪ 2006 ዓ.ም)፡፡ የተለምዶ ህጐች ከመደበኛው ህግ ጋር እንኳን ሳይቀር ሊጋጩ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ብዙ ግዜ የሚከሰተው የሴቶችን የመሬት መብቶች በተመለከተ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ በበርካታ የዓለም ክፍሎች፣ በተለይም በአፍሪካ የመሬት መብቶች በአመዛኙ የሚወሰኑት በልማዳዊው ህግ ነው፡፡ በብዙ ቦታዎች መብቶችና መሬት የማግኘት ዕድልን በተመለከተ ከመደበኛ እና በኢ-መደበኛዊው አሰራሮች መካከል ያለው መስተጋብር ግራ መጋባትን፣ ውጥረቶችን እና ውዝግቦችን ያስከትላል፡፡ ስለዚህም እነዚህን ነገሮች ችላ ማለት የሚችለው በጣም ከፍተኛ አደጋ እንዲያጋጥመው የሚፈቅድ ኢንቬስተር ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ምናልባትም እጅግ በጣም ፈታኝ የሆኑ ሁኔታዎች የሚከሰቱት በአንድ መሬት ላይ ተመሳሳይ የባለቤትነት መብቶች ጥያቄ በሚነሱባቸው ቦታዎች ነው፡፡ ለአብነት ያህል በብዙ ሀገሮች፣ ማህበረተሰቦች፣ ቤተሰቦችና ግለሰቦች የቆዩ ልማዳዊ የመሬት አጠቃቀም ህጐች ሊኖራቸው በሚችሉባቸው አካባቢዎች ህጋዊ የመሬት ባለቤትነት መብት የሚኖረው መንግስት ነው፡፡ መንግስትና የልማዳዊው ህግ ተጠቃሚዎች የሆኑት ሁለቱም ህጋዊ ተደርገው ሊታዩ የሚችሉ የባለቤትነት መብቶች ይኖሩዋቸዋል፡፡ በሌሎች እንደ አርብቶ አደሮች ባሉት የሚያዙ መብቶች ደግሞ ወቅታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንደነዚያ ባሉ ሁኔታዎች የአርብቶ አደሩ ማህበረሰቦች የተወሰኑ ቦታን በዓመት ውስጥ ለተወሰኑ ግዜያት ብቻ ለከብቶቻቸው በግጦሽነት ከትውልድ ትውልድ ተጠቅመውበት የነበረ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ምንም አይነት በህጋዊነት የተመዘገበ የመሬት ይዞታ መብቶች ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ቢሆንም ለመጠቀም ያላቸው መብቶች በሌሎች በአካባቢው በሚገኙ ማህበረሰቦች ተቀባይነት ያላቸው ለሆኑ ይችላሉ፡፡

ይህ ደግሞ የትኞቹ የመሬት ባለቤትነት መብቶች ናቸው? ህጋዊ ሊባሉ የሚችሉት የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በመመሪያዎቹ ግልፅ እንደተደረገው ሁሉ እንደነዚያ ያሉት መብቶች መደበኛ መብቶችንና እንደዚሁም የህግ ከለላ የሌላቸውን ግን ደግሞ እንደ ህጋዊ የሚቆጠሩ ልማዳዊ መብቶችን ይጨምራሉ (5-3) ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር መደበኛና ተለምዶዋዊ የመሬት ባለቤትነት መብቶች ሁለቱም እንደ ህጋዊ መቆጠር እንደማይችሉ ነው፤ ታድያ የትኞቹ ናቸው የምር ህጋዊ መባል የሚችሉት? (AFD 2006:18)፡፡ መመሪያዎቹ ይህን አስመልክቶ ቁርጥ ያለ ምላሽ አይሰጡም፤ ሆኖም ህጋዊ የሆኑት የባለቤትነት መብቶች የትኛዎቹ እንደሆኑ መወሰን የሚችልበትን መንገድ በግልፅ ያመለክታሉ(አንቀፅ 4.4)፡፡ በዚህ መምሪያ ውስጥ በጉዳዩ ላይ ረዘም ያለና ጥልቀት ያለው ዳሰሳ ማድረግ የማይቻል በመሆኑ፤ በምግድ (2007 ዓ.ም ለ) መሰረት ማለት የሚችለው በህግ ግልፅ እውቅና ያላቸው የባለቤትነት መብቶችም ሆኑ በማህበረተሰቦች በጣም ረዘም ላለ ጊዜ እንደ ህጋዊ ይታዩና ይሰራባቸው የነበሩ ግን ደግሞ ግልፅ የህግ እውቅና የሌላቸው ልማደዊ ወይም ኢ መደበኛ መብቶች

በሙሉ ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ በተገቢ ትጋት ፕሮጀክት ቀረፃ በሚያካሂዱ ኢንቬስተሮችም እንደ ህጋዊ ተቆጥረው ተቀባይነት ሊያገኙ ይገባል፡፡

በእርግጥ ማህበረሰቦች በሙሉ አንድ ወጥ ቡድን አይደሉም፡፡ እንዲያውም የተለያዩ የየራሳቸው ቅድሚያ የሚሰጡዋቸው ነገሮች፣ ውስንነቶች እና ሀይል ያላቸው ቡድኖችን የሚያቅፉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የገጠር ሴቶች ወይም በተለይ ተጋላጭ የሆኑ አንዳንድ የማህበረሰቡ ክፍሎች ባህላዊ ወይም ማህበረሰባዊ መገለል ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ የማህበረሰቦችን የመሬት መብቶች ለማወቅና ለማክበር የሚደረጉ ጥረቶች ለተገለሉና ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ክፍሎች ልዩ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

'ህጋዊነትን'የተመለከቱ አመለካከቶች በመንግስትና በማህበረሰቦች፣ እንደዚሁም በማህበረሰቦቹ በራሳቸው ውስጥ ወይም በመካከለቸው የከረረ የመከራከሪያ ርዕስ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ያህል በተወሰነ መሬት ላይ በአመት ውስጥ ለጥቂት ወራት ብቻ የቆዩ አርብቶ አደሮች በሚኖራቸው የመሬት መብቶች አይነትና መጠን ላይ የአርብቶ አደሩ ቡድኖችና በቋሚነት ነዋሪ የሆኑት ገበሬዎች ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ነባር ማህበረሰቦች ወይ አካባቢው በስደት የሄዱ ማህበረሰቦች ይገባናል ስለሚሏቸው መብቶች ህጋዊነት፣ ቢያንስ ቢያንስ የነዚህን መብቶች ጥንካሬና እንደዚሁም የፕሮጀክት ኢንቬስትመንትን አስመልክቶ ድርድር ሲካሄድ ስለሚኖራቸው ቦታና ከፕሮጀክቱ ከሚገኙ ጥቅሞች ስለሚያኖራቸው ድርሻ ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡

ከመሬት ይዞታ መብቶች ጋር በተገናኘ የሚያጋጥም አደጋ የሚመነጨው ለእነዚህ መብቶች በቂ እውቅና ካለመስጠት፣ ካለማካተትና ካለማክበር የተነሳ ነው (USAID 2007ዓ.ም ሉ፡9)፡፡ መሬት ነክ መብቶች በሙሉ የሚዳኙት በመደበኛ ህግ በሆነባቸውና ተገቢና ግልፅ የሂሣብ አያያዝ ስርአቶች አላቸው ሊባሉ የሚችሉ ያደጉ ሀገሮችን የመሬት ባለቤትነት ምዝገባና አስተዳደር ስርዓቶች ለተለመዱ ኢንቬስተሮች፣ በአብላጩው የዓለም ክፍል ውስጥ አካባቢያዊ መብቶችን ማካተት ቀላል ነገር አይሆንም፡፡ በርካታ በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገሮች ባላቸው ደካማ የመሬት አስተዳደሮች ሳቢያ መደበኛ የሆኑትን መብቶች እንኳዋን ለይቶ ማወቅ አዳጋች ይሆናል፡፡ ከዚህም የተነሳ በመሬት ላይ የሚደረጉ ኢንቬስትመንቶች ብዙውን ግዜ የአካባቢውን ነዋሪዎች የመሬት መብቶች በበቂ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይሳናቸዋል፡፡ (መንዴን ፕሮጀክት 2005፡10)፡፡

በUSAID (2007ዓ.ም ሉ፡9) መሰረት ባለመጠየቃቸው እና /ወይም በፕሮጀክት ተጎጂ በመሆናቸው ሳቢያ ቅሬታ የሚያድርባቸው ነዋሪዎች የፕሮጀክቱን ትግበራ በተቃውሞች ወይም በሌሎች ዘዴዎች ሊያግዱ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ማህበረሰቦች እንደ ይዞታቸው በሚቆጥሩት መሬት ላይ በሚተገበሩ ኢንቨስትመንቶች ላይ ተቃውሞ ያነሳሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ሚርዛና ለሎች (2006 ዓ.ም) እንደገለፁት ከሆነ በ39 ሰፋፊ የግብርና ኢንቬስትመንቶች ላይ የተደረገ አንድ ጥናት በጣም በተደጋጋሚ የፕሮጀክቶቹ አሉታዊ ተፅዕኖዎች መሬት-ነክ ጉዳዩችን የሚመለከቱ ስለመሆናቸው ጥናቱ ከመደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

መቀላቀሎችን፣ ማስተላለፎችን ወይም 'ብራውንፊልድ' ፕሮጀክቶች የሚካተቱባቸው እና በተለይም ኢንቬስተሩ በመተግበር ላይ የነበረ ፕሮጀክትን ከሌላው የሚወስድበት ሁኔታ ከኖረ አስቸጋሪ ነገር ሊፈጠር ይችላል፡፡ ኢንቬስተሩ መሬቱ ከመነሻው እንዴት እንደተገኘ፣ መሬቱን የተመለከተ ወቅታዊ ግጭቶች፣ አካባቢውን ጉስቁልና ወይም የስብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ ያለው መረጃ ያልተሟላ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚሁም መሬት ሻጩ ወይም በአካባቢው ያለ ሸሪኩ በሙስና ወይም በስብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተግባር ላይ ተሳታፊ ይሁን አይሁን ማረጋገጥ አዳጋች ሊሆን ይችላል (ምዕራፍ 5 እና 6ን ይመልከቱ)፡፡ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ እንደተብራራው ለአንድ ኢንቬስተር ወይም 'ኦንሬተር ከግሪን ፊልድ' ሁኔታ ውስጥ ሊከሰት የሚችል አደጋን ከማስወገድ ይልቅ ' በብራውን ፊልድ ' አካባቢ አስቀድሞ የነበረ ጉዳትን ማቃለል የበለጠ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡

የዚህን አይነቱን በመሬት ይዞታ መብት ላይ የሚያጋጥም አደጋ ለማስወገድ አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ አለመቻል በጣም ውድ ዋጋ አስከፋይ ውጤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡ በ2004 ዓ.ም፣ የመንዴን ፕሮጀክት የአካባቢ ነዋሪዎችን የመሬት መብቶች ወደ ጐን በመተው የገንዘብ ጉዳት ማስከተሉን የሚገልፅ በስፋት የተነበበ ዘገባ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ጉዳቱም ከከፍተኛ የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ጭማሪ እስከ ፕሮጀክቱን ሙሉ በሙሉ በማቆም ሳብያ የተከሰቱ ወጪዎች የሚደርስ መሆኑን ጠቅሷል (መንዴን ፕሮጀክት 2004፡3)፡፡ ይኸው ዘገባ ሶስት ሰፋፊ ድምዳሜዎች ላይ ደርሷል፡፡

1. በመሬት ይዞታ መብት ዙሪያ የሚነሳ ጥያቄ፣ 'ውጫዊ' ከመሆን በላቀ መልኩ፣ ከኢንቨስትመንት በቋሚነት ሊገኝ በሚችለው የገንዘብ ትርፍ ላይ ትልቅ አደጋ ሊሆን እንደሚችልና፣ እንደዚሁም በመሬት-ነክ ኢንቬስትመንት ላይ በሚደረግ በማንኛውም የተጎጂነት ግምገማ፣ የብድር መጠን ትንተናን ኢንሹራንስ ክፍያን ጨምሮ፣ ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ መሆኑን፤

2. ገንዘብን በተመለከተ የሚነሱ ተጐጂነቶች ዘርፈ ብዙዎች መሆናቸውነ እና ይህም ስራው ለተወሰነ ጊዜ በመገታቱ ምክንያት የሚደርስ የግንባታ ግዜ መራዘምና ካልታሰበ የገንዘብ ፍሰት ኪሳራ አንስቶ የኢንሹራንስ ሽፋን እጦቶችን ተከትሎ እስከ ሚመጣ የንብረቶች መወረስ ይደርሳል፡፡ የተጎጂነቱ መጠን መባባስ በጣም የተፋጠነና የማይቀለበስ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በተራው ጉዳዩን በአግባቡ መያዝ ይቻል ዘንድ ተለምዷዊዎቹ የአደጋ አረዳድና የማቃለያ ዘዴዎችን ማጐልበት የሚያስፈልግ መሆኑን ይመለከታል፡፡

3. እነዚህ አደጋዎች በንግድ ተቋሙ ወይም በኢንቬስተሩ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ ከፍተኛ ከመሆን እስከ ውድመት ሊደርስ ይችላል፤ ወይም የመነሻ ንድፍ ስራ (የሚጠቁመው ነገር ቢኖር) ከመሬት ይዞታ መብት ጋር የተያያዙ ችግሮች የሚያጋጥሙት ኢንቬስትመንት ወጪው በከፍተኛ መጠን ሊጨምር እንደማችል ነው፡፡ በወጪ ላይ እንደዚያ ያለ መጠነ-ሠፊ የዋጋ ግሽበት ክስተት የውሳኔ አሰጣጥን ለማስለወጥና፣ የአደጋ መድረስ አይቀሬ ስለመሆኑ ግንዛቤ መኖሩን ማረጋገጥ ስለማስፈለጉ በቂ ምክንያት ይሆናል (መንዴን ፕሮጀክት፣ 2004 ዓ.ም፡5)

ቀጣዩ ክፍል እነዚህ የጐሉ አደጋዎች እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ይዳስሳል፡፡

## ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

አንድ ኢንቬስተር በመሬት ይዞታ መብት መንስኤነት በፕሮጀክት ላይ ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ለመቀነስ ምን ማድረግ ይችላል? ከዚህ አኳያ በተገቢው ትጋት እና በፕሮጀክት ቀረፃ ወቅት መወሰድ የሚገባቸው ሶስት እርምጃዎች አሉ፡- (1) የመሬት መብቶችን በመላ አብጠርጥሮ መለየትና እውቅና መስጠት፤ (2) ፕሮጀክቱ በነዛ መብቶች ላይ ሊያሰድር የሚችላቸውን ተፅዕኖዎች መገምገም፤ እና (3) ጉዳትን ለማስወገድ ወይም ወደሌላ እድል ለመሸጋገር ፕሮጀክቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ናቸው፡፡

### 1. ለመብቶች እውቅና መስጠት

በቅድሚያ ህጋዊ የመሬት መብቶችን ለማክበር የሚፈልግ ሰው የእነዚያ መብቶች ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ በኢንቬስትመንት ሣቢያ ህጋዊ የመሬት ባለቤትነት መብቶች እንዳይጣሱ የሚፈልግ ሰው መጀመሪያ ማድረግ ያለበት መደበኛም ሆነ ኢ-መደበኛ የመሬት መብቶች ያሏቸው ባለይዞታዎች በሙሉ በቅጡ መለየታቸውንና ተመዝግበው መያዛቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ሂደት መሬቱ የሚገኝበትን ሁኔታ እና መጠኑን ብሎም የሚስተዋሉ መጠነ መሻሻሎች መወሰንን ማካተት ይኖርበታል፡፡ (ባዘማአስ ፣ 2005 ዓ.ም ፡1)

መብቶችን ለማወቅ በመጀመሪያ ደረጃ መወሰድ ያለበት እርምጃ ብሄራዊ መደበኛና ልማዳዊ የመሬት ይዞታ መብት ህጐችን፡- መደበኛው ሕግ ልማዳዊውን ህግ ምን ያህል እንደሚያካትት ጭምርና፣ እንደዚሁም ተገቢነት ያላቸው የመንግስት ተቋማትን አስተዳደራዊ አሰራሮች፣ የክርክር አፈታት ዘዴዎችንና ትግበራዎችን ይጨምራል (USAID፣ 2007 ዓ.ም ለ፡18፤ AFD፣ 2006 ዓ.ም፡18)፡፡ በUSAID 2007 ዓ.ም ሀ ምልከታ መሰረት፣ ምንም እንኳን በአንድ አገር ውስጥ የመሬት ይዞታ መብት ስለሚገኝበት ሁኔታ መሠረታዊ ግንዛቤ ማስጨበጥ የሚችሉ ጥሩ የመረጃ ምንጮች ሊገኙ ቢችሉም አብዛኛዎቹ ኢንቬስተሮች ከዚህ ደረጃ ላይ የባለሙያ እርዳታ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል፡፡

ቀጥሎ መደረግ ያለበት ደግሞ ብሄራዊ የመሬት ማህደሮችን በተመለከተ ጥንቃቄ የተመላበት ዳሰሳ ማድረግና የመንግስት ባለስልጣናትን ማነጋገር ነው፡፡ የሚካሄደው ዳሰሳ መንግስት በምን መልኩ የመሬት ምደባ እንደሚያወጣ (የመንግስት) የህዝብ፣ የግል ወይም ልማዳዊውን)፣ መሬቱ የተወሰነ ጥበቃ የሚደረግለት መሆን አለመሆኑን (ለልማት ወይም ለደን ጥበቃ የመሳሰሉትን)፣ እንደዚሁም ከተቻለ ሰዎች በመሬቱ ላይ ያላቸውን የመጠቀም መብቶች የሚጠይቁት ምን ያህል እንደሆነ፡- በዓመቱ ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ወይም ዓመቱን ሙሉ ማሳየት አለበት፡፡ (ባዘማአስ፣ 2003 ዓ.ም፡4)

የመንግስት ማህደሮች መቃኘት አስፈላጊ ነው፤ ዳሩ ግን በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች የሚገኘው መረጃ አጥጋቢ ያልሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ብዙ ግዜ የመስክ ላይ ግምገማ፤ እንደ ባለድርሻ አካላት መለያ ሂደት አንድ ክፍል ተቆጥሮ፣ መደረግ አለበት፡፡ ቀጥሎም በመንግስት ማህደሮች ውስጥ ግልፅ ያልተደረጉ መብቶችን፣ የመጠቀም መብት ያላቸውን ወይም የመጠቀም ውል መፈፀም የሚፈልጉትን ጭምር፤ ለመለየት ይረዳል፡፡ የባለ-ድርሻ አካላትን የመለያ ስራ ሊኖር የሚችለውን የመብት ባለቤቶችን አድማስና በምክክሮች አጠቃላይ ሂደት ውስጥ መሣተፍ የሚገባቸውን ለመለየት ሊረዳ ይችላል፡፡ በመሆኑም ለምክክር፣ ድርድር እና ፕሮጀክቱ የሚቀጥል ከሆነ ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችል መሰረት ሊጥል ይችላል (ምዕራፍ 3ን ይመለከቱ)፡፡

የባለድርሻ አካላትን የመለየት ስራ የአካባቢውን ነዋሪ ከጅምሩ አሳታፊ በሆነ መንገድ ማካሄድ አስፈላጊነት ይኖረዋል፡፡ ይህ ክንውን ተጐጂ ከሆነ ከሁሉም የማህበረሰብ ክፍሎች ጋር፣ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ አርብቶ አደሮችን እና በተለይም በእጅጉ የተገለሉ ሌሎች ቡድኖች ጭምር ጋር ሰፊ መስተጋብርን ማስከተል ይኖርበታል፡፡

የሚያካሂደው ግምገማ መብቶች ያሏቸውን ብቻ ሳይሆን እነዚያን መብቶች አይነትና መጠን፣ እንደዚሁም መሬቱ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ እንደሚገኝ ጭምር ማሳየት አለበት፡፡ መሬቱ የሚገኘው በነባር ህዝቦች ቁጥጥር ስር ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ሁኔታዎች መብቶች የጋራ ወይም የሚጋጩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶች በሌሎች መሬት ላይ የሚያርሱ ጨሰኞች፣ ሌሎች መሬቱን ለከብቶቻቸው በግጦሽነት በግዜያዊነት የሚጠቀሙ እንደ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ክፍሎች ያሉት፣ ያሏቸው የመጠቀም መብቶች ግዜያዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ያምሆነ ይህ ሁሉም መብቶች ተለይተው መታወቅ አለባቸው፡፡

የተለያዩ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉዋቸው ነገሮች በከፍተኛ ደረጃ የሚለያዩ በመሆኑ መብቶችን የመለያ ስራ የሚጠይቀው ወጪ ምክንያታዊ ነው ሊሰኝ የሚችል ነው፡፡ ለአንድ ሄክታር የሚያስፈልገው ወጪ በአንድ ጥናት (መንዴን ፕሮጀክት፤ 2007 ዓ.ም፡ 26) መሰረት US $0.15 እስከ US $ 0.30 ይደርሳል፤ ሆኖም የሚያስፈልገው ወጪ ከዚህ በጣም በከፍተኛ መጠን ሊጨምር ይችላል፡፡ ገንዘብ ለመቆጠብና ማህበረሰቡ ላይ ሊኖር የሚችለውን የወጪ ጫና መቀነስ ይቻል ዘንድ መብቶችን የመለየቱ ሂደት ከሌሎች መረጃ የማሰባሰቢያ ዘዴዎች ጋር በተጓዳኝነት ሊሰራ የሚችልና መሰራት ያለበትም ነው፡፡ እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ ይህ ሂደት ዓማተግ የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ ሊካሄድ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በምግድ የተፈጠሩት እንደ SOLA እና ግልፅ የይዞታ መብት አያያዝ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ያሉት ለማህበረሰብ አቀፍ መለያ ስር የሚያገለግሉ ቀልጣፋና ዋጋቸው ረከስ ያሉ አሰራሮችን በማቅረብ ላይ ይገኛሉ (መእድ፣ 2007 ዓ.ም፡ሀ)፡፡

## 2. በመሬት መብቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን መገምገም

መጠቀሱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል ሊባል ቢችልም፣ ኢንቬስትመንት ሊካሄድ በታሰበበት አካባቢ ያለውን የባለይዞታዎች ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች መለየት በራሱ በቂ አይሆንም፤ ከዚህ ጐን ለጐን የሚያስፈልገው ወጭ በእነዚያ መብቶች ላይ ያለውን ተፅዕኖ መገምገም የባለ መብቶችን ባለቤቶች ውሳኔ ሊጐዱ ስመለቻል/አለመቻል ውሳኔ ላይ መድረስ በእኩል ደረጃ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ (ውሁገን 2006 ዓ.ም፣ 22-23)፡፡

መመሪዎቹ ፕሮጀክቶቹ ሊኖሩት የሚችሉትን አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ቅድመ ግምገማዎች መኖር እንዳለባቸው ያሰገነዝባሉ (አንቀፅ 12፡10)፡፡ በብዙ ሁኔታዎች የአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክ (አኢባ 2005ዓ.ም) እና ሌሎች እንደነዚያ ያሉ ግምገማዎች መካሄዳቸውን ይፈልጋሉ፡፡[6]

---

[6] በአንድ ጥናት የተሰጠው ምክረ ሀሳብ የሚያሳየው የአካባቢ መረጃ የጉዳት ግምገማ መረት ማድረግን ይጠይቃል፡፡( ሙደን ፕሮጀክት፣2013፤21)

ሳጥን 3፡-
የሴቶች የመሬት ይዞታ
መብቶች

> የመሬት መብቶች የመለያ ስራ አካል በማድረግ የሴቶችን የመሬት ይዞታ መብቶች ለይቶ ማወቅ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በአብዛኛዎቹ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ሴቶች የመሬት ባለቤት የመሆን፣ የመቆጣጠርና የማግኘት አቅማቸው እጅጉን የተገደበ ነው፡፡ ሴቶች የሚይዙት መሬት ከወንዶች በጣም ያነሰና የመሬት ይዞታ መብቶቻቸው የሚረጋገጡላቸው በዝቅተኛ ደረጃ ነው፡፡ መሬትን አስመልክቶ በሚካሄደው የውሣኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ሴቶቹ ድምጻቸውን ለማስማት አደጋች ሆኖ ያገኙታል፡፡ በመሆኑም መሬት ለንግድ ተቋማት የሚያዝ በመሆኑ ሴቶች ለመሬት፡- ለእርሻም ሆነ ግንባታ ነክ ላልሆኑ የደን ውጤቶች ያላቸው አቅርቦት አናሳ ስለሚሆን እጅጉን ለጉዳት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡ የሴቶች የመሬት ይዞታ መብቶችን የሚያዳክሙ ኢንቬስትመንቶች በተለይም በቤተሰብ የምግብ ዋስትናና በደህንነታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ያሳድራሉ፡፡
>
> በመሬት ላይ የሚደረጉ ኃላፊነት የተላበሱ ኢንቬስትመንቶች ሴቶች ያሏቸውን የመሬት ይዞታ መብቶች ማክበርና ከተቻለ ማጠናከር ያለባቸው ስለመሆኑ በስፋት ስምምነት የተደረሰበት ነው፡፡ ለምሣሌ፡- ከመርሆዎቹ ወስጥ ሶስቱ፣ ኃላፊነት የተላበሱ ኢንቬስትመንቶች የፆታዎችን እኩልነት ማስፈንና ሴቶችን በተለያዩ መንገዶች፡- ሴቶች እኩል የመሬት ይዞታ መብቶች ያሏቸው መሆኑን የሚያሳይ አቋም ለመውሰድና፤ እንደዚሁም አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችንና ግብዓቶች ያሏቸውና በማህበረሰብ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ በሚገባ መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን በማረጋገጥ ጭምር የመሬት አቅርቦትና የተፈጥሮ ሀብቶች አቅራቦት እንዲኖራቸው ማድረግ አለባቸው ይላል፡፡

በምግብ ዋስትና እና በሰብአዊ መብቶች ጭምር ላይ የሚኖሩ ተፅዕኖዎች ግምገማ የአጠቃላይ የዓማተግ አንዱ ክፍል መሆን አለበት፤ የተለየ ክንውን መሆን አይኖርበትም ማለት ነው፡፡ ግምገማው የሚካሄድበት መንገድ እና ግዜ የሚወሰነው ሊካሄድ በታሰበው ኢንቬስትመንት ልዩ ሁኔታዎች፣ ባካባቢው ማህበረሰብ ፍላጐቶች እና አቅም እንደዚሁም በኢንቬስትመንቱ አይነትና መጠን ጭምር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ውል ከተፈጸመ በኋላ የሚኖሩት አማራጮች ውስን በመሆናቸው ግምገማው መካሄድ ያለበት በተገቢ ትጋት እና ወቅት ማለትም ስምምነቶች ላይ ከመድረሱ በፊት እና ወደ ፕሮጀክት ትግበራ ከመገባቱ አስቀድሞ ነው (AFD፣2006 ዓ.ም ገፅ 22)[7]፡፡ እዚህ ላይ በመንዴን ፕሮጀክት (2005 ዓ.ም፡ 21-22) መሰረት ይበልጡን አስፈላጊ የሚሆነው ነገር፡ የተፅዕኖ ግምገማው በአካባቢው ነዋሪ ላይ ከሚኖሩ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ጋር ተያይዞ የሚከሰት አደጋ አያያዝ ዋነኛው ክፍል እንዲሆን ማድረግ ላይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የግምገማው ውጤት ተጨባጭ እና ተዓማኒ መሆን ይችል ዘንድ ግምገማው በገለልተኛ ባለሙያ መከናወን ይኖርበታል (መንዴን ፕሮጀክት፤ 2005 ዓ.ም፡ 21-22)፡፡ የመሬት ይዞታ መብትን አስመልክቶ የሚካሄድ የተፅዕኖ ግምገማ ታድያ ባለ ይዞታዋች ባሏቸው መብቶች ላይ የሚኖሩ ተፅዕኖዎችን በሙሉ፣ የሚከተሉትን ጭምር ማሳየት ይኖርበታል፡-

- መሬት ሊገኝበት የሚቻልበትን መንገድና የመሬት ግብይት እንዴት ሲካሄድ እንደቆየ፣ በተለይም መሬቱን ለህዝብ ጥቅም ለማዋል በመንግስት ለመውሰድ የታሰበበት ግዜ ኖሮ ከነበረ፤
- ፕሮጀክቱ ሰዎችን፤ ያለፍቃዳቸው ወይም በፍቃዳቸው በሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ የሚያደርግበት ሁኔታ ስለመኖሩ፤
- መሰረተ-ሰፊ አሳታፊ የምክክር ሂደት ሊኖር ስለመቻሉና፣ ከሆነም ተሳታፊዎቹ እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ፤ (ስለምክክር የሚያብራራውን ክፍል ይመልከቱ)
- ድርድሮች ሲደረጉ ተሳታፊዎቹ እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉና ፕሮጀክቱ ቀጣይነት የሚኖረው ከሆነ ውል ፈራሚዎቹ እነማን እንደሚሆኑ፤
- በግብይቱ ይሰማማል ተብሎ ስለሚገመተው ግለሰብ ወይም ተቋም ያለው ህጋዊ መሰረትና የመሬቱ ህጋዊ ባለቤት መንግስት ሊሆን ከቻለ፣ የመሬቱ ተጠቃሚዎች (ኢ-መደበኛ የመጠቀም መብቶች እንጂ በመሬት ላይ የባለይዞታነት መብቶች የሌላቸው) በሂደቱ እንዴት መሣተፍ እንደሚችሉ፤
- በመሬቱ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ስለመኖራቸው፤
- መሬቱን ከመጠቀም ወይም ከመቆጣጠር ፍላጐት ጋር በተያያዘ ግጭት ወይም ከዚያ ባለፈ አመፅ ኖሮ ያውቅ እንደሆነ፤
- ኢ-መደበኛ የመሬት መብቶች አለን ሊሉ የሚችሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ የሚስያብሉ ስፍራዎች መሬቱ ላይ ስለመኖራቸው፤

---

[7] የአካባቢያዊና የማህበረሰባዊ ተፅዕኖ ግምገማ፤ ሰነዱ ከመፈረሙ በፊት  እንደሚቀረብ ቢታወቅም፤ ተግባራዊ የሚሆነው ከፊርማ በኋላ ነው፤ ፕሮጅክቱ  በመሬት ይዞታ ላይ እና በሰብዓዊ መብት ላይ  ጉልህ ጉዳት ካደረሰ ውሉ ሊሰረዝ እንደሚችል ይደነግጋል፤ ሰሞለር፣2014

- በነባር ህዝቦች፣ በሴቶች እና በወጣቶች የመሬት ይዞታ መብቶች እና እንደዚሁም እንደ አርብቶ አደሮች ላሉት ወቅታዊ መብቶች ላይ ሊኖሩ የሚችለውን ተፅዕኖ፤
- ሊኖሩ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ ማናቸውም ጎጂ ተፅዕኖዎች እንዴት ሊቃለሉ እንደሚችሉ የሚሉትን ይጨምራል (ኤ ኤፍ ዲ፣ 2006 ዓ.ም 61-62፣69)።

በተባበሩት መንግስታት የንግድ እና ልማት ጉባኤ (ተመንልጉ) በመሰለ ሁኔታ ላይ በቅርቡ በተካሄደ ጥናት እንደተገለፀው፣ ሁኔታዎች ብዙውን ግዜ ውስብስብ በመሆናቸው የሚኖረውን ተፅዕኖ ለመረዳት ቀላል አለመሆኑን እና፤ እንደዚሁም በኢንቬስተሮች እና በአካባቢው ማህበረሰቦች መካከል ለተፈጠረው ግጭት በተደጋጋሚ መንስኤ የነበረው መሬትን ለመጠቀም ወይም ህጋዊው የመሬት ባለይዞታ ለጊዜው ሳይጠቀምበት የቆየ መሬትን ከተገቢ በላይ ያለአግባብ የራስ ማድረግ ነበር። ህጋዊ የባለቤትነትና የመጠቀም መብት የነበራቸው የበፊተኞቹ የመሬት ባለቤቶች (መንግስት ወይም ቀደምት ኢንቬስተሮች የነበሩቱ) ግን ደግሞ መሬቱን ሳይጠቀሙበት መቆየታቸው በሁሉም ቦታዎች በተደጋጋሚ የተስተዋለ ክስተት ነው። በዚህ ክፍተትም ሌሎች ሰዎች መሬትን መያዝ፣ ማዘጋጀትና ማረስ ብሎም ህጋዊ ያልሆኑ መብቶችን በራሳቸው መስጠት ችለዋል። መሬቱም እንደነዚህ ባሉ ሰዎች በመያዙ ምክንያት የስራ ፈቃድ የተሰጣቸው ወይም መሬቱን ያገኙ አዳዲስ ኢንቬስተሮች አንዳንድ ግዜ በመሬቱ ላይ መብቶቻቸውን በስራ መተርጎም አዳጋች ሆኖ አግኝተውታል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ እንዲያውም አዲሶቹ ኢንቬስተሮች ከመምጣታቸው በፊት ሰዎች መሬቱን ለአስርት አመታት ወይም ለብዙ ትውልዶች ሲጠቀሙበት የነበረ ነው (ሚርዛ እና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም 36)።

በመሬት ይዞታ መብት ላይ የሚኖር ተፅዕኖን አስመልክቶ አሳታፊ በሆነ መልኩ የተሰራ ግምገማ (እንደ የአጠቃላይ ዓማተግ አንድ ክፍል ሁኖ ወይም ሳይሆን) ከሌላ ፕሮጀክቱ ተገቢ ያልሆነ ኢንቬስትመንት ሰለመሆኑ የአደጋ ጠቋሚ ምልክት ሆኖ መታየት አለበት (ሳጥን 43ን ይመልከቱ)

ሳጥን 4፡-
የመሬት ይዞታ መብቶች
የአደጋ መንስኤዎች

**ከፍተኛ አደጋ**

- ሊፈቱ የማይችሉ በርካታ ቁጥር ያላቸው የቆዩ ወይም የቀርብ ግዜ መሬትን የሚለከቱ የመብት ጥያቄዎች ወይም ክርክሮች መኖር፤
- እንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ብዙ ግዜ ሊከሰት የሚችለው መሬት በመያዝ፣ በመቀላቀል ወይም ቀጣይነት ያለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሚያረግበት በ‘ብራውን ፊልድ’ ኢንቬስትመንት ነው (ይህም መሬት ለንግድ ጥቅም እየዋለ በማይገኝበት ወይም ለሎች የንግድ አላማዎች ጥቅም ላይ በሚውልበት ከ(ግሪን ፊልድ ኢቬስትመትን በተቃራኒ መልኩ ነው)።
- የአካብቢው ነዋሪዎች ከቦታቸው ላይ መፈናቀል፤ መንስኤውም መንግስት መሬቱን ቀደም ባለው ግዜ ወስዶት የነበረ ወይም ፕሮጀክቱ መሬቱን ለልማት ስራ አውለዋለሁ በሚል ምክንያት መሬቱን ያለ አግባብ በመውሰዱ ነው፤
- የፕሮጀክቱ ቀረፃ ነዋሪው ህዝብ የመሬት ባለይዞታነት መብቶቻቸውን ለሌሎች በስፋት አስተላልፈው እንዲሰጡ በመፈለጉ ሳቢያ ብዙ ሰዎች ያለፈቃዳቸው ወይም በፍቃደኝነት ወደ ሌላቦታ ተወስደው እንዲሰፍሩ ሊደረጉ ይችላሉ።
- ኦፕሬተሩ ወይም ዋናው ኢንቬስተር እራሱ ሳያከናውናቸው የቀሩና ወደፊትም የማያከናውናቸው ነገሮች ሲኖሩ፤
  - o አሳታፊ የሆነ ባለድርሻ አካላትን የመለየት ስራ ፤
  - o በመሬት ይዞታ መብት ላይ ሊደርስ የሚችል ተፅዕኖ ግምገማ (ምን አልባትም የተሟላ ዓማተግ አንድ ክፍል ተደርጎ)፣ ወይም
  - o ማህበረሰብ-አቀፍ የምክክር ሂደቶች ።

**መካከለኛ አደጋ**

- በፕሮጀክቱ የተያዘው መሬት በፕሮጀክቱ ቆይታ ወቅት ለምርት ስራ ያስፈልጋል ተብሎ ከሚገመተው መጠን በላይ ከሆነ፣ ፕሮጀክቱ ከሚገባ በላይ ትርፍ ለማጋበስ የታሰበ ነው የሚል ስጋት ያሳድራል።
- ፕሮጀክቱ ሊካሄድ በታሰበበት አካበቢ የመሬት መብቶች ያሏቸው ተመዝግበው ላይያዙ ስለሚችሉና ወይም የሚያገኙትም በልማዳዊ ሕግ ከሆነ እና ኦፕሬተሩ ሕጋዊ መብቶች ያሏቸውን ባለ ይዞታዎች የመለያ ስራ አሳታፊ በሆነ መልኩ ሳይሰራ ከቀረ፤
- ሊተገበር የታሰበው ፕሮጀክት በመሬት ይዞታ መብት፣ በፆታ፣ በምግብ ዋስትና እና በሰብዓዊ መብቶች ላይ ሊያሳድር የሚችላቸውን ተፅዕኖዎች ግምገማ በገለለተኛ ዓማተግ መካሄድ ይኖርበታል።
- በ ዓማተግ ምክረ ሀሳቦች መሰረት ፕሮጀክቱ ከተከለሰ በመሬት መብቶች፣ በምግብ ዋስትና፣ በፆታ፣ በስብአዊ መብቶች ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ ጎላ ያሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ግልፅ ማድረግ ይቻላል።

## 3. ጉዳትን ለማስወገድ ኘሮጀክቱን ማሻሻል

የተፅዕኖ ግምገማው በህጋዊ የመሬት መብቶች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ወይም መከሰታቸው አይቀሬ የሆኑ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ካሣየ፣ አሉታዊ ተፅዕኖዎቹን ለማስወገድ ኘሮጀክቱ እንደገና መከለስ ይኖርበታል (ምዕራፍ ስድስትን ይመልከቱ) ፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ኢንቬስተሩ በኢንቨስትመንቱ መግፋት አይኖርበትም፡ ፡ ይህም 'በህጋዊ የመሬት መብቶች ላይ ምንም ጉዳት አታድርስ እና እንዳይደርሱም ተከላከል፤ ከደረሱም ተገቢውን ምላሽ ስጥ' ከሚለው የመመሪያዎቹ ማሳሰቢያ አኳያ ነው (አንቀፅ 3.2 እና 12.4፤ እንደዚሁም ከመርሆዎቹ ቁጥር 10ን ይመልከቱ)፡፡

ኘሮጀክቱ ቀጣይነት የሚኖረው ከሆነ የተፅዕኖ ግምገማው አሉታዊ ተፅዕኖዎቹን ለማቃለል መወሠድ የሚገባቸውን የማቃለያ እርምጃዎች በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

- የመሬት ይዞታ መብቶች ካሏቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በሽርክና መስራት፣ ወይም በአነስተኛ መጠን አምራች ከሆኑት ጋር ውሎችን መፈፀም፤ የመሬት መብቶችን ለሌሎች ማስተላለፍን የማያስከትሉ አማራጭ የኢንቬስትመንት ሞዴሎችን መመርመር፤
- መሬትን በኪራይ በግልፅ መንገድ ሊያዝ የሚችልበት እና ቀደም ከነበረው የሚለይ የመሬት ማግኛ መንገድ በስራ ላይ ማዋል፡፡ ኪራዩ በጣም ለተራዘመ ግዜ የሚቆይ ከሆነ ወይም መሬቱ መጠን ሰፊ ከሆነ በኪራይ የሚያዙ መሬቶች እንኳን ሳይቀሩ ችግር ፈጣሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የአጭር ግዜ ቆይታ የሚኖራቸውን አማራጮችን ማጤን ያስፈልጋል፡፡በኪራይ መጠነ-ክፍያዎች እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ማድረግ የሚያስችሉ ውይይቶችን ማካሄድ እንዲቻል ከዋጋ ግሽበት መከሰት ጋር ተያይዘው ሊደረጉ የሚችሉ ተገቢ ማስተካከያዎችን ወይም በየግዜው ሊከሰቱ የሚችሉ አንቀፆችን ጭምር ማካተት ይኖርበታል፡፡
- እውን ሊደረጉ የሚችሉ ሌሎች አማራጮቹን በማሰላሰል በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሰዎችን በሌላ ቦታ የማስፈር ድርጊትን ማስወገድ፤ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሰፈራን ማስወገድ የማይቻል ከሆነ፣ ወደ ስፈራው ለማንቀሳቀስ ፈቃደኛ ለሚሆኑት ሚዛናዊ የሆነና ወድያውኑ ተከፋይ የሚሆን ክፍያ መስጠትን እንደዚሁም ግብአቶችና የተሻሉ የኑሮ ሁኔታዎች በዘላቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- በመሬት መብቶች ላይ የሚደርሰውን ተፅዕኖ ለማቃለል በኘሮጀክቱ ሊያዝ የሚችለውን የመሬት መጠን ማሣነስ ወይም ወሰንተኞችን መቀያየር፤ እንደዚሁም፣
- የማህበረሰቡ አካላት ሂወታቸውን ለዘለቄታው ማቆየት የሚያስችሏቸውን ጥቂት የእርሻ ቦታዎች እና ክልሎች ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ አማራጭ ሁኔታዎችን በአስተማማኝ ደረጃ በቀጣይነት ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ፡፡ ወደኋላ ላይ ይበልጥ ተብራርቶ እንደሚገኘው፣ ኢንቬስተሮች በምንም መልኩ ይሁን፣ የማካካሻ ክፍያ በመስጠትም እንኳ ቢሆን፣ የአካባቢውን ነዋሪዎች መፈናቀል የሚያስከትሉ ድርጊቶችን ከመፈፀም መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ እንደ አጠቃላይ ህግ፣ ኢንቬስተሮች የትናንሽ ባለይዞታዎችን እና ሌሎችን የአካባቢ ነዋሪዎችን የመሬት መብቶች ለሌሎች ማስተላለፍን የሚያስከትሉ የኘሮጀክት ሞዴሎችን ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡ (Oxfam Australia፡ 2006፡53)፤ ወይም ቢያንስ ቢያንስ እነዚያን መሰል የመብት ማስተላለፎች አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉበት እድል ማሣነስ አለባቸው፡፡ መመሪያዎቹ መንግሥታት የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ያበረታታሉ፡-
    - o በትናንሽ ባለይዞታዎች የሚደረጉ ኢንቬስትመንቶችና ባለትናንሽ ህዝባዊ ወይም ግላዊ ባለይዞታዎችን ላገናዘቡ ኢንቬስትመንቶች ድጋፍ መስጠት (አንቀፅ 12.2)
    - o የመሬት ይዞታ መብቶች በከፍተኛ ደረጃ ለኢንቨስተሮች መተላለፍን የሚያስከትሉ የተለያዩ የማምረቻና የኢንቬስትመንት ሞዴሎችን ማስተዋወቅ (አንቀፅ 12.6) ፤ እና
    - o የመሬት ይዞታ መብቶች ካሏቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ጋር አብሮ መስራትና ትብብርን ማጠናከር (አንቀፅ 12.6)

## የአጋርነት ስራዎች

ኦፕሬተሩ (ስራ አስኪያጅ) ከአካባቢው ገበሬዎች ጋር በሽርክና ሊሰራባቸው የሚችልባቸው ዘርፈ ብዙ መንገዶች አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንደኛው የእርሻ ቦታ በኮንትራት መውሰድ ሲሆን፣ ይህም አንዳንድ ግዜ 'አውት ግሮወር' ወይም የከንውኑ አንቀሳቃሽ ሞተር ተብሎ ይጠራል።በእንደዚህ አይነቱ የአሰራር ዘዴ ኦፕሬተሩ አብዛኛውን ግዜ ምርታቸውን በሚሸጡበት በባለ አነስተኛ ባለይዞታዎች መረብ የተከበበ አነስተኛ 'ማዕከላዊ' የእርሻ መሬት ይይዛል። ኦፕሬተሩም በአካባቢው ገበሬዎች ሙያዊ ድጋፍ፣ ግብአቶችንና ምናልባትም ብድር ሊሰጥ ይችላል (USAID፣ 2007 ዓ.ም፡39)።

እንደነዚህ ያሉ የሽርክና ስምምነቶችም እንኳን በአካባቢው ነዋሪዎች የመሬት ይዞታ መብቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖራቸው ይችላል ለምሣሌ ፕሮጀክቱ የትናንሽ እርሻዎች ባለይዞታ ገበሬዎች ዋጋ እንዲጨምሩ ሊያደርጋቸው ቢችልም፤ ምናልባትም ቁርስራሽ እርሻዎቹ የበለጠ ትርፋማ ሊሆኑ በመቻላቸው። ወይም በምግብ ሰብል ምርቶች ምትክ በሌሎች ለገበያ ተብለው በሚመረቱ ከፍተኛ ዋጋ በሚያወጡ ስብሎች በመተካታቸው ምክንያት ይሁን፣ ወንዶቹ ሴቶቹን ለብዙ አስርት አመታት በቁጥጥራቸው ስር የነበሩትን ብጥስጣሽ እርሻዎች ሊያስለቅቋቸው ይችላሉ። የዚህ ዓይነቱ ድርጊት የእነዚያን ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች ያላቸውን ሴቶች መብቶች ስለሚያሳንስ፣ በፊቱንም መሬት የማግኘት ዋስትና ያልነበራቸውን በተለይም ሴቶችን እና የተገለሉ ክፍሎች፤ የመሬት ዋጋ እየጨመረ ሲሄድ መሬት የማግኘት እድላቸው አናሳ መሆኑ ስለማይቀር በሽርክና የመስራት ዘይቤ ውስጥ የሴቶች መብቶች ጥበቃ ሊያገኙ የሚችሉባቸውን መንገዶች ማካተት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን እነዚህ የአሰራር ዘዴዎች ሚዛናዊና ግልፅነት ባላቸው ተገቢ ድርድሮችና ውሎች ላይ መመስረት ይኖርባቸዋል። ኃላፊነት የተላበሱ 'Out grower' አሰራሮች ላይ እንደዚህ ያሉ ስምምነቶችን የማድረግ ሀሳብ ያላቸው ካሉ ኃላፊነት የተላበሱ 'Out grower'አሰራሮችን በተመለከተ የተፃፉ በርካታ ምክር አዘል ፅሁፎች ስለሚገኙ እነሱን መመልከት ጠቃሚ ይሆናል (ምግድ፣ 2004 ዓ.ም ሀ)[8]

የመሬት ይዞታ መብቶች ያሏቸውን የአካባቢውን ነዋሪዎች በፕሮጀክት ውስጥ የማሣተፊያ ሌላኛው መንገድ በፕሮጀክቱ ውስጥ የአክሲዮን ድርሻ በመስጠት ነው። የመሬት መብቶች ባለቤቶች የሆኑቱ ከመሬት ላይ በፊት ያገኙ የነበረውን ገቢ ወይም ምርት ሊተኩ የሚችሉበት የገቢ ምንጭ ሊያስፈልጋቸው ስለሚችል፤ የድርሻዎች ፍትሀዊነት መታየት የሚኖርበት ለመሬቱ ግዥ ወይም በኪራይ መልክ ከተከፈለው ዋጋ በተጨማሪነት ነው። ፕሮጀክቱ ስኬታማ ሊሆን ካለመቻሉ እና ስራ ማይኖርበት ወይም በፕሮጀክት ማጣሪያ ሂደት ላይ መሬቱ ለአካባቢው ነዋሪዎች በሚጠቅም መንገድ ሊውል ስለመቻሉ ምንም ዋስትና ሊኖር ስለማይችል እንደ 'መሬት ለአክሲዮን ድርሻ' ባሉት ሞዴሎች ላይ የተመሰረቱ የአክሲዮን ድርሻ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ስምምነቶች አደጋን ያዘሉ ናቸው። ስኬታማ የሆኑ ፕሮጀክቶችም እንኳን ቢሆኑ ከኢንቬስትመንት ላይ ተጨባጭ ውጤት ማስገኘት የሚችሉት ከብዙ አመታት በኋላ ነው።፣ የመብት ባለበቶች ከሆኑት የአካባቢ ነዋሪዎች ውስጥ አብላጫዎቹ ደግሞ ለዚያን ያህል ግዜ ያለምላሽ በትእግስት መጠበቅ ስለማይችሉ፣ ከፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ አንስቶ የገቢ ምንጭ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል።

ፕሮጀክቱ የሚያዘውን የመሬት መጠን ማሳነስ እንደዚሁ ተገቢ ሊሆን ይችላል። ኢንቬስተሮቹ ለፕሮጀክቱ የተመደበውን መሬት ሙሉ በሙሉ ሳይጠቀሙ በመቅረታቸው ምክንያት ግጭት ስለመፈጠሩ አብነት ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ። ለምሣሌ በ2006 ዓ.ም በ ተመንልኑ የተደረገ ጥናት፣ በጥናቱ ከተካተቱ ናሙናዎች በ ¼ ውስጥ ኦፕሬተሮቹ የተጠቀሙት ከተመደበው መሬት ውስጥ በ10% ያነሰ ነበር። ለዚህ ውጤት መገኘት መንስኤ ከሆኑት የተለያዩ ምክንያቶች ውስጥ የፕሮጀክቱ መጠን እና እድሜ፣ በቂ ያልሆነ የገንዘብ ምደባ ወይም ተገቢ ያልሆነ የፕሮጀክት ግምገማና እቅድ ተጠቃሾች ናቸው። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ መሬት ከተፈላጊው ውጤት በአመዛኙ አሉታዊ ነው (ሚርዛና ሌሎች 2006 ዓ.ም፡36-38)። ይህ መሆኑ ደግሞ 'መሬቱ የተያዘው ለግምታዊ አላማዎች ነውን?' የሚያስኝ ጥርጣሬ ያሳድራል። አንዳንድ ገንዘብ አቅራቢዎች፣ ዓፋድን ጨምሮ፣ ውጤታማ ለማይሆኑ በመላምት ላይ ለተመሰረቱ ኢንቬስትመንቶች ገንዘብ አያቀርቡም (ዓፋድን ፣ 2006 ዓ.ም)። የዚህ ዓይነቱ ችግር ሊወገድ ወይም ሊቃለል የሚችለው በፕሮጀክት እቅድ አወጣጥ

[8] የተባበሩት መንግስታት ንግድና ልማት ጉባኤ፤ የተባበሩት መንግስታት የምግብና የግብርና ድርጅት ዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ድጋፍ ድርት 2015 ህጋዊ የኮንትራት እርሻ ።

የሚሣተፉት ሰዎች፣ የመሬቱ መጠን አግባብነት ያለው መሆኑን /አለመሆኑን እና የዚህ አይነተ ትንተና መደረግ ያለበት በቅድመ ግምገማ ደረጃ ወይም ወደ ትግበራ ከመገባቱ በጣም ቀደም ብሎ ስለመሆኑ ለመወሰን የሚያበቃ ችሎታና አካባቢ-ነክ እውቀት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ነው፡፡

ኢንቬስተሮች የኦፕሬተሩን የስራ እቅዶች እና ፕሮጀክቱን የመተግበር ችሎታ ያለው ስለመሆኑ እና በመጀመሪያው የእርሻ ቦታ የማልማት ስሌት ላይ በመመራት፣ ያለምንም ማመንታት መገምገም ይኖርባታል (ሚርዛና ሌሎች 2006 ዓ.ም፡38)፡፡

የመሬት መብቶች በፍቃደኝነት ሊተላለፉ በሚችሉባቸው ቦታዎች (በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ተዳሶ እንደሚገኘው) ኢንቬስተሮች የመሬት ባለቤትነት መብቶች ያላቸው ባለይዞታዎች ሚዛናዊና ወድያውኑ ተፈፃሚነት የሚኖረው ክፍያ እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው፡፡ ለመብቶች እውቅና የመስጠት ሂደት ክፍያ ማግኘት የሚገባቸውን ክፍሎች ማወያየት ይኖርበታል፡፡ በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ መካተት የሚገባቸው ህጋዊ የመብት ባለቤቶች ብቻ ሳይሆኑ በመብቶቻቸው ላይ ተፅዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ፡- መደበኛም ሆነ ኢ-መደበኛ መብቶች ያላቸው በሙሉ መሆን ይኖርባቸዋል(USAID 2007 ዓ.ም ለ፡36-37፣42)፡፡

## ግምትና ዋጋ አሰጣጥ

አነስተኛ ገቢ ያላቸው በሚገኙባቸው በበርካታ ገጠርማ የአገሪቱ አካባቢዎች የመሬት ዋጋን መተመን በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘው ዘዴ መሬቱ በገበያ ላይ ሊኖረው የሚችለውን ሚዛናዊ ዋጋ በመወሰን ነው፡፡ ይህም ብዙ ግዜ የሚተረጎመው አንድ ፈቃደኛ ገዢ ፈቃደኛ ለሆነ ሻጭ የሚከፈለው ዋጋ ተደርጎ ነው፡፡ የመሬት ግብይይቶች በትክክል ተመዝግበው በማይያዙበት እና ቀልጣፋና ግልፅ የሆነ የመሬት ገበያ በሌለበት ሁኔታ መሬቱን በገበያ ላይ የሚኖረውን ዋጋ መገመት በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል ማለቱ ከዚህ መምሪያ አላማ አኳያ በቂ ይሆናል፡፡ ሁሉም ወገኖች ማለትም፡- ኢንቬስተሮች፣ ኦፕሬተሮች ማህበረሰቦች እና መንግስት፣ የገጠር መሬትን ሚዛናዊ የገበያ ዋጋን ማስላት አዳጋች ሁኖ ሊያኙት ይችላሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ኦፕሬተሮች በመንግስት ወይም በማህበረሰቦች የሚጠየቁ በጣም ዝቅተኛ የመሰሉ ዋጋዎችን ብዙ ግዜ በጥንቃቄ መመልከት ይኖርባቸዋል፡፡ ዝቅተኛ ዋጋ፣ በተለይም ከጥቅል ችሮታ ወይም የታክስ ምህረት ጋር የተገናኘ ከሆነ በፕሮጀክቱ ጅምር ላይ ማራኪ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ያንን መቀበል አደገኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም መሬታቸውን የሸጡት ወይም ያከራዩት እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ መሆንን ሲገነዘቡ ማህበረሰቡ ወይም መንግስት ኋላ ላይ ችግሮች ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይም አሳሳቢ የሚሆነው መሬቱ የተሸጠው እና መንግስታትም ከዚህ አይነቱ አሰራር መቀጠብ ያለባቸው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በመደበኛነት በበቂ ሁኔታ ክለሳ ማድረግ የሚቻል ስለመሆኑ በስምምነቶች ውስጥ ሳይካተት ከቀረ፡፡ መሬትን በኪራይ መስጠት ላይ ከፍተኛ የችግር መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡[9]

በብሔራዊው ህግ መሰረት (ለምሣሌ ንብረት ማስለቀቅን በሚማለከተው ህግ) መንግስት እንዲከፍል በሚጠበቅበት ክፍያ ብቻ ተጎጂ የሚሆኑ ወገኖች በሙሉ ሚዛናዊና በቂ ክፍያ ማግኘት መቻላቸው አጠራጣሪ ነው (ቀጥሎ ያለውን ይመለከቱ)፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው ሁሉ፣ ህጉ ለልማዳዊ የመሬት ይዞታ መብቶች እውቅና ላይሰጥ ወይም ለወቅታዊ ተጠቃሚዎች ተደራራቢ መብቶች ላላቸው ሌሎች ባለይዞታዎች ክፍያ ላይፈቀድ ይችላል፡፡ በተጨማሪም፣ ሴቶች በመሬት ላይ መጠቀም ይችሉ እንደሁ እንጂ የመሬት ይዞታ መብቶች ስለማይኖራቸው የሚሰጣቸው ክፍያ ብዙውን ግዜ ወይ አነስተኛ ነው፣ አልያም ምንም ክፍያ አያገኙም፡፡ ለምሣሌ፡ ሴቶች የግንባታ ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶችን በተለምዶ ያገኙበት የነበረው በደን የተሸፈነ አካባቢ በኢንቬስትመንት ፕሮጀክት ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡ በዚሁ መንስኤ ታድያ ሴቶቹ እንደነዚያ ያሉ የደን ውጤቶችን የማግኘት እድል ስለማይኖራቸው በቂ ክፍያ ማግኘት ይችሉ ዘንድ ኢንቬስተሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡[10]

---

[9] በርካታ ጥናቶች የሚያረጋግጡት የገንዘብ ካሳን በቀላሉ ወንዶች፤ በአካባቢ ታዋቂ ሰዎች ይበልጥ ተጠቃሚ ናቸው፤

[10] በርካታ ተነባባ ሰነዶች በመሬት ዋጋ ግምት ላይ ይገኛሉ፤ ቱና 2012

## የመሬት ማስለቀቅ

በመሬት ይዞታ መብቶች ላይ ምናልባትም በጣም አስከፊ የሆነ ተፅዕኖ ሊደርስ የሚችለው መብቶቹ ያላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች በመሬታቸው ላይ በግዳጅ ሊፈናቀሉ ከቻሉ ነው፡፡ የመፈናቀል ክስተት ብዙ ግዜ የሚፈጠረው መንግስት አለኝ የሚለውን የመሬት ባለቤትነት መብትን ወይም ያለውን ስልጣን በመጠቀም መሬት አስለቅቆ ለሆነ የህዝብ አገልግሎት ወይም ጥቅም ሲያውል ነው፡፡

በጥሬ ትርጉሙ፣ 'ማስለቀቅ' ማለት መንግስት ተጎጂ የሚሆኑትን ሰዎች ፈቃድ አላገኘም ማለት ነው፡፡ በተለይም እነዚያ የተፈናቀሉት ሰዎች በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት በነፃነት ፍቃድ የመስጠት ወይም የመንፈግ መብት አላቸው የሚባሉት ነባር ህዝቦች ከሆነ ጉዳዩን አስቸጋሪ ያደርገዋል (ነቅዕፈ) (ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ)፡፡ ከዓፋድ የአፈፃፀም መስፈርቶች ውስጥ አንደኛው ዓላማ በግዳጅ የሚደረግ መፈናቀልን ማስወገድ ነው፤ ምክንያቱም በሚፈናቀሉት ሰዎቹ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሊደርሱ የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ በመሆኑ ነው (ዓገድ፣2004 ዓ.ም መስፈርት 5)፡፡ በአጠቃላይ መመሪያዎቹ መሬት ማስለቀቅን በግልፅ አይከለክሉም፡፡ እነዚህን መመሪያዎች የሚከተሉ መንግስታት 'ለሕዝባዊ አላማ' የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ትርጉም በመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ በሚፈቅድ መልኩ በግልጽ ማስቀመጥ አለባቸው (አንቀፅ 16.1)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች ያሏቸውን በሙሉ፣ በተለይም ለአደጋ ተጋለጭ የሆኑትን እና የተገለሉ ክፍሎችን፣ መብቶች ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሊደረግ የሚችለው አግባብነት ባለው የብሔራዊው ህግ መሰረት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን እንዲያገኙ እና ወድያውኑ ተፈፃሚ የሚሆን የካሳ ክፍያ በመስጠት ነው (አንቀፅ 16.1)፡፡ ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶቻቸው ህጋዊ ለሆነ ለህዝብ አላማ ሲባል የተወሰዱባቸው ሰዎች ብሄራዊ ህግን ያገናዘበ ሚዛናዊ የሆነ የዋጋ ተመን እና ወድያውኑ ተፈፃሚነት የሚኖረው የካሳ ክፍያ መንግስታት መስጠት እንዳለባቸው መመሪያዎቹ ይመክራሉ (አንቀፅ 16.3)፡፡

ይሁን እንጂ ሰዎች ከቦታ የመፈናቀል በብሄራዊ ሕግ መሰረት ህጋዊነት ሊኖረው የሚችል ቢሆን እንኳን፣ የአደጋ መጠንን ለመቀነስ የሚፈልጉ ኃላፊነት የተላበሱ ኢንቬስተሮች የሰዎች መፈናቀልን እና ያለ ፍቃደኝነት የሚካሄድ ሰፈራን የሚያስከትሉ ፕሮጀክቶችን ማስወገድ ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳንድ ኢንቨስተሮች፣ ለምሣሌ እንደ የአፍሪካ የግብርና ንግድ እና የኢንቬስትመንት ፈንድ (አግንኢፈ) ያሉቱ፣ የዚያን አይነት ፖሊሲ እንዳለ ተቀብለውታል፡፡ በእርግጥ አደጋን የማቃለል አንደኛው ጠቃሚ ስልት በምንም መልኩ ቢሆን ሰፈራን ማስወገድ ነው፡፡ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሰፈራም እንኳ ለብዙ ችግሮች የሚያዳርግ እና ወደ ሰፈራ እንዲንቀሳቀሱ ለሚገደዱት ሰዎች አጥጋቢ በሆነ መልኩ ማካሄድ አዳጋች ነው (ሚርዛና ሌሎች 2006 ዓ.ም 39-40)፡፡

ምንም እንኳ ኢንቬስተሮች መሬት በመንግስት እንዲወሰድ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ማስወገድ ያለባቸው ቢሆንም፣ መብቶቻቸውን ለኢንቬስተር ወይም ኦፕሬተር ለማስተላለፍ ስምምነት ላይ ከደረሱ የሙብት ባለቤቶች ጋር በሚያደርጓቸው ድርድሮች ላይ ይህንን የዋስትና ክፍያ መስፈርት መጠቀም ይችላሉ፡፡ በበዙ ሁኔታዎች ተጐጂነትን ለማስወገድ መብቶችን ከማስተላለፍ ጋር የሚደረጉ ክፍያዎች በጥሬ ገንዘብ መልክ ብቻ ከሚሰጡት ክፍያ በላይ መሆን አለባቸው፡፡ ለምሣሌ፡- መሬት የመስጠትና በገንዘብ መልክ ያልሆኑ ሌሎች ክፍያዎች በማራጭነት እንዲኖሩ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም 'ሚዛናዊ ክፍያ'ለመሬቱ ተገቢ ከሚሆነው ዋጋ በላይ ይሄዳል፤ እንደዚሁም በአካባቢና በማህበረሰብ ላይ የሚደርስ ተጎጂነትን እና ሌሎች ጉዳቶችን ማለትም የሰፈራ ወጪን እና የአዲስ ቤት ግንባታን፣ እና በስራ ወይም በገቢ ምንጮች ላይ የሚፈጠሩ ለውጦችን ጭምር ማጠቃለል አለበት (ምግድ፣ 2000 ዓ.ም)፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ሁኔታ የተለየ በመሆኑ ለሁሉም የሚስማማ አንድ ወጥ የሆነ አሰራር ሊኖር አይችልም፡፡ መብቶቻቸውን ለማስተላለፍ በተደረጉ ስምምነቶች መሰረት ክፍያ የተሰጣቸው ወይም የካሳ ክፍያ ተሰጥቷቸው ይዞታቸው እንዲለቁ የተደረጉ ሰዎች ያሉበት ሁኔታ ከፕሮጀክቱ በፊት ከነበሩበት ሁኔታ የባሰ መጥፎ መሆን የለበትም እናም አሁን የሚገኙበት ሁኔታ በተጨባጭ የተሻለ ሆኖ መገኘት አለበት፡፡

## የመሬት የኋላ ታሪክ የሚመለከቱ ጉዳዮች

ለፕሮጀክቱ በተፈለገው መሬት መንስኤነት የአካባቢው ነዋሪዎች ያለ ይሁንታቸው ከረጅም ግዜ በፊት ምናልባትም ከብዙ አመታት በፊት-ኢንቬስተሮቹን ለየት ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ፡፡

ለምሣሌ፣ መሬቱ በመንግስት በመወሰዱ ምክንያት ሰዎች በግድ ለቀው እንዲሄዱ ተደርገው ይሆናል፡፡ ሰዎቹም በቂ የሆነ የካሳ ክፍያ አግኝተው ወይም ሣያገኙ ቀርተው ይሆናል፡፡ ያመሬት ደግሞ ከጥቂት አመታት በኋላ ለሶስተኛ ወገን ተላልፎ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዛ በኋላ፣ በኢንቬስተሩ ጥያቄ መሰረት ለፕሮጀክቱ ተሰጥቶ ይሆናል፡፡ ስለዚህ መሬቱ በመጀመሪያ በመንግስት በመወሰዱ ሳቢያ የተነሱና በዚያው የቀጠለ ቅሬታዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

እንደዚያ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም አንድ ኢንቬስተር ምን ማድረግ አለበት? እንደዚያ ያሉ ሁኔታዎች ሲኖሩ፣ ኢንቬስተሮች የታሰበው ኢንቬስትመንት ለመተግበር ያለው እድል ምን ያህል እንደሚሆን እንደገና በከፍተኛ ደረጃ ማሰላሰል ይኖርባቸዋል (ዘዘዘአስ፣ 2005 ዓ.ም፡- መርህ 2.3)፡፡ ፕሮጀክቱ ሊጋፈጥ የማይችል የማህበራዊ ተቀባይነት እጦት ሊጋጥመው ስለሚችል በኢንቬስመንቱ አለመግፋት ተመራጭ ሊሆን ይችላል (AFD 2006 ዓ.ም፡37)፡፡ ኢንቬስተሩ በተቻለው አቅም ሁሉ ኦንሬተሩ ካሣ የመስጠት እርምጃ እንዲወስድ መገፋፋት ይኖርበታል፡፡ያለበለዚያ ደግሞ ኢንቬስትመንቱን ለሚካሄድ እየተነሱ ያሉ ቅሬታዎች መፈታትን እንደ ቅድመ ሁኔታ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ኢንቬስተሮች ሻጩ/አከራዩ (መንግስት ወይም በመንግስት መሬቱ የተላለፈለት ወገን) በመጀመሪያ ደረጃ መሬቱን እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ግልፅ በመሆን መጀመር ይኖርበታል፡፡

መብቶችን ለይቶ ማወቅ፣ ተፅዕኖዎችን መገምገም እና የማቃለያ እርምጃዎችን መውሰድ ፕሮጀክቱ ከሚተገበርባቸው ማህበረተሰቦች ጋር ከሚደርግ ተገቢ ምክክር ጐን ለጐን የሚካሄድ ነው፡፡ የሚቀጥለው ምዕራፍ እርእስም ይኸው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

ሣጥን 5፡-
የመሬት ባለይዞታነትና መብቶች
አደጋ የመቆጣጠር ዝርዝር

የግብርና ኢንቬስትመንቶች ለሁሉም ተጎጂ ወገኖች ጥቅም ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ኢንቬስትመንቶች ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች ያሏቸውን ሊጐዱ የሚችሉበት አደጋ ሁሌም አለ፡፡ በጣም ጫፍ የሚደርሱ ሁኔታዎች በገንዘብ የሚደርሰው ጉዳት በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ዶላሮች ሊደርስ ይችላል፡፡ ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች፣ ተመዝግበው የተያዙ መደበኛ መብቶችና ብዙ ጊዜ ተመዝግበው የማይያዙ ኢ-መደበኛ መብቶችን ሁለቱንም ይይዛሉ፡ ህጋዊ የመሬት ባለይዞታዎች የሚባለው ምድብ ብዙ ግዜ ወቅታዊ ወይም ተደራራቢ መብቶች ያሏቸውን ሰዎች፣ እንደ አርብቶ አደሮች ያሉትን ጭምር ያካትታል፡፡ በተለይም ለሴቶች መብቶች ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡

- ✓ በፕሮጀክት ቀረፃ ምዕራፍ ላይ፣ የትናንሽ ባለይዞታዎችንና የሌሎቹን የአካባቢ ነዋሪዎች የመሬት ባለይዞታነት መብቶች መተላለፍን የሚያስከትሉ የፕሮጀክት ሞዴሎችን አጢኖ፣ ወይም ቢያንስ ቢያንስ እነዚያን መተላለፎች አስፈላጊ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችን አሳንስ፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን፣ ማስለቀቅንና ማፈናቀልን የግድ የሚሉ ፕሮጀክቶችን አስወግድ፡፡ አንድ ጠቃሚ የሆነ አደጋን የማቃለያ ስልት ማንኛውንም የሰፈራ እንቅስቃሴን፣ በፈቃደኝነትም ይሁን ያለፈቃደኝነት የማደረግን፣ ማስወገድ ነው፡፡
- ✓ የመሬት ይዞታ ባለመብቶችን በሙሉ መለየትና ማወቅ፡-
  - o ከመሬት ጋር ስለሚያያዙ ብሔራዊና አካባቢያዊ ልማዶች ባለሙያዎችን በማነጋገር መረዳት፤
  - o ከመንግስት ባለስልጣኖት ጋር መገናኘትና መሬትን የሚመለከቱ የመንግስት ሰነዶችን መቃኘት፤
  - o ከማህበረሰቡ ጋር የሴቶች፣ ወጣቶችና ለአደጋ-ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎች ተወካዩች መኖራቸውን በማረጋገጥ፣ በጣም ቀደም ብሎ ምክክሮችን መጀመር (ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ) ፤ እና
  - o በአካባቢው ያሉ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መብቶች ያሏቸውና ተጠቃሚዎች በሙሉ ለይቶ ለማውጣት ማህበረሰቡ እገዛ የሚያደርግበት አሣታፊ የሆነ የመለያ ስራ ማካሄድ፤
- ✓ በተገቢ የዝግጅት ሂደት ምዕራፍ ላይ፣ ፕሮጀክቱ በመሬት ይዞታ መብቶች ላይ ሊኖሩት ይችላሉ ተብለው በአሣታፊ የመለያ ስራ የተለዩ ተፅዕኖዎችንና በአካባቢው በፆታ፣ በምግብ ዋስትና እና በሰብአዊ መብቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን ለመለየት ገለልተኛ የሆነ የአማተግ እንዲካሄድ ማድረግ ወይም እንዲደረግ መጠየቅ (ምዕራፍ 6ን ይመልከቱ)፡፡ እንደዚሁም አሉታዊ ተፅዕኖዎቹ ሊቃለሉ የሚችሉበትን መንገድ መጠቀም አለበት፡፡
- ✓ የአማተግ በተጨባጭ የደረሱ ወይም ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን ከጠቆመ፣ ተፅዕኖዎቹን ለማስወገድ እንዲረዳ ፕሮጀክቱን-እንደገና መቅረፅ ያስፈልጋል፡፡ በአካባቢው ሁኔታ ላይ በመመስረት ለፕሮጀክቱ ከለሣ ተስማሚ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ መንገዶች፤ የሚከተሉት ጭምር አሉ፡-
  - o መጠነ ሰፊ የመሬት ይዞታ መብቶች መተላለፍን የማያስከትሉ፣ ከአካባቢው የመሬት ይዞታ መብቶች ጋር በሽርክና መሰራት ወይም ከአነስተኛ ደረጃ አምራቾች ጋር ውል በመፈፀም መስራት የሚያስችሉ፣ አማራጭ ኢንቬስትመንት ሞዴሎችን መመርመርና መጠቀም፤
  - o መሬት የሚያዝበት የተለየ የኪራይ አሰራር፣ ተገቢ በሆነ ስምምነትና በቅድመ-ሁኔታዎች የሚቀመጡበት ያሉትን፣ መሬት ወዲያውኑ ሙሉ ለሙሉ በማስተላለፍ ምትክ ኪራይ በየጊዜው የሚከለስበት ወይም ለአጭር ጊዜ በሚቆይ የኪራይ ውል አሰራርን መጠቀም፤

- o በፕሮጀክት ሊያዝ የሚችለውን የመሬት መጠን መቀነስና/ወይም ተፅዕኖን ለመቀነስ አዋሣኞችን ማስተካከል፤ እና
- o የማህበረሰቡ አካላት ቢያንስ ቢያንስ ለህይወታቸው ማቆያ መሬቱን ለእርሻ መጠቀም እንዲቀጥሉ መፍቀድ፣

✓ በአካባቢው የመሬት ባለይዞታነት መብቶች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን ማስወገድ የማይቻል መሆኑ ከተረጋገጠ በኢንቬስትመንቱ አለመግፋት፡፡

# 3

# ምክክር፣ ተሳትፎ እና ድርድር

## የወካይ ምልክቶች አጠቃቀም

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

በርካታ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች መኖር ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በኢንቬስትመንቱ መግፋት እንደሌለበት ሊያነሳሰው ይገባል፡፡

### መካከለኛ የአደጋ መንስኤዎች

ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በተገቢ ዝግጅት ምዕራፍ ላይ ፕሮጀክቱን በድጋሚ በመፈተሽና አደጋዎችን የማቃለያ መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# 3. ምክክር፣ተሳትፎና ድርድር

## ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

መመሪያዎቹ በታሰበው ኢንቬስትመንት ሳብያ ሊጐዱ ከሚችሉ ወገኖች በሙሉ ጋር መጠነ ሰፊ እና ሁሉን አቀፍ የሆነ ምክክር ማድረግን ያበረታታሉ፡፡ በዚህ ረገድ 'ምክክር እና ተሳትፎ' በሚከተለው መልኩ ትርጉም ተሰጥቶዋቸዋል፡-

"ውሳኔዎች ከመሰጠታቸውና ለአስተዋፅኦቸው ምላሽ ከመስጠቱ በፊት፣ ተያያዥነት ባላቸው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ በተለያዩ ወገኖች መካከል ያለውን ስልጣን የአለመመጣጠንና ንቁ፣ ነፃ፣ ስኬታማ፣ ትርጉም ያለው እና በእውቀት ላይ የተመሰረቱ የግለሰቦችና ቡድኖችን ተሣትፎ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ህጋዊ የመሬት ባለይዞታነት መብቶች እያላቸው በውሣኔዎች ተጐጅ መሆን ከሚችሉ ወገኖች ጋር መነጋገርና ድጋፋቸውን ማግኘት ያስፈልጋል፡፡"

መመሪያዎቹ መንግስታትና ሌሎች ክፍሎች (ኢንቬስተሮች ጭምር ከሁሉም ባለ ድርሻ አካላት፣ ማለትም ነባር ህዝቦች እና ሌሎች ልማዳዊ የመሬት ስርዓቶች ካሏቸው ሌሎች ማህበረሰቦች፣ አነስተኛ ይዞታ ካላቸው እና ተጎጂ ልሆኑ ከሚችሉ ማናቸውም ቡድኖች ጭምር ጋር በአግባቡ እንዲመካከሩ ይገፋፋሉ (አንቀፅ 7.3)፡፡[11] ነባር ህዝቦች ልዩ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይኸውም የመሬት ባለቤትነት መብቶቻቸውን የሚነኩ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶች በእንቅስቃሴያቸው መግፋት ከመቻላቸው በፊት 'ነ ቅ ዕ ፈ' ያቻውን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው (አንቀፅ 9.9)፡፡ ሌሎች ማህበረሰቦችን የመመካከር እና የመሳተፍ መብት ይኖራቸዋል(አንቀፅ 12.7)፡፡

## ለ. አደጋው ምንድነው?

በቂ ምክክር እና የተሳትፎ ሂደቶችን የማያካትቱ ኘሮጀክቶች፣ ያንን ከሚያደርጉት በበለጠ፣ በጣም ከፍተኛ ወጪዎችን ከራሣቸው ላይ ማምጣታቸው አይቀሬ ሊሆን ይችል (የመንዴን ኘሮጀክት፣ 2006 ዓ.ም)፡፡ የዚህም መንስኤ ተገቢ ምክክር ማድረግ በህጋዊ የመሬት መብቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከማወቂያና የማስወገጃ ሂደት ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ ነው፡፡ አስቀድሞ (በምዕራፍ 6 ውስጥ) እንደተብራራው ሁሉ፣ በምግብ ዋስትና፣ በአካባቢ እና በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚደርስ ጉዳትን ከማስወገድ ጋርም የሚገናኝ ነው፡፡

የሚከተሉትን ነገሮች ያለበቂ የምክክር፣ የተሳትፎ እና የድርድር ሂደት ማድረግ የሚቻል ቢሆን እንኳ፣ አስቸጋሪ መሆኑ ግን አያጠራጥርም፣ ይኸውም፡-

- ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶችን፣ በተለይም ልማዳዊ መብቶችን በትክክል መለየት እና እውቅና መስጠት፤

[11] የመመሪያው አንቀጽ 8.6 ለምክክር ሁሉም ተጎጅዎች መገኘት እንዳለባቸው ፤አንቀጽ 9.9 ደግሞ ከነባር የህብረተሰቡ ነዋሪዎች እና ከሌሎችም ነዋሪዎች ጋር በባህላዊ የይዞታ ስሪት ላይ ምክክር እንደሚያስፈልግ፤ይደነግጋል፡፡

- ሊካሄድ የታሰበው ኢንቬስትመንት በመሬት ይዞታ መብቶች፣ በምግብ ዋስትና፣ በሰብዓዊ መብቶች እና በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችላቸውን ተፅዕኖዎች በተሟላ መልኩ እና በትክክል መገምገም፤
- የመሬት መብቶችን ለማስተላለፍ በሚደርስ በማንኛም ስምምነት ላይ ሁሉም የህጋዊ መብቶች ባለቤቶች ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆነ እና ፈቃደኛ ስለመሆኑናቸው፤
- በኘሮጀክቱ መላ የቆይታ ግዜ ከህብረተሰቡ ጋር ውጤታማ ለሆነ እና ቀጣይነት ላለው ግነኙነት በቂ መሰረት መጣሉን (USAID 2007 ዓ.ም ለ፡13-14)

ስምምነታቸውን ባለመጠየቃቸው ቅሬታ የገባቸው ሰዎች/ክፍሎች በተቃውሞዎች ወይም በሌሎች መንገዶች የኘሮጀክቱ እንቅስቃሴ እንዲዘገይ ወይም እንዲገታ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ጠንካራ በሆነ የምክክር ሂደት ላይ ኢንቬስት ማድረግ፣ ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ መሆኑ ሳይዘነጋ፣ እንደዚያ መደረጉ ግን ከገንዘብ አንፃር ትርጉም የሚሰጥ ነው፡፡ አንደዛ ያሉ ወጪዎች ተገቢ የሆነ የዝግጅት ትንተና አካል ተደርገው መታየት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምክክር ሂደት የሚደረገው ወጪ ተጎጂ ከሆኑ ሰዎች ጋር በሚገባ በመነጋገር ሊወገዱ ይችሉ በነበሩ ከመሬት መብቶች ጋር ተያይዘው በሚፈጠሩ ግጭቶች ሳብያ የሚከሰቱ የኘሮጀክት መጓተቶች ምክንያት ሊያገጥሙ ከሚችሉ ወጪዎች እጅጉን ያነሰ ነው (USAID 2007 ዓ.ም ለ፡22፣27)፡፡ እንደዚሁም ሁሉ የዘለቄታዊነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በሆነ መልኩ የሚያስፈልጋቸው ኘሮጀክቶች ኢንቬስትመንት በሚደረግበት ግዜ ውስጥ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር ተገቢ ምክክር ሳያደርጉ ከቀሩ ማረጋገጫውን ማግኘት መቻላቸው አጠራጣሪ ይሆናል(ዘዘዘማ0ስ፣ 2005 ዓ.ም፡- መርህ 1-1፣2-3፣ 6.3፤ ባዘማአስ፣ 2005 ዓ.ም፡- መስፈርት 2ለ)

ሣጥን 6 ፡-
የምክክርና ድርድር
የአደጋ መንስኤዎች

**ከፍተኛ አደጋ**

- ኦፕሬተሩ በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ ተጐጂ ወገኖች ጋር ባህላዊ ተገቢነት ያለው፣ ሁሉን አሣታፊ የሆነ የምክከር ሂደት አላካሄደም፡፡
- ነባር ማህበረሰቦች ነፃ፣ ቅድመ፣ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃዳቸውን (ነቅእፈ) አልሰጡም፡፡

**መካከለኛ አደጋ**

- በኘሮጀክት የእቅድ ምዕራፍ ላይ የአካባቢ ማህበረሰብ ተሣትፎ አላደረገም፡፡
- ተጐጂ ወገኖች ስኬታማ ስነ-ባህላዊ ተገቢነትና ግልፀኝነት ባለው የምክክር ሂደት ውስጥ ገና ተሣታፊ አልሆኑም፡፡
- ኘሮጀክቱን የሚመለከት አስፈላጊ የሆነ መረጃ በሙሉ በምክክር ላይ ገና ግልፅ አልተደረገም፡፡
- መደበኛና ኢ-መደበኛ የመሬት ይዞታ መብቶች የሚተላለፉበትን አግባብ) አስመልክቶ በፅሁፍ የተያዘ የተሟላ ስምምነት ላይ ገና አልተደረሰም፡፡
- ነባር ማህበረሰቦች ኘሮጀክቱ በሚካሄድበት ቦታ ላይ ወይም በአቅራቢያዊ ይኖራሉ፡፡
- ፈቃድ የተገኘው ከልማዳዊ አመራሮች ብቻ ነው፡፡

## ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

ስኬታማ የምክክር እና የድርድር ሂደት ማካሄድ የሚቻለው እንዴት ነው? ከመመሪያዎቹ አኳያ ታድያ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው መሰረታዊ የሆኑ ዘዴዎች ከዚህ በታች ተገልጿል፡-

1. በማህበረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ተጎጂ የሚሆኑ ወገኖች በሙሉ ስለፕሮጀክቱ በበቂ መጠን ማወቅ እና ፍላጐቶቻቸውንም ለማንፀባረቅ እድሉን ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡
2. ሂደቱ ተጎጂ የሚሆኑ ወገኖች በሙሉ ትርጐም ባለው መልኩ ማካተት አለበት፡፡
3. የተደረገው ስምምነት በሁሉም ወይም ቢያንስ በአብላጫዎቹ ተጎጂ ወገኖች መደገፍ አለበት፡፡ (ምርጥ የሚባለው ፕሮጀክትም እንኳን የተወሰነ ተቃውሞ ሊያርስበት የሚችል ነው፡፡)

እነዚህን ግቦች ማሳካት ይቻል ዘንድ፣ (መንዴን ሮጀክት 2006 ዓ.ም፡3-4) ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነቶች ለማጎልበት ብዙ ጊዜ እና ግብአቶችን መመደብ አስተዋይነት ነው፡፡

## 1. ምክክር መደረግ ያለበት ጊዜ

ምክክሮች መጀመር ያለባቸው በተገቢ ትጋት እና በፕሮጀክት እቅድ ዝግጅት መጀመሪያ ግድም ላይ ሆኖ ሂደቱ ግን እስከ ፅንሰ ሀሳብ ነደፋ ድርድር ማከናወኛ እና ፕሮጀክት እንቅስቃሴ ድረስ መዝለቅ አለበት፡፡ በብዙ ሁኔታዎች፣ ማህበረተሰቡን በምክክር ሂደት ውስጥ ለማሳተፍ እንዲቻል ምክሩ ዓማተግ ጋር መያያዝ አለበት፡፡ ምክክሮች ትርጉም ያላቸው እንዲሆኑ ለማድረግ ደግሞ ውል ከመፈፀሙ በጣም ቀደም ብሎ በመጀመር ለማህበረሰቡ የተስማማ በሚሆን ፍጥነት መካሄድ አለበቸው (AFD 2006 ዓ.ም፡26)፡፡ ኦፕሬተሩም ከማህበረሰቡ ጋር መነጋገሩን እና አብሮ መስራቱ በባለድርሻ አካላት ማሳተፊያ እቅድ መሠረት በፕሮጀክቱ መላ የቆይታ ወቅት መቀጠል ይኖርበታል፡፡

## 2. የምክክር ተሳታፊ አካላት

መመሪያዎች ተጎጂ ከሚሆኑ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚደረግ ምክክር እንዲኖር ይጠይቃሉ (አንቀፅ 9.7)፡፡ በባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ህጋዊ የመሬት ባለይዞታነት መብቶች ያላቸውን ሰዎች ስለመለየት እና በፕሮጀክቱ ሳብያ ሊደርስባቸው ስለማሚለው ተፅዕኖ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ በስሞለር እና ሌሎች (2006 ዓ.ም፡14) እንደተገለፀው በምክክር ሂደት ውስጥ ማካተት ያለባቸው ህጋዊ መብቶች ያሏቸው ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ወገኖች መሆን አለባቸው፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ አከባቢ የራሱ መለያ ባህሪ ሊኖረው ቢችልም፣ መብቶችን በመለያ እና በተፅዕኖ ግምገማ ደረጃ የተለዩት የተጎጂ ወገኖች ዝርዝር በአጠቃላይ የሚከተሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች ፡- በብሄራዊ፣ በክልል እና በአካባቢ ደረጃ ያሉ ባለስልጣኖችን፤ ከበሬታ የሚሰጣቸው የአከባቢ መሪዎችን (ብዙውን ግዜ ባህላዊ ስልጣን ያላቸውን)፤ ህጋዊ የመሬት ባለቤትነት መብት ያላቸውን፤ ልማዳዊ ወይም ኢ መደበኛ መሬት የመጠቀም መብት ያላቸውን፤ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ እንደ አርብቶ አደሮች ያሉ በቋሚነት ነዋሪ ያልሆኑ ቡድንኖችን፤ ጭሰኞችን እና አዛውንቶችን ማካተት ይኖርበታል (USAID 2007 ዓ.ም ዓ.ም ለ፡14፣21)፡፡ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይት የማድረግ እቅድ ያላቸው ሁሉ በመጀመሪያ እንደዚያ ለማድረግ የመንግስት ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልግ መሆን አለመሆኑን በግልፅ ማወቅ አለባቸው፡፡ እውነተኛ አሳታፊ የሆኑ ምክክሮችን ማካሄድ አስቸጋሪ ነው፡፡ በበርካታ አካባቢዎች ልማዳዊ ስርአቶችን እና ተቋማትን ጠብቆ የማቆየት ፍላጐት እና ማህበረሰቡ አስፈላጊ አድርጐ የማይወስዳቸው ቡድኖች ጋር መድረስ መቻል መካከል ውጥረት ሊኖር ይችላል፡፡ ይህን ማለት ግን የተገለሉ ቡደኖች መካተት የለባቸውም ማለት አይደለም፤ እንዲያውም እነሱን ማካተቱ በጣም ፈታኝ ሁኖ የሚታይ ግን ደግሞ በጣም አስፈላጊ እና ስለዚህም ለዚህ ስራ ገንዘብ መመደብ ያስፈልጋል ለማለት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቃሚ የሆነ መመሪያ ሊሰጡ የሚችሉ በርካታ የመረጃ ምንጮች አሉ (ዓፋድ 1999 ዓ.ም)፡፡ እንደ አጠቃላይ ህግ፣ ምክክሮች ከአካባቢው ባህላዊ መሪዎች ጋር ብቻ ተወስኖ መቅረት የለባቸውም፡፡ እነዚህ አመራሮች ምንም እንኳዋን ሰፊውን ማህበረሰብ መወከል የሚችሉ

ቢሆንም፣ ምናልባት የራሣቸው ፍላጐቶች ሊኖራቸው የሚችሉ እና የያዙትን የአመራር ቦታ ለግል ጥቅም ማዋል የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ሣጥን 7፡- ማህበረሰብ የማሣተፊያ አቅዶች

*ምንጭ፡- ስሞለር እና ሌሎች፣ 2006ዓ.ም ፡14*

በተባበሩት መንግስታት የንግድና ሰብአዊ መብቶች ልዩ መልእክተኛ መሰረት፣ ማህበረሰቡ የተስማማበት የምክክር፣ የተሣትፎና የድርድር ሂደት በማህበረሰብ የማሣተፊያ እቅድ ውስጥ ከጅምሩ መቀመጥ አለበት፡- እንደዚያ ያለው እቅድ እያንዳንዱን የሂደቱን ቅደም ተከተል በግልጽ የሚያስቀምጥ ሆኖ፣ ለስምምነቱ የመዳረሻ መንገድ ሆኖ ማገልገል አለበት፡፡ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

1. ሀላፊነትና ተጠያቂነትን በግልፅ የሚያስቀምጥ እቅድ
2. ውል ከመፈፀሙ አስቀድሞ ከተጐጂ ወገኖችና ከግለሰቦች ጋር የሚደረግ ምክክር፤
3. ትርጉም ያለው የማህበረሰብ ማሣተፊያ አንድ ክፍል ሆኖ፣ ፕሮጀክቱን የሚመለከት መረጃና ፕሮጀክቱ ሊኖረው የሚችለውን ተፅዕኖ ይፋ ማድረግ፤
4. ቀደም ባለው ግዜ፡ ፕሮጀክቱን አስመልክቶ ከሚመለከታቸው ወገኖች በአንደኛው ማህበረሰቡን ለማሣተፍ ስለተደረጉ ጥረቶች፣ የሚታወቅ ነገር መኖር/አለመኖሩን፤
5. የአገር ውስጥና ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን እንኳን የሚያሟላ ማህበረሰቡን የማሣተፊያ እቅድ፤ ምሣሌ፡- ነቅአፈ ወይም ተጎጂ ከሆኑት ጋር ምክክር ማድረግ ያለበት መሆኑን ሊጠየቅ ይችላል፡፡

## 3. ምክክር የመከወኛ ዘዴ

አንድ የምክክር ሂደት የእያንዳንዱ ቡድን ልዩ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል (AFD 2006 ዓ.ም፡62)፡፡ ይህንን ስኬት ማምጣት የሚያስችሉ ብዙ ስልቶችና ቴክኒኮች ቢኖሩም ምርጥ የሚባለው ዘዴ የሚወሰነው ግን በአካባቢው የተለየ ሀኔት ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ምክክሮች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረቱ፤ ተአማኒ፣ ሁሉን አቀፍ እና ሴቶችን አሳታፊ የሆኑ፤ እንደዚሁም በምክክሩ ሂደት ተሳታፊዎች ትርጉም ያለው ግብረ-መልስ የማግኘት እድል እንዲኖራቸው የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ዘዴ የመሬት መብት ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ እና የጋራ መግባባት መፈጠሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ሌሎች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

ቦታ፡- ምክክሮች ሁሉም አመቺና ቅርበት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ ይኸውም ብዙ ግዜ ከሰዎች በሚኖሩባቸው ወይም በሚሰሩባቸው አካባቢዎች እያሉ በቀጥታ መነጋገርን ይጠይቃል፡፡ እንደዚህ መሆኑ ደግሞ የሴቶችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

ስብሰባዎች በሚገባ እንዲታወቁ መደረግ አለባቸው፡- ሰዎች ስለስብሰባዎቹ ማወቅ ስለሚኖርባቸው የተለያዩ የመገናኛ መንገዶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ የማስታወቂያዎች ቦታዎችን፣ የሚካሄዱ ክንውኖችን እና በርካታ ክፍሎችን ሊያጋጥሙ የሚችሉ መሰናክሎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በአንዳንድ አካባቢዎች ሴቶች ከመኖሪያ ቤቶቻቸው ርቀው መሄድ የማያስችላቸው ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ከዚህም የተነሳ በመንደሩ አማካኝ ቦታዎች ወይም በወረዳው የመሬት አስተዳደር ቢሮ ውስጥ የሚለጠፉ ማስወቂያዎችን ላያዩ ይችላሉ፡፡

ለባህሉ ተስማሚ የሆነ፡-ምክክሮች ከባህሉ ጋር ተስማሚ መሆን አለባቸው፡፡ ይኸውም ቋንቋ-ነክ፣ የአካባቢውን የውሳኔ አሰጣጥ ልማዶችን እና ፆታዊ ጉዳዩች የመሣሰሉት ማጤን ይኖርባቸዋል ማለት ነው፡፡ በማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ለየት ያሉ ክፍሎች፣ ማለትም እንደ ሴቶች እና አርብቶ አደሮች ካሉት ጋር የሚደረጉ ምክክሮች የቋንቋ አጠቃቀምን ወይም ምክክሮች የሚካሄዱበትን ጊዜ በተመለከተ መነጋገርን ሊጠይቅ ይችላል (AFD፣ 2006 ዓ.ም፣26)፡፡[12]

ሁሉንም ባለ ድርሻ አካላት አሣታፊ የሆነ፡- ተጎጂ የሆኑ ክፍሎች በሙሉ ትርጉም ባለው መልኩ የመሣተፍ ዕድል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ለስኬታማነቱም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ፡- መንግስታዊ ያልሆኑ አካባቢ

[12] በስትራቴጅዎች ለሰፊ ምክክር ላይ ሴቶችን ማሳተፍ ይገባል ኬንት 2012

በቀል ድርድሮችን (መያድቶችን) ወይም ህዝባዊ የሆኑ ድርጅቶችን (ህድቶችን)፣ በማህበረሰቡ ውስን የተለያዩ ክፍሎች አመኔታ ያላቸውን በአወያይነት መጠቀም ሊረዳ ይችላል፡፡ ከአወያዬቹ ውስጥ ደግሞ ጥቂቶቹ ሴቶች መሆን ቢችሉ ጠቀሜታ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡

ከቅጣት ነፃ መሆን፡- በብዙ አካባቢዎች ግለሰቦች ቅጣት ሊከተለን ይችላል ከሚል ስጋት ባህላዊ መሪዎች፣ የመንግስት ተወካዩች፣ የፓሊስ ወይም ወታደራዊ ባለስልጣናት ባሉበት ሃሣባቸውን ለመግለፅ ፈቃደኛ ላይሆኑ ይትላሉ፡፡ ስለዚህ የመንግስትና የአካባቢ ባለስልጣናት በማይገኙበት ስብሰባዎችን ማካሄድ እና የማህበረሰቡን አባላት ከጉዳት ለመጠበቅ ሲባል ሀሳባቸውን ብቻ (ስማቸው ሳይጠቀስ) መዝግቦ መያዝ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

የማህበረሰቡን ውሳኔዎች ማክበር፡- ምክክሮች ትርጉም ያላቸው እንደሆኑ ከተፈለገ ውጤቱ ኢንቬስተሩ ወይም ኦፐሬተሩ እንደሚፈልጉት ላይሆን ቢችል እንኳ የማህበረሰቡ ውሳኔዎች መከበር አለባቸው፡፡

በርካታ ምክክሮችን በተለያዩ ግዜያት ማካሄድ፡- በአጠቃላይ፣ ስኬታማ ተሳትፎ ሊኖር የሚችለው ለብዙ ወራት ወይም አመታትን ሊጠይቁ የሚችሉ ተከታትይ ምክክሮችን በማካሄድ ብቻ ነው፡፡ ቀጣይነት ያላቸው ግንኙነቶችን ለማመቻቸት ከተፈለገ፣ ወደ ፕሮጀክት ትግበራ ከተገባ በኋላም እንኳ ቢሆን፣ ለማንኛውም እድል የሚሰጥ ግልፅ መመሪያ መከተል ተመራጭ ይሆናል፡፡[13]

የምክክሩ ይዘት ፕሮጀክቱን የሚመለከቱ አስፈላጊ መረጃዎች በሙሉ ሰዎች ማወቅ እንዲችሉ ማድረግ አለበት፡፡ በምዕራፍ 5 ውስጥ በተሟላ መልኩ ተብራርቶ እንደሚገኘው ሁሉ የምክክሩ ሂደት አንድ ክፍል ተደርጎ ኦፕሬተሮቹ ፕሮጀክት ነክ የሆኑ አስፈላጊ መረጃዎችን ግልፅ እንዲያደርጉ ኢንቬስተሮቹ መገፋፋት አለባቸው፡፡ ከአካባቢው ማህበረተሰቦች ጋር የሚደረግ የማያቋርጥ ግንኙነት ማድረግ ሰላማዊ ግንኙነቶች እንዲመሰረቱና የፕሮጀክት ኦፕሬተሩ በውሎች ውስጥ በተቀመጠው አግባብነት መስራት/አለመስራቱን ማህበረሰቡ ቁጥጥር ማድረግ እንዲችሉ ሊረዳ ስለሚችል፣ የዚህ አይነቱ ግልፀኝነት በፕሮጀክቱ መላ የቆይታ ግዜ ውስጥ መቀጠል አለበት፡፡

ያለጥርጥር አንዳንድ ግዜ ምክክር የመሬት ባለቤትነት መብቶች ካላቸው ጋር ለሚደረጉ እውነተኛ ወደሆኑ ድርድሮች ሊያመራ ይችላል፡፡ አንድ ድርድር ወጤታማ እንዲሆን ካስፈለገ በምክክር ግዜ የሚሰራባቸውን መርሆዎችና ስርዓቶችን፣ በጣም የተገለሉና ለአደጋ የተጋለጡ ክፍሎች ድምፃቸውን ማሰማት የሚያስችሉ ስልቶችን ጭምር መጠቀም ይኖርበታል፡፡ የመብት ባለቤትነቶችን የመለያ ሂደት፣ መሬት የመጠቀምን መብት በተመለከተ ለመነጋገር መብት ያላቸው እነማ እንደሆኑ ግልፅ ማድረግ አለበት፡፡ ብዙ ግዜ የመሬት ግብይትን አስመልክቶ የአካባቢው ማህበረሰቦች ውል ፈፃሚ ለመሆን የሚያስፈልገውን የባለቤትነት መብቶች ላይኖሯቸው የሚችል ቢሆን እንኳ አስፈላጊ የሆኑ የባለድርሻ አካላት መሆናቸው መዘንጋት የለበትም፡፡ ፕሮጀክቱ ያለችግር እንዲቀጥል ከተፈለገ አጠቃላዩን ማህበረሰብ ማማከር ብቻ ሣይሆን ትብብራቸውን እና ፈቃዳቸውን ጭምር ማግኘት የግድ ይላል፡፡ ይኸውም መደበኛው ህግ የውል ፈፃሚነት ቦታ የማይሰጣቸው ቢሆን እንኳ፣ ማህበረሰቦቹም እንደ አንድ የስምምነቱ ፈፃሚ አካል ሆነው መታየት አለባቸው፡፡

በብዙ ሁኔታዎች፣ ኦፕሬተሮች ከማህበረተሰቡ ጋር የሚያደርጓቸው ስምምነቶች በፅሁፍ የተያዙ እና ሁሉም ወገኖች ከፕሮጀክቱ የሚጠብቋቸውን ነገሮች፣ መብቶቻቸውን እና ሀላፊነቶቻቸውን በግልፅ ያስቀመጡ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ መደረግ ያለበት የመሬት ይዞታ መብቶችን ለማስተላለፍ እንደዚያ ያለው ስምምነት አስፈላጊ በማይሆንበት ወይም በህግ የማይጠየቅ ቢሆንም እንኳን ነው፡፡ አሰቀድሞ እንደተገለፀው ሁሉ፣ እንደዚያ ያለው ስምምነት ከምክክር እቅድ በመነሳት እየጎለበተ ሊሄድ ይችላል፡፡ ብዙዎቹ ማህበረሰቦች እነሱን ወክለው በሚገባ ለመደራደር እውቀቱ ያላቸው አባላት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም ኢንቬስተሩ ወይም ኦፕሬተሩ ማህበረሰቡ ብቃት ያላቸው ህጋዊ ተወካዩች እነዲኖሯቸው ቢረዳቸው ተመራጭ ይሆናል፡፡ ከተቻለ ደግሞ የህግ እርዳታ በሚሰጥ መርሃግብር አማካኝነት ወይም በሌላ መንገድ፣ ግን ደግሞ ኢንቬስተሩ ለማህበረሰቡ ምክር ለሚሰጠው ግለሰብ ወይም ወገን በቀጥታ ክፍያ የማይፈፀምበት አሰራር በመቀየስ ሊሆን ይችላል (አንድ ኦፕሬተር ለማህበረሰቡ ተወካይ ክፍያ ሊሰጥ ይችላል)፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ የጥቅም ግጭት የሚፈጥር ሆኖ ሊታይ ይችላል፤ በተለይም ተወካዩ ያለውን ታማኝነት ለማህበረተሰቡ እና ክፍያውን ለፈፀመለት ሰው ወይም ወገን የሚያሣይ ከሆነ ነው፡፡ ለማህበረሰቡ ጠበቃ ወይም ሌላ ተወካይ ማግኘት አስቸጋሪ ወይም አላስፈላጊ ሆኖ ኦፐሬተሩ ካገኘው ብዙ ግዜ ተአማኒነት ያላቸው አካባቢ በቀል መያድቶች እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

---

13 አብዛኛዎች የተባበሩት አሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጀት ከዚህ በፊት የነበሩ ዝርዝሮች፤ 2015-28-29

## 4. ነፃ፣ቅድመ እና በዕውቅት ላይ የተመሠረተ ፈቃድ (ነቅዕፈ)

በመመሪያዎቹ ውስጥ እንደተገለፀው፣ መሬትን ወይም የተፈጥሮ ሀብቶችን ሊጎዳ የሚችል ሊካሄድ የታሰበ ማንኛውም ፕሮጀክት ወይም ኢንቬስትመንት፣ ተጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ ክፍሎችን ነቅዕፈ ካላገኘ በስተቀር ወደ ስራ መግባት አይኖርበትም፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ለነባር ህዝቦች በክልላቸው እየተተገበረ የሚገኘን ፕሮጀክት የመቃወም ላዕላይ ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡ የኢንቨስትመንቱ አይነት ወይም አድማስ የሚለዋወጥ ከሆነ ደግሞ፣ ይህ ስልጣን የፕሮጀክቱ መላ የቆይታ ግዜ ሊመለከት ይችላል፡፡

በምግብ እና ግብርና ድርጅት (ምግድ) እንደገለጸው ከሆነ ስለ ነቅዕፈ በስፋት ተፅፏል (2006 ዓ.ም ለ)፤ በጉዳዩ ላይ ዘርዘር ያለ ገለፃ መስጠት ከዚህ ህትመት ወሰን በላይ በመሆኑ እንደዚያ አልተደረገም፡፡ የአካባቢው ነባር ህዝቦች ነቅዕይ ለመስጠት ያላቸው መብት የሚመነጨው ነባር ህዝቦችንና ነፃ በሆኑ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ ጎሣን መሰረት ያደረጉ ህዝቦችን አስመልክቶ በዓለም አቀፍ የወዝ አደሮች ድርጅት (አወድ) ከተደነገገው ደንብ (ቁጥር 169)፣ እና የነበር ህዝቦች መብቶችን ከሚመለከተው የተባበሩት መንግስታት መግለጫ ነው፡፡ የዚህ መምሪያ መነሻ፣ 'ነፃ፣ ቅድመ እና እውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድን ማክበር' በሚል ርዕስ የመሬት ባለይዞታነትን በተመለከተ ለመንግስታት፣ ለንግድ ተቋማት፣ ለመያድቶች እና ለአካባቢ ነባር ህዝቦች በቀረበው መምሪያ ውስጥ ስለ ነቅዕፈ ከተሰጠው የሚከተለው ማብራሪያ ነው(ምግድ፣ 2006 ዓ.ም ለ)፡፡

> “የነባር ህዝቦች የጋራ መብት፣ በእንዱስትሪ ወይም የፕሮጀክቱ ወገን በሆነ ማንኛውም የውጭ አካል መሬቶቻቸውን፣ ወሰኖችን፣ በተለይም በጋራ ባለቤት የሆኑባቸውን ወይም የያዟቸውን፣ አለበለዚያም የሚጠቀሙባቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ሊጐዳ በሚችል ጉዳይ ላይ፤ ከመንግስት ከመፅደቁ በፊት፣በፊት በፈቃዳቸው ለመረጧቸው ተወካዮቻቸው ወይም በልማዳዊ ወይም ሌሎች ተቋማት አማካኝነት ውሳኔዎች ለመስጠትና ፈቃዳቸውን የመስጠት ወይም የመንፈግ መብቶቻቸውን ይጨምራል፡፡”

በምግድ (2006 ዓ.ም ለ) የቀረበውን የነቅዕፈ አራት ባህሪያትን፣ እያንዳንዳቸውን በጥልቀት መመልከት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

<u>ነፃ፡-</u> ስለ ፕሮጀክቱ ፈቃዳቸውን ለመስጠት/ላለመስጠት የሚወስኑ ሁሉ፣ እንደዚያ ማድረግ ያለባቸው ያለምንም 'ጫና፣ ማስፈራሪያ ወይም ጥምዘዛ' መሆን አለበት፡፡

<u>ቅድመ፡-</u> ፈቃድ መጠየቅ ያለበት ከማንኛውም ማረጋገጫ ወይም የፕሮጀክት ክንውኖች ከመጀመሪቸው በጣም ቀደም ብሎ መሆን አለበት፡፡ የግዜ ሰሌዳው በባህሉ መሰረት ተስማሚ የሆነና ምክክር ለማካሄድ እና ለአካባቢው ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ፍፃሜ ማግኘት የሚያስችል በቂ ግዜ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

<u>በዕውቀት ላይ የተመሰረተ፡-</u> ሰዎች ስለፕሮጀክቱ ተገቢ የሆነ ምሉዕ መረጃ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የሚሰጠው መረጃም 'ተጨባጭ፣ ትክክለኛና መረጃ የሚደርሣቸው ሰዎች ሊረዱት በሚችሉት መንገድ' መቅረብ አለበት፡፡

<u>ፈቃድ፡-</u> ነዋሪዎቹ በመሬታቸው ላይ ሊካሄድ በታሰበው የፕሮጀክት ክንውን የሚስማሙበት መሆን አለበት፡፡ ይኸውም ፈቃዳቸውን የመስጠት መብት፣ ፕሮጀክቱን አንፈልግም የማለት ወይም የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ፈቃድ የመስጠት መብትን ይጨምራል፡፡

እዚህ ላይ እንደገና፣ አስፈላጊ የሚሆነው ጉዳይ ፈቃድ መጠየቅ ያለበት ከማን ነው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ማህበረሰቡ እንዴትና በማን መወከል እንደሚፈልጉ መወሰን አለባቸው፡፡ የሚሰጠው ውሳኔም ከአካባቢው ልማዶች አኳያ ከቦታ ቦታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ስለዚህ የሴቶች፣ የሰራተኞች፣ የመሬት ይዞታ አልባዎችን ተሳታፊ መሆን የማይችሉ የሌሎች ክፍሎች ፍላጐቶችም መንፀባረቅ የሚችሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦፕሬተሮች ብርቱ ጥረቶች እንዲያደርጉ ኢንቬስተሮቹ መገፋፋት አለባቸው፡፡ በመጨረሻም ፈቃዳቸውን መሰጠት ወይም መንፈግ የሚኖርባቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ማለትም መሬቱ ላይ በተጨባጭ እየተጠቀሙ የሚገኙና በታሰበው ፕሮጀክት በቀጥታ ተጐጂ የሚሆኑ ልማዳዊ ባለይዞታዎች ጭምር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል (ባዘማስ፣2005 ዓ.ም፡13)

በተጨማሪም ነቅእፈ ለአንድ ጊዜ ብቻ ተሰጥቶ ወደሚያበቃ ውሣኔ አሰጣጥ ከሚያመራ ሂደት ባሻገር የሚሄድ ነው፡፡ እንዲያውም ቀጣይነት ያለው ግንኙነት መኖርን የሚጠይቅ የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡ በነቅእፈ ላይ የተብራራ ሀሣብ ማግኘት ካስፈለገ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት በተመለከተ 'ነፃ፣ ቅድመና በእውቀት

ላየ የተመሰረተ ፈቃድን ማክበር’ በሚል ርዕስ፣ ለመንግስታት፣ ንግድ ተቋማት፣ መያድቶች፣ ነባር ህዝቦችና ለአካባቢ ማህበረሰቦች በምግድ የተዘጋጀውን መምሪያ መመልከት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል (ምግድ 2006 ዓ.ም ለ)፡፡

መመሪያዎቹ (አንቀፅ 9.9) የሚጠይቁት ነቅዕፈ ነባር ህዝቦች በሚገኙባቸው አካባቢዎች ብቻ ስራ ላይ እንዲውሉና፤ ምክክርና ተሳትፎን የሚመለከቱት መርሆዎች ደግሞ በሌሎች ማህበረተሰቦች አካበቢ እንዲተገበሩ ነው፡፡ በእነዚያ መርሆዎች በአንቀፅ 38.6 የተቀመጠው፡- “ከሌሎች ጋር መነጋገሪያ ህጋዊ የባለቤትነት መብቶች ያሏቸውን፣ በሚሰጡ ውሣኔዎች ተጎጂ ሊሆኑ የሚችሉትን፤ በተለያዩ ወገኖች መካከል ያለውን የስልጣን አለመመጣጠንን ከግምት ውስጥ በማስገበት ከውሣኔ፣ ድጋፍ ከሚፈልጉና ለአስተዋፅዖቻቸው ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ተያያዥነት ባላቸው የውሣኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ንቁ፣ ነፃ፣ ተገቢ፣ ትርጉም ያለውና በእውቀት ላይ የተመረተ የማህበረተሰቦችንና የቡድኖች ተሳትፎ ማረጋገጥ” የሚል ነው፡፡ ለኢንቬስተሮች አሰተዋይነት የተመለከተ የአደጋ ቁጥጥር ዘዴ የሚሆነው ኢንቬስተሩ በሚፈልገው መሬት ላይ የአካባቢው ነዋሪዎች እየኖሩና እየሰሩ በሚገኝበት በማንኛውም ቦታ በነቅእፈ መልክም ይሁን ወይም በምምክርና በተሳትፎ መርሆዎች መልክ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ ነው፡፡

በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ነቅእፈን መጠቀም ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ለምሣሌ የ 'ባዮ ማቴሪያል' የዘለቄታዊነት ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት (ባዘማአሥ) ነቅእፈ በሁሉም ቦታዎች መተግበርን እንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል (መሥፈርት 12 ለ እና 11-12)፡፡ በተመሣሣይ መልኩ የዘንባባ ዘይት የዘለቄታዊነት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሥርአት (ዘዘማአስ)መሬትን ለወይራ ዘይት ምርት መጠቀም የሌሎች የመሬት ተጠቃሚዎች መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ መብቶችን ሊያሳጣ በሚችልባቸው በማናቸውም ቦታዎች ነቅእፈ ተግባራዊነት እንዲኖራቸው ይጠይቃል (መርህ 2.3)፡፡ እንደዚሁም እንደ ኮካኮላ፣ ፔፕሲና ኔስትል ያሉት በብዙ አገሮች የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ የንግድ ተቋማት ነቅእፈ በእነሱ የሥርጭት ሰንሰለቶች ውስጥ በሚገኙ መሬት በሚያዝባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ ነባር ተወላጆች የማይኖሩ ቢሆንም እንኳን፣ ነቅእፈ እንዲሰራባቸው ይጠይቃሉ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ‘ነባር’ መሆን /አለመሆኑ መወሰን አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰበት የፅንሰ ሀሳቡ ትርጉም የለም፡፡ በመሆኑም በተለያዩ አገሮች ፅንሰ ሃሣቡን አስመልክቶ የተለያዩ ቃላት፡- ቀደምት ሰፋሪዎች፣ ኮረብታ ላይ የሚኖሩ ሰዎች፣ የመጀመሪያዎቹ ብሄሮች፣ ወዘተ ያሉት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ (ዓፋድ፣ 2004 ዓ.ም፡- የአፈፃፀም መለኪያ 7፣ አንቀፅ 4-5)፡፡ በአንዳንድ አገሮች ውስጥ ማህበረተሰቦች ራሳቸውን ነባር ተወላጅ አድርገው ሊያዩ ይችላሉ፡፡ ቢሆንም በመንግሰት ባለስልጣናት ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ የዓንድ (ተጓዳኝ መርሆችን የሚጠቀሙ ትላልቅ የግል ባንኮች) አንዳንድ ግዜ አንድ የስራ ቡድን 'ነባር ተወላጅ' የሚለውን መሥፈርት ማሟላት መቻል/ አለመቻሉን ለመወሰን ደንበኞቻቸውን ባለሙያዎችን እንዲቀጥሩ መጠይቅ ይፈልጋሉ፡፡ ነቅእፈ የሚለውን መጠቀም ኢንቬስተሮችንም ሆነ የአካባቢውን ማህበረሰቦች ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል፤ በማንኛውም ሁኔታ፣ በተለይም በትናንሽ ፕሮጀክቶች፣ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር ከሚመሰረቱ አወንታዊ ግንኙነቶች የረጅም ጊዜ ተጠቃሚ ለመሆንና፤ አሻሚ የሚሆኑ ነገሮችንና አንድ የተወሰነ ቡድን ነባር ተወላጅ መሆን/ አለመሆኑ ለመወሰን የሚያስፈልገውን ወጭ በማስወገድ ረገድ ጠቀሜታ ይኖርዋል፡፡

ለማጠቃለል ያህል፣ መመሪያዎቹን የሚከተሉና ህጋዊ የመሬት ባለይዞታነት መብቶችን የሚያስከብሩና ጉዳት ለማያደርሱ ፕሮጀክቶች ብቻ የገንዘብ ደጋፍ ለማድረግ የሚወሰኑ ኢንቬስተሮች ጠንካራ ምክክርና አሳታፊ ሂደት ተጉጂ ከመሆኑ ከሁሉም ማህበረሰቦች ጋር እንዲኖር አበክረው መጠየቅ አለባቸው፡፡ እንደዚሁም ህጋዊ የመሬት ይዞታ መብት ያላቸውን የሁሉንም ማህበረሰቦች መላ ነቅእፈ የሌለው ማንኛውም ፕሮጀክት መቀጠል የሌለበት ስለመሆነ ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጥ ግፊት ማድረግ አለባቸው፡፡

ሣጥን 8፡-
የምክክር እና የድርድር መቆጣጠሪያ ዝርዝር

በቂ የሆነ የምክክር፣ የተሳትፎና የአካባቢውን ነዋሪዎች ይሁንታን የሚያካትቱ ፕሮጀክቶች፣ ይህን ከሚያደርጉት የበለጠ፣ ለከፍተኛ ወጪዎች ሊዳረጉ ይችላሉ፤ ምክንያቱም የባለይዞታነት መብቶችን መለየት፣ ተፅዕኖዎችን መገምገም ወይም ቀጣይነት ያለው ውጤታማ ግንኙነት ከማህበረሰቡ ጋር መመስረት፣ ፈፅሞ አይቻልም ባይባልም እንኳን አስቸጋሪ መሆኑ ስለማይቀር ነው፡፡ ምክክር የአማተግ አካል መሆን አለበት፡-

- ✓ ኢንቬስተሩ አብሮ ሊሰራ ያሰበውን ማህበረሰብ ልማዶችንና ባህልን የሚያውቅ በአካባቢው የሚገኙ ባለሙያ ማማካር
- ✓ ሂደቱ የሚመራበት ማህበረሰቡን የማሣተፊያ እቅድ ማዘጋጀት
- ✓ ምክክሩ ቀደም ብሎ ፕሮጀክት በሚታቀድበት ምዕራፍ ላይ መጀመርና በተገቢ ትጋት ምዕራፍም፣ የመግባቢያ ሰነድ ድርድርና የፕሮጀክት ትግበራ በመላ ይቀጥላል
- ✓ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ ህጋዊ መብቶች ያሏቸውን ብቻ ሣይሆን ተጐጂ ባለድርሻ አካላት በሙሉ በምክክር የተካተቱ መሆኑን በማረጋገጥ ከአሳታፊ የመለያ ስራ የሚገኙ ውጤቶችን መጠቀም
- ✓ የቡድኑን ልማዶች፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ የውሳኔ አሰጣጥ አሰራሮችና ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ምክክሮቹን መንደፍና ማቀድ ምክክሮችም ይሁንታዊ አሳታፊ፣ እውነተኛ ትብብራዊ፣ በመረጃ ልውውጥ ላይ የተመሰረተና ትርጉም ላለው ግብረ መልስ ሌሎች ዕድሎችን የሚሰጥ መሆን አለበት
- ✓ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉት የተለያዩ ክፍሎች ሴቶችና የአርብቶ አደር ክፍሎች ያሉት፣ ከአጠቃቀም፣ ከአቀራረብ ከቦታ ወይም ከግዜ አንፃር የተለያዩ መስተጋብሮች ሊያስፈልጋቸው እንደሚችል፣ በመገንዘብ እነዚህ ክፍሎች መሣተፍ የሚችሉበትን መንገድ መቀየስ
- ✓ ባህላዊ አግባብነት ባለው መንገድ ለማህበረሰቡ ተገቢ መረጃ መስጠት
- ✓ በርካታ ምክክሮች በተለያዩ ክፍለ ጊዜያት ማድረግና ይህንኑም በፕሮጀክቱ መላ የቆይታ ወቅት ውስጥ መቀጠል
- ✓ በምክክሮቹ ጊዜ የተደረሰባቸው ማናቸውም ውሳኔዎች መዝገቦ መያዝ
- ✓ ኢንቬስትመንቱ የነበር ተወላጆችን መሬትንና የተፈጥሮ ሀብቶቻቸውን የሚጎዳ ከሆነ፣ ፕሮጀክቱ የእነሱ ነፃ፤ ቅድመና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈቃድ (ነቅእፈ) የሚጠይቅ መሆኑን፤ ለእነሱ ማረጋገጫ መስጠት ፈቃድ የመስጠት መብት፣ ፕሮጀክቱን ያለመቀበል መብት ወይም የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ፋቃድ የመስጠትን መብት ይጨምራል፡፡
- ✓ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ከሚመሰረት ጤናማ ግንኙነት ለረጅም ግዜ የሚቆይ ጥቅም ለማግኘት ለማንኛውም ሁኔታ የእነሱን ነቅእፈ የማግኘት አስፈላጊነት ላይ የመሰረተ መመሪያ ማራመድ

# 4

## የቅሬታዎችና የክርክር አፈታት

## የወካይ ምልክቶች አጠቃቀም

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

በርካታ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች መኖር ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በኢንቬስትመንቱ መግፋት እንደሌለበት ሊያነሳሰው ይገባል፡፡

### መካከለኛ የአደጋ መንስኤዎች

ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በተገቢ ትጋት ዝግጅት ምዕራፍ ላይ ፕሮጀክቱን በድጋሚ በመፈተሽና አደጋዎችን የማቃለያ መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# 4. ቅሬታዎች እና ክርክር አፈታት

## ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

መመሪያዎች በመሬት ይዞት መብቶች ላይ የሚነሱ ግጭቶትን ለመፍታት የሚስያችሉ ስርአቶችን የመቀየስና የመተግበር ዋንኛው ኃላፊነት ያለባቸው መንግስታት መሆናቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ መንግስታትም የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡-

ሕጋዊ የይዞታ መብት ጥሰቶች ለመዳኘት የሚያስችል የፍትሕ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህም በመደበኛ የፍትሕ አካላት ወይም በሌሎች የክርክር መፍቻ ዘዴዎች የሚሰጥ ሆኖ፤ ለሁሉም ተደራሽ፣ ፈጣን፣ ውጤታማ እና ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል (አንቀፅ 3.1.4) ፡፡ መንግሥታት በመሬት ይዞታ መብቶች ላይ የሚነሱ ግጭቶችን ለመፍታት ወቅታዊና አቅምን ያገናዘቡ ህጋዊ ወይም ሌሎች አማራጭ መንግዶችን መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ አለባቸው (አንቀጽ 4.9 እና 21.1) ”

የንግድ ተቋማት በሰብአዊ መብቶችና በህጋዊ የመሬት ይዞታ መብቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ካደረሱ ተጐጂዎቹ መፍትሄ የሚያገኙባቸውን መደበኛ ያልሆኑ መንገዶችን ማመቻቸት ወይም መተግበር አለባቸው፡፡ (አንቀፅ 3.2)

እንደነዚያ ያሉት አሰራሮች "ለሁሉም፡- ለሴቶች እና ወንዶች፣ ከቦታ ቋንቋ እና ቅደም ተከተላቸው ተደራሽ መሆን አለባቸው" (አንቀፅ 21.1) ፡፡ መመሪያዎቹ እንደዚሁ የግሉ ዘርፍ መጫወት ያለበትን ሚና እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡- ”

## ለ. አደጋው ምንድ ነው?

መፍትሄ ያላገኙ የመብት ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ፕሮጀክቱ ሊያደክሙ ወይም ተጎጂ ነን የሚል እምነት ባላቸው ወገኖች በሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ከመስጠት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተጨማሪ ወጪዎች ጫና እንዲያርፍበት ይደረጉታል፡፡ ፍርድ ቤት የሚደርሱ ጥያቄዎች ክፍተኛ የሆነ የፕሮጀክት መጓተትን ሊያስከትሉ ይችሉል፡፡ በተባበሩት መንግስታት የንግድ እና ልማት ጉባኤ (ተመንልጉ)በ39 መጠነ-ሰፊ በሆኑ የግብርና ኢንቬስትመንቶች ለይ በቅርቡ የተደረገ ጥናት በኢንቬስትመንቶች ምክንያት መሬት የማግኘት/የመጠቀም ዕድል በመቀነሱ ሳብያ የተከሰቱ ቅሬታዎች እና ክርክሮች በሁሉም ቦታዎች በተደጋጋሚ የታዩ የፕሮጀክቶቹ አሉታዊ ተፅዕኖዎች መሆናቸውን አሳይቷል (ሚርዛ እና ሌሎች 2006 ዓ.ም)፡፡

የዚህ አይነቱ አደጋ የሚመነጨው ከሁለት ተያያዥነት ካላቸው ክስተቶች ነው፡፡ አንደኛው በፕሮጀክቱ የተጎዱ ወይም ጉዳት ሊደርስባቸው በሚችሉ የመሬት ይዞታዎች ወይም በሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የተፈጠረ ክርክሮችን ይመለከታል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ክርክሮች በመንግስት ተቋማት መፍትሄ ይሰጣቸዋል ብለው

ኢንቬስተሮቹ ሊገመቱ ይችላሉ፡፡ በብዙ አገሮች ውስጥ በተግባር የሚታየው ግን ቅሬታዎች ያሏቸው ወገኖች ፍትህ ለማግኘት ከፍተኛ መሰናክሎች፣ ማለትም ተአማ፣ ተደራሽ፣ ፈጣን እና አድሎአዉ ያለሆኑ የፍትህ አሰጣጥ ሂደቶች ያለመኖር ጭምር/የሚያጋጥሟቸው መሆኑን ነው (መንዴን ፕሮጀክት 2004 ዓ.ም፣ ተመሠመከመቢ 2003 ዓ.ም፡29-31)፡፡ ምንም እንኳን ኢንቬስተሩን ወይም ኦፕሪተሩን ከክርክሩ መፈጠር ጋር የሚገናኛቸው ነገር ባይኖርም፣ እንደነዚያ ያሉ ያልተፈቱ ግጭቶች ፕሮጀክትን አደጋ ላይ ሊጥሉት ይችላሉ፡፡

ሁለተኛው፣ በፕሮጀክቱ በራስ መንስኤነት ሊፈጠሩ በሚችል ቅሬታዎች ወይም ክርክሮች ጋር የቆራኘ ነው፡፡ እንደዚያ አይነቱ ሁኔታ ሲኖር ኢንቬስተሩ ወይም ኦፕሬተሩ ከማንም የበለጠ ቀጥተኛ የሆነ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

በሁለቱም ሁኔታዎች ቢሆን ኢንቬስተሮቹ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ነክ አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል፡፡ በፍሪንክስ እና ሌሎች (2006 ዓ.ም) መሰረት፣ በአንዳንድ በተባባሱ ሁኔታዎች ደግሞ በመሬት ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች፣ በማዕድናት ቁፋሮና ማውጣት መስኮች ላይ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች ስራቸውን በማቋረጣቸው ምክንያት በየአመቱ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ያወጣሉ፡፡ በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩትም ቢሆኑ ከፍተኛ ኪሣራ እንደዚሁ ሊያጋጥማቸው መቻሉ ብዙ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

መፍትሄ ያላገኙ ግጭቶች በግብርና ስራ ላይ የተማሰማሩ ፕሮጀክቶች የዘላቂታዊነት ጠቃሚ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቶች ወይም ገንዘብ በብድር ከማግኘት ሊያግዳቸው ይችላሉ፡፡ የፕላስቲክ ጥሬ እቃዎች ወይም 'ባዩፊውል' በሚመረትበት መሬት ጋር በተገናኘ መፍትሄ ያላገኙ ግጭቶች ካሉ የ'ባዩ ማቴሪያል' የዘለቄታዊነት ማረጋገጫ (ባዛማ) ማግኘት አይችሉም (መርህ 12.1)፡፡ የዘንባባ ዘይት ዘለቄታዊነት ማረጋገጫ አሰጣጥ (ዘዘዘደአ) እንደዚሁ ተመሣሣይ መርህዎችን ይዟል (መርህ 2.2)፡፡ እንደዚሁም ከ 'ኢኮዌተር' መርሆዎች ውስጥ ስድስተኛ መርህ በአንዳንድ ሁኔታዎች ተበዳሪዎች የቅሬታ አፈታት ስርዓቶች እንዲኖሯቸው ይጠይቃል፡፡

## ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

መንግስታት ክርክሮችን መፍታት እንዳለባቸው መመሪያዎቹ ያስገነዝባሉ፡፡ ቢሆንም በብዙ ሀገሮች ውስጥ ያለው መደበኛው የህግ ስርዓት ግን በሚገባ አይሰራም፡፡ መሬት ነክ ለሆኑ ጉደዩች መፍትሄ ለማግኘት አመታት ወይም እስከ አስርት አመታት ሊወስድ ይችላል፡፡ በእርግጥ የግል የንግድ ድርድቶች መደበኛውን የህግ ስርዓት የሚተካ ስርዓት ማቋቋም አይችሉም፡፡ ይሁን እንጂ ከመደበኛዎቹ ስርዓቶች በተጨማሪነት ተገቢ የቅሬታ ወይም የክርክር አፈታት ስርዓት እንዲኖር ለማድረግ ኦፕሬተሮች ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት ለመስራት ዝግጁነት እንዲኖራቸው ኢንቬስተሮች የበኩላቸወን ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡ እንደዚያ መደረጉ በመሬት ይዞታ መብት ዙሪያ ከሚፈጠረ ቅሬታዎች ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ጉዳቶችን መጠን ለመቀነስ በጣም ሊረዳ ይችላል፡፡ የንግድ ስራ ና የሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ በተባበሩት መንግስታት (ተመ) የተነደፉት አበይት መርሆዎች (ለምሳሌ መርህ 29)፣ የንግድ ድርጅቶች "ከፍተኛ ተጎጂ መሆን ለሚችሉ ግለሰቦችና ማህበረተሰቦች ተገቢ የቅሬታ አፈታት ስርዓቶችን ራሳቸው በመቀነስ ወይም በተሳትፏቸው ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው" ያስገነዝባሉ፡፡ መርህ-9 እንደዚሁ ተመሣሣይ ነጥቦችን አካቷል (ምግድ፣ 2006 ዓ.ምሐ)፡፡

በአንዳንድ ቦታዎች የቅሬታ አፈታት ስርዓቶች መኖር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ ለአብነት ያህል በጋራ ስምምነት ላይ የተደረሰበትና፣ በሁሉም ተጐጂ ወገኖች ተቀባይነት ያለውና ሊተግባር የሚችል በፅሁፍ የሰፈረ የቅሬታዎች አፈታት ስርዐት መኖርን የዘዘማአሥ ማረጋገጫ ለመስጪያነት አንደ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል (ዘዘመአሥ፣ 2005 ዓ.ም መርህ 6.3)፡፡

ታድያ ስኬታማ ነው ሊባል የሚችል የቅሬታ እና ክርክር አፈታት ስርዐት መለያ ባህሪያት ምንድን ናቸው? በዚህ ርእሰ-ጉዳይ ላይ ጠቃሚ ሃሣቦችን በዝርዝር ለአንባቢያን የሚያቀርቡ አያሌ ፅሁፎች ይገኛሉ (መልካም ምግባር ማስታወሻ በዓፋድ፣ 2001 ዓ.ምን ይመልከቱ)፡፡ ኢንቬስተሮች ወይም የፕሮጀክት ኦፕሬተሮች ለተወሰነ አካባቢ ተስማሚ የሆነ የአሰራር ዘዴ በመንደፍ አካባቢ-ነክ እውቀት ካላቸው ባለሙያዎችና ድርጅቶች ምክር ለማግኘት መጣር አለባቸው፡፡ በጥቅል አነጋገር እንደነዚያ ያሉት ዘዴዎች ስኬታማ ናቸው የሚሰኙ የምክክር ሂደቶች መለያ የሆኑ ባህሪያትን ያካተቱ፣ ከማህበረሰቡ ጋር በቅንጅት የተነደፉና ባህላዊ ተስማሚነትና ግልፀኝነት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን፣ ስሞለርና ሌሎች (2006 ዓ.ም፡2) እንደጠቀሱት ከሆነ፣ የአሰራር

ዘዴዎቹ ማህበረሰቦቹ ቅሬታቸውንና ስጋታቸውን ወቅታዊና ሚዛናዊ የሆነ ምላሽ ማግኘት በሚችሉበት መንገድ ማቅረብ የሚያስችሏቸው መሆን አለባቸው፡፡ በምክክርና በድርድር ሊፈቱ የማይችሉ ጉዳዮችን አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ገለልተኛ አካል ሊኖር ይገባል፡፡ የአካባቢው ማህበረሰብ አመኔታ የተቸራቸው፣ ለፆታ ነክ ጉዳዩች ትኩረት የሚሰጡ መያድቶችም፣ በተለይም ሴቶችና የተገለሉ ክፍሎች በልማዳዊ አሰራሮች ተጠቂ ሊሆኑ በሚችሉባቸው አካባቢያዎች እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡[14]

እንደዚህ ያሉ አሰራሮች፣ ከማህበረሰቡ ጋር በስፋት ከተደረገ የምክክር ሂደት ላይ መመሥረት አለባቸው፡፡ ኦፕሬተሮቹ በዚህ ሂደት ውስጥ ማህበረሰቡ ቅሬታዎችን በምን አግባብ እንደሚፈቱ፣ ለዚያ ማህበረሰብ ለፕሮጀክቱ ጭምር ተስማሚ የሆነ አሰራር ላይ ከስምምነት ለመድረስ እንዴት እንደሚወያዩ ኦፕሬተሮቹ የማወቅ አጋጣሚ ይገኛሉ፡፡

የተጎጂነታቸውን መጠን ለመቀነስ በመመሪያዎቹ መሰረት መንቀሳቀስ የማፈልጉ ኢንቬስተሮች፣ለመሬት ወይም በሌሎች ጉዳዩች ዙሪያ ለሚከሰቱ ማናቸውንም ግጭቶች ሚዛናዊ የሆነ መፍትሄ የሚያስገኝ ፓሊሲ መቅረፅና መተግበር እንደዚሁም ለባህል ቦታ የሚሰጥና ለሁሉም የባለድርሻ አካላት ስምምነት ላይ የተደረሰበት የቅሬታ አፈታት ዘዴ መጠቀም አለባቸው (ኦክስፋም፣ 2006 ዓ.ም፡53)፡፡

ሳጥን 9፡-
ቅሬታና ክርክር አፈታት
መቆጣጠሪያ ዝርዝር

ምላሽ ያላገኙ የባለይዞታነት ጥያቄዎችና ቅሬታዎች የፕሮጀክቱን ስራ ሊያዳክሙ ይችላሉ፤ ወይም ተጐጂ  ነን የሚሉ ወገኖች የሚያነስዋቸውን ጥያቄዎች ከማስተናገድ ጋር በተያያዘ የተጨማሪ ወጪዎች ጫና ያርፍበታል፡፡

- ✓ መደበኛ ያልሆነ የቅሬታና የክርክር አፈታት ስርዓት መፍጠር ከማህበረሰቡ በሚደረገው የምክክር ሂደት ጋር አንደኛው የመወያያ ርዕስ መሆን አለበት፡፡ የአሰራር ሂደቱን ማህበረሰቡና ኦፕሬተሩ በጋራ ሆነው ግልፅ ማድረግ አለባቸው፡፡
- ✓ ብዙ ጊዜ ሂደቱ ሲነደፍ የባለሙያን ድጋፍ መጠየቅ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ አንደ ስኬታማ የምክክር ሂደቶች ሁሉ የቅሬታ አፈታት ስርዓት ከማህበረሰቡ አባላት፣ ሴቶችን ጭምር፣ ልማዶች፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ የውሣኔ አሰጣጥ መንገዶችና ፍላጐቶቻቸውን የሚስማማ መሆን አለበት፡፡
- ✓ አሰራሩ ወቀታዊና ሚዛናዊ ወደ ሆነ የቅሬታና የክርክር አፈታት ማምራት አለበት፡፡

[14] ሁለገብ ከዳኝነት ውጭ ቅሬተዎች የመፍቻ መንገዶች ዝርዝር የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ መልዕክተኛ ጽህፈት ቤት፤፡

# 5

# ግልፀኝነትና ሙስና

## የወካይ ምልክቶች አጠቃቀም

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

በርካታ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች መኖር ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በኢንቬስትመንቱ መግፋት እንደሌለበት ሊያነሳሰው ይገባል፡፡

### መካከለኛ የአደጋ መንስኤዎች

ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በተገቢ ዝግጅት ምዕራፍ ላይ ፕሮጀክቱን በድጋሚ በመፈተሽና አደጋዎችን የማቃለያ መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# 5. ግልፀኝነትና ሙስና

## ሀ. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

ኢንቬስትመንታቸውን በመሬት ላይ ሊያውሉ ወይም በኢንቬስትመንቶቹ ተጐጂ ለሚሆኑ ወይም ሌሎች ወገኖች በሙሉ የግልፀኝነት አሰራርን ማራመድና ሙስናን ማስወገድ አስፈላጊ ስለመሆኑ መመሪያዎቹ በተወሰኑት ክፍሎች ውስጥ በአፅንኦት ይገልፃሉ፡፡ የሚከተሉት መንገዶች እንደ አብነት ተጠቃሽ ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

- መንግስታት መስናን ለመከላከል፤ በተለይም የግልፀኝነት አሰራርን በማጎልበት፣ ውሳኔ ሰጪ አካላት ተጠያቂነት እንዲኖርባቸው በማድረግና አድሏዊ ያልሆኑ ውሳኔዎችን በወቅቱ እንዲሰጡ ለማደረግ ያለመታከት መስራት አለባቸው (አንቀፅ 10.5) ፡፡ ❞
- መንግስታትም ሆኑ ሌሎች ወገኖች ጭምር የእቃዎች ግብይይቶችና የገበያ ዋጋ ውሎችን በተመለከተ የሚሰጡ መረጃዎች፣ በምስጢር መያዝ የሚገባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሁኖ፣ ግልፅና በስፋት የሚሰራጩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው (አንቀፅ 11.4) ፡፡ ❞
- መንግስታትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተዋናያን ሙስናን ለመከላከል በተለይም ህዝቡ እንዲያጋልጥ በማድረግ እነዚህን ስነ-ስርአቶች ማስተዋወቅና በገበያዎች እንቅስቃሴ ውስጥም መተግበራቸውን መቆጣጠር አለባቸው (አንቀጽ 11.7) ፡፡ ❞
- በመሬት፣ በዓሣ ሀብትና በደኖች ላይ በሚደረጉ ኢንቬስትመንቶች መንስኤነት በመሬት ባለይዞታነት መብቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውም ውሎች በግልፀኝነት በዘርፉ አግባብነት ባላቸው ብሄራዊ ፖሊሲዎች እና አነስተኛ ባለይዞታዎች ተኮር ከሆኑ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና እድገት ዘለቄታ ያለው የሰው ሀብት እድገት አላማዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ መተግበር አለባቸው (አንቀፅ 12.3) ፡፡ ❞
- ውል ፈፃሚ የሆኑ ወገኖች በሙሉ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች በሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉና ስለድርድሮቹም ማወቅ እንዲችሉ የተሟላ መረጃ መስጠትና እንደዚሁም ስምምነቶችን ተጎጂ የሆኑ ወገኖች በሙሉ ሊረዱ በሚችሉበት አኳኋን በፅሁፍ ሰፍረው እንዲቆዩ በማድረግ ጥረት ማድረግ አለባቸው (አንቀፅ 12.11) ፡፡ ❞

ሌሎች ክፍሎች የግልፀኝነት አሰራሮችን አስፈላጊነት በማስተዋወቅና፣ ባለድርሻ አካላትም ከውርስና በካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ የሚፈፀም የውሳኔ ተግባርን እንዲያስወግዱ፤ በመሬት ባለይዞታነት መብቶች ላይ መረጃ እንዲኖር፣ ለእነዚያ መብቶችም ዋጋ መስጠትና የክርክር አፈታት ስርዓቶች እንዲኖሩም ግፊት ማድረግ ይኖርባቸዋል (አንቀፅ 16.6፣17.5፣18.3፣18.5 እና 21.5) ፡፡

## ለ. አደጋው ምንድነው?

ሙስና እና የግልፀኝነት አሰራር አለመኖር በኢቬስተሮች ላይ ብዙ ጉዳቶችን ያስከትልባቸዋል፡፡ ሙስና በስፋት የመንሰራፋት እድል ሊያገኝ የሚችለው ይበልጡን የግልፀኝነት አሰራር እጦት ባለባቸው ቦታዎት በመሆኑ፣ ሁለቱ የማይነጣጠሉ ናቸው በመንዴን ኘሮጀክት (2005 ዓ.ም፡4) መሰረት፣ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ከግልፀኝነትና ከሙስና ጋር የተያያዙ ችግሮች የሚስተዋሉት የግብርና ኢንቬስትመንቶች በከፍተኛ ደረጃ እየተለመዱ በመጡባቸው በበርካታ አገሮች ውስጥ ነው፡፡

በሙስና መሣተፍ ኦፕሬተሮችንና ኢንቬተሮች ተግባራዊነት ባላቸው በተለያዩ አገር-ዘለል ብሄራዊ ህጐች በወንጀል ተጠያቂነት እንዲኖርባቸው ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ የግሉ ዘርፍ ኢንቬስተሮች በውጭ አገራት የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራትን በተመለከተው የአሜሪካ ህግና እንደዚሁም በዓለም አቀፍ የንግድ ግብይይቶች ላይ በውጭ ሀገር ባለስልጣናት የሚፈፀም ጉቦን ለመዋጋት በኢኮኖሚያዊ ትብብርና ልማት ድርጅት |ኢትልድ| ስምምነትን ባፀደቁ በብዙ አገሮች ብሔራዊ ህጐች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ በመሬት ላይ ከሚደረጉ ኢንቬስትመንቶች ጋር ተያይዞ የሚፈፀም ሙስና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ጐጂ ነው፤ በመሆኑም የኢንቬስትመንቱ ወጪ ከመጨመርም በላይ ለግጭት መንስኤ ይሆናል(ኢትእድ፣ 1889 ዓ.ም፡35-36)፡፡ ስለዚህ በAFD (2006ዓ.ም፡47) መሬት ሙስና ትልቅ የአደጋ መንስኤ በመሆኑ ኢንቬስተሮች ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩርት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

የመሬት መብቶች ለኢንቬስተሮች እንዲተላለፉ ያደረገው በዋነኛነት መንግስት ከሆነ ደግሞ መጠነ-አደጋው ሊጨምር ይችላል፤ ምክንያቱም እንደነዚያ ያሉ የመብት ማስተላለፍ ሂደቶች መኖር ጉደዩን በማስፈፀም ተዋንያን ለሚሆኑት ባለስልጣናት የገንዘብ ምንጭ የማግኚያ ጥርጊያ መንገድ ስለሚከፈትላቸው ነው፡፡ በመሆኑም በአካባቢው ነዋሪዎች በመሬት ወይም በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች ባለስልጣናቱ ውሳኔ ለመስጠት ወይም በትክክል ተመዝግበው እንዲያዙ ለማድረግ የሚኖራቸው ፍላጐት አነስተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ይኸውም በፅሁፍ የተያዘ ቋሚ መረጃ የሚኖር ከሆነ ለሙሰኛ ባለስልጣናቱ ጉቦ የማግኘት እድላቸውን አጣብቂኝ ውስጥ

ሊከትባቸው ስለሚችል ነው (መንዴን ኘሮጀክት፣ 2005 ዓ.ም፡29)፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ ከፍተኛ አደጋ የሚኖርበት ሁኔታ የሚከሰተው ኢንቬስተሩ በሽርክና ለመስራት ስምምነት ላይ ሲደርስ ነው (ይህም ብዙ ህጋዊ ቅርፆች) ሊኖሩት የሚችል መሆኑን፡ - በንግድ ተቋማት፣ በእሽሙር ማኅበር፣ ወይም በመደበኛ የሽርክና ማኅበር አሰራሮች መልክ ጭምር በፓለቲካው ተሳትፎ ካለው ግለሰብ ጋር (ብዙውን ግዜ ከፍተኛ የፖለቲካ ባለስልጣን ወይም እንደዚያ ካለ ሰው ጋር ዝምድና ያለው ግለሰብ ጋር ሊደረግ የሚችል ነው)፡፡ እንደነዚያ ያሉ ግለሰቦች ለጉበኛነትና ለሙሰኝነት እጅጉን ተጋላጭ የሆኑ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡[15] የግልፀኝነት አሰራር አለመኖር ለሙስና ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ህዝቡ በተለይም የአካባቢው ማህበረሰብ እንዳንድ ኢንቬስትመንት መቃወም የሚችሉበትን አጋጣሚ ሊያባብሰው ይችላል፡፡ የመረጃ እጥረት በአካባቢው ህዝብ ላይ እርግጠኛ ያለመሆን ስሜትን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይህም በበኩሉ ፍራቻና ሊካሄዱ በታሰቡ ኘሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ወደ ማስነሳት ሊያመራ ይችላል፡፡ በአንፃሩ ማህበረሰቦች የበለጠ እያወቁ በሄዱ ቁጥር፣

ሣጥን፡-10፡-
የግልጸኝነትና ሙስና
የአደጋ መንስኤዎች

**ከፍተኛ አደጋ**

- ኘሮጀክቱ ሊተገበር የሚችልበት አካባቢ ትልቅ ሙስና ያለበትና ከታሰበው ኘሮጀክት ጋር በተገናኘ የሙስና ተግባራት ተስተውሏል፡፡
- በኢንቬስትመንቱ ውስጥ ያሉ በእሽሙር የሚሰሩ ወይም ሌሎች የአካባቢው አጋሮች የሙስና ተግባራት ሲፈፅሙ ታይቷል፡፡

**መካከለኛ አደጋ**

- ተጐጂ ባለድርሻ አካላት ስለኘሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ የፕሮጀክቱ ንብረት ባልሆኑ ነገሮች ሁሉ ላይ መረጃዎችን በሙሉ ግልፅ ማድረግን በሚያካትት ተጐጂ ባለድርሻ አካላትና በሚያካትት ውጤታማ፣ ለባህሉ ተስማሚና ግልጽነት ባለው የምክክር ሂደት ላይ ገና ተሳታፊ አልሆኑም፡፡
- በአካባቢው ያሉ የኘሮጀክቱ ሽሪክ ወይም ኦፕሬተር ባለድርሻ አካላት፣ (ለአካባቢው ማህበረሰቦች ጭምር) የፕሮጀክቱ ንብረት ባልሆኑ ነገሮች ሁሉ ላይ መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ አይሆንም፡፡
- ለበአገር ውስጥ ወይም ኘሮጀክቱ በሚተገበርበት አካባቢ የህግ የበላይነት ደካማ ነው፡፡

[15] ለውይይት ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ስጋት ያለበት ሰው ፌደራል የገንዘብ ተቋማት ኢንስቲትዩሽን የምርመራ ካውንስል ህትመት ይመልከቱ የታተመበት ጊዜ ያልተገለጸ፤

ኢንቬስትመንትን ለመቀበል የሚኖራቸው ስሜት የተሻለ ሊሆን ስለሚችል በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግልፀኝነት መኖር አወንታዊ ውጤት ሊኖረው ይችላል (ሚርዛ እና ሌሎች፣ 2006ዓ.ም፤ እና ዓፋድ የአፈፃፀም መለኪያ 1፣ አንቀፅ 29)፡፡

የግሉ ዘርፍ ተወካዩች ምስጢራዊነትን በተመለከተና ፕሮጀክት ነክ የሆኑ ግልፅ መረጃዎችን በስፋት ለመስጠት የሚጠይቀው የወጪ መጠን ላየ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቅርቡ የተደረገ አንድ ጥናት፣ የላቀ ግልፀኝነት መኖር የንግድ ስራን ከመጉዳት ይልቅ ከተሻለ የገንዘብ ነክ ክንውን ጋር በአወንታዊ መልኩ የሚዛመድ መሆኑ አሳይቷል (ሚከርትና ካልአን፣ 2002 ዓ.ም፡54-55)፡፡

## ሐ. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

### 1. ሙስና

በተወሰነ አካባቢ ሙስና በአጠቃላይ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ኢንቬስተሮች ርዕሱን በተመለከተ የተፃፉና ይፋ የተደረጉ የተለያዩ ህትመቶችን ለምሳሌ በዓለም አቀፍ የሙስና እይታዎች ግልፀኝነት የአገሮች ደረጃ ማውጫ ማገላበጥ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ኢንቬስተሮች የዛ አይነቱን መረጃ የኢንቬስትመንት አደጋ መጠን ለመለካት የሚያደርጉት የአጠቃላይ ጥረት አካል አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ (መንዴን ፕሮጀክት 2005 ዓ.ም፡23-25) ፡፡ሌላኛው ማሳያ ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት አገር ሙስናን ለመዋጋት የተባበሩት መንግስታት የ1995 ስምምነትን ምን ያህል ተግብራለች የሚለውን ነው፡፡

ብዙሃኑ ኢንቬስተሮች በአገር አቀፍ እና በፕሮጀክት ደረጃ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎችን በበቂ ሁኔታ ለመረዳት በአካባቢው ካሉ ባለሙያዎች ምክር ሊያስፈልጋቸው ይችላል (UNGC 2006 ዓ.ም)፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው በተለይም ለውጭ ሰዎች ለመረዳትና አቅራቦት ለማግኘት በጣም አዳጋች የሚሆኑ በልማዳዊ መንገድ ውሳኔ ሰጪ የሆኑ ተቋማት ተስፋፍተው በሚገኙባቸው ቦታዎች ነው፡፡ እንደነዚህ አይነቶቹ ተቋማት ከሙስና ነፃ አይሆኑም፡፡ በአካባቢው የሚገኙ ምሁራን እንደነዚህ ባሉ አካላት ወይም ግለሰቦች ላይ ምናልባትም ቁጥጥር ማድረግ እና ተፅዕኖ ማሳረፍ ስለማይችሉ፣ የመሬት ባለይዞታነት መብቶች ማስተላለፎች ሲኖሩ በህገወጥና አግባብ ባለሆነ መንገድ ተጠቃሚ የመሆን እድል ሊሰጣቸው ይችላል (USAID 2007 ዓ.ም ለ፡ 12)፡፡ እነዚያን መሰል አሰራሮች የአካባቢውን ማህበረሰብ፣ በተለይም ሴቶችንና አነስተኛ ወይም ምንም ተፅዕኖ ማሳደር የማይችሉትን፣ ሊጎዱ ይችላሉ፡፡ መመሪያዎቹ በግልፅም ባይሆን ይህን አደጋ ይጠቀማሉ፡፡ ይኸውም ነባር ህዝቦች የባለይዞታነት መብቶችን ባሏቸው ማህበረሰቦች እና ሌሎች የልማዳዊ መብቶች ባለቤቶች በስፋት ባሉባቸው አካባቢዎች የሚፈፀም ሙስናን መዋጋት አስፈላጊ መሆኑን በሚያሳስብ መልኩ ነው(አንቀፅ 9.12)፡፡

እንደዚሁም ኢንቬስተሮች በፕሮጀክት እንቅስቃሴ ወቅት በማንኛውም ግዜ ቢሆን አቋማቸው ለሙስና ምንም ትዕግስት የማይኖር መሆኑን የሚያንፀባርቁ ፓሊሲዎችንና አሰራሮችን መከተል አለባቸው፡፡ ኦፕሬተሮቹ ወይም ኢንቨስት የሚያደርጉባቸው ፕሮጀክቶች ተመሣሣይ አቋም እንዲይዙ ኢቬስተሮቹ ግፊት ማድረግ አለባቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ፓሊሲዎች ከግልፀኝነት ጋር ከሚያያዙ ተመሣሣይ ሀሳቦች ጋር በተጓዳኝነት መታየት አለባቸው፡፡

በዛ ያሉ የደረጃ መለኪያዎች እና ማረጋገጫ መስጫ ስርዓቶችም እንደዚሁ ይህንኑ ምክር አዘል ሀሳብ አስገዳጅነት ባለው መልኩ ያስተጋባሉ፡ ለምሣሌ የንግድ ተቋማት ለስነ-ምግባራዊ አሰራሮች ቁርጠኝነትን ማሳየት እንዳለባቸው የሚጠይቀው የዘዘዘማአ አባል በማድረግ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው የሚጠይቁ ክፍሎች ተቋማቱ ፓሊሲዎቻቸው ሙስናን፣ ጉቦንና ማጭበርበርን የሚያግዱ መሆን እንዳለባቸው ማወቅ አባቸው (መርህ 1.3) ፡፡

በተመሣሣይ መልኩ የእርሻ መሬት መርሆችን የተቀበሉ ተቋማዊ ኢንቬስተሮች በግብርና ኢንቨስትመንት 'ከፍተኛ የስራና ስነ-ምግባራዊ መለኪያዎችን' በሚያሟላ መልኩ መንቀሳቀስ አለባቸው (መርህ 4) ፡፡ እንደዚሁም እነሱን ወክለው የሚሰሩትም ተመሣሣይ የሆኑ ከፍተኛ የስራ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ መገፋፋት አለባቸው፡፡

ፖሊሲዎቹ በራሣቸው በቂ አይደሉም፡፡ ኢንቬስተሮች ያለጥርጥር የውስጥ ቁጥጥሮች ማለትም የቁጥጥርና የአፈፃፀም መርሀ ግብሮች ጭምር ሊኖራቸው የሚገባና ጥቅም ላይ እንዲያውሉም የሚገፋፉ መሆን አለባቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ የውስጥ ቁጥጥሮችና መርሀግብሮች የንግድ ተቋሙ መረጃ አያያዝ ጉቦኝነትን ወይም በሌሎች የሙስና ተግባራት አባሪነትን ለመደበቂያነት ማዋል የማይችሉ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው (ኢትልድ 2003 ዓ.ም፣ ክፍል VII፣ አንቀፅ 2)

## 2. ግልፀኝነት

ኢንቬስተሮች ከግብይይት ጋር ተያያዥነት ያላቸው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ ለህዝቡ እንዲደርሱ በማድረግ ከግልፀኝነት እጦት መነሻ የሚከሰቱ አደጋዎችን መቆጣጠር ይችላሉ፡፡ይህም ከሚከተሉት ውስጥ ጥቂቶቹን ወይም ሁሉንም ሊጨምር ይችላል፡- ውሎች፣ ዓማተግ፣ የተግባራዊነት መለኪያ ጥናቶች፣ የፕሮጀክቱ ባለቤትነት ዋነኛው ተጠቃሚ ማንነት ወይም የሸሪኩ እና ውድድር በመኖሩ ሳቢያ በሚስጥር መያዝ ከሚገባው መረጃ ውጭ ያለማንኛውም አስፈላጊ የሆነ መረጃን ይመለከታል፡፡ ምናልባትም የግልፀኝነት መኖር ከባለድርሻ አካላት ተሣትፎ፣ ምክክር እና ከማህበረሰቡ ጋር ጠንካራ ግንኙነቶች የመመስረት ሂደት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡

በአፍሪካ ውስጥ በመሬት ላይ የሚደረጉ መጠነ ሰፊ ኢንቬስትመንቶችን በተመለከተ አባል የሆኑ መንግስታት መሰረታዊ መርሆዎች የሚጠቁሙት “ኢንቬስተሮች በኢንቨስትመንቶቻቸው ሳብያ ሊጐዱ ለሚችሉ ወገኖች የተሟላ ፕሮጀክት ነክ መረጃ በግልፅ እንዲሰጡ መጠየቅ” ያለባቸው መሆኑን ነው (የአፍሪካ ህብረት፣ 2006 ዓ.ም፣ መርህ 4) ፡፡ በምዕራፍ 3 ውስጥ እንደተገለፀው የዓፋድ ደንበኞቹ የምክክር ነቅአፈ መስፈርቶችን ማሟላት ይችሉ ዘንድ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲሰጡ ይጠየቃል፡፡

> “ (i) የፕሮጀክቱን ዓላማ፣ አይነትና መጠን፤ (ii) የታሰበው ፕሮጀክት ተግባራት የሚወስደው ግዜ፤ (iii) በማህበረሰቦቹ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎች እና ተፅዕኖዎች እንደዚሁም ተገቢ የሆኑ የማቃለያ እርምጃዎች (iv)ባለድርሻ አካላትን የማሳተፊያ ሂደት፤ እና (v) የቅሬታ አፈታት ዘዴዎች ናቸው፡፡[16]

ኢንቬትስመንቱን የሚመለከት የተወሰኑ መረጃዎች፡- ማለትም የስራ እቅዶች፣ የገበያ ጥናቶች ወይም ወቅታዊ ንግድ ነክ መረጃዎች ያሉት ግልጽ ቢደረጉም ሌሎች ተወዳዳሪዎችን የበለጠ ተጠቃሚ ሊደርጉ የሚችሉ ከሆነ በሚስጥር ሊያዙ ይችላሉ፡፡

ይሁን እንጂ በፕሮጀክቱ መላ የቆይታ ገዜ ግልፀኝነት የተመላበት አሰራርና ሚዛናዊ የሆነ የተሟላ መረጃ ይፋ ቢደረግ ማህበረሰቦችንና መንግስታትን ፕሮጀክቱን በሂደት ለመቆጣጠር ያስችላቸዋል(ስሞለርና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም ፡49)፡፡ ይህ ደግሞ ተጎጂ ከሚሆኑ ባለድረሻ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት የመመስረቻ መንገዶች ውስጥ ዋነኛው ነው፡፡[17] የመረጃ ግልፅ መደረግ ከተወዳዳሪዎች አንፃር በትክክል ተጎጂ ያደርጋል ሊባል ከሚችል እና በሚገባ ተለይቶ የተቀመጠ መረጃ በስተቀር፣ የመረጃ ይፋነትን የሚያራምድ አሰራር መከተል ብልህነት ነው (EIB፣ 2007 ዓ.ም)፡፡

የኢንቨስትመንት ውሎችን ግልፅ ማድረግ|አለማድረግ ኢንቬተሮችን እና ኦፕሬተሮችን በብርቱ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው፡፡ ሆኖም እንደዚያ መደረጉ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ መጠነ ሰፊ የሆነ ግብብነት ያለ ይመስላል (ስሞለርና ሌሎት፣ 2006 ዓ.ም፡53)፡፡ ለምሳሌ በንግድና በሰብአዋ መብቶች ላይ የተባበሩት መንግስታት ልዩ መልዕክተኛ፣ ዓለም አቀፍ የጠበቆች ማህበር፣ የተባበሩት መንግስታት ምግብ የማግኘት ዋስትና ልዩ ቃል አቀባይ እና ሌሎች ጭምር ይህንን አቅዋም ይጋራሉ፡፡ የዘዘዘመአ እንደዚሁ በሚስጥራዊነት መያዝ ከሚገባቸው ንግድ ነክ ጉዳዩች በስተቀር ፕሮጀክቱን የሚመለከቱ ሰነዶች በሙሉ ግልፅ እንዲያደረጉ ይጠይቃል (መርህ 1.2)፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ጥቂት አገሮች፡- ኢኳዶር፣ ኢትዩጵያ፣ ላይቤርያ እና ፔሩን ጨምሮ፣ የዚህን አይነት አሰራር እንዲኖር በህጋቸው ይጠይቃሉ (ስሞለርና ሌሎች 2006 ዓ.ም፡53)፡፡

---

16 የዓለም የፋይናንስ ድርጅት የስኬት መለኪያ አንቀጽ 29 ግልጽ መሆን ያለባቸውን መረጃዎች ይገልጻል፤

17 በአጋር አካላት መካከል ያለው ግንኙነት አስፈላነት በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮርፖሬሽን የአፈጻጸም ደረጃ የሚያመለክት የማያቋርጥ የሪፖርት ግነኙነት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ሊቀርብ ይገባል፡፡ የዓለም አቀፍ የፋይነንስ ኮርፖሬሽን የአፈጻጸም ደረጃ ይመልከቱ 1፤ ክፍል 36፤

ኢንቨስተሮች እና ኦፕሬተሮች ኢንቬስትመንቶቻቸው በመሬት ይዞታና በሰብአዊ መብቶች ላይ ስላሳረፋቸው ተፅዕኖዎች በየዓመቱ ማሣወቅ ከቻሉ የግልፀኝነት አሰራርን ሊያጎለብት ይችላል፡፡ አበዳሪዎች ለምሣሌ የኢኩዌተር መርሆዎች (መርህ 8)፣ እንደዚሁም ሌሎች ኢንቬስተሮች ወይም የኢንቬስተሩ የትውልድ አገር እንኳን ሳይቀር፣ የዚህ አይነቱን ዘገባ ብዙ ግዜ ይፈልጋሉ፡፡[18] በመሬት ላይ እራሳቸው በቀጥታ ኢንቨስት የሚያደርጉ ኢንቬስተሮች በመደበኛነት ሪፓርት ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሲሆን በቀጥተኛ መንገድ የማይሣተፉ ኢንቬስተሮችም ቢሆኑ እነሱ ኢንቬስት የሚያደርጉባቸውን እንደዚያ እንዲያደርጉ መገፋፋት አለባቸው፡፡ ዘገባን ማቅረብ የሚለው አስተሳሰብ ፕሮጀክቶች በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያደርሷቸውን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን እና እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ጭምር በግልፅ ማሣወቅ እንዳለባቸው ከሚደነግገው ከተባበሩት መንግስታት የንግድ እና ሰብአዊ መብቶች አበይት መርሆዎች ውስጥ ከተካተቱት መመሪያዎችጋር የሚጣጣም ነው (ዊካሬ እና ካልሆን፣ 2002 ዓ.ም፡26)፡፡ የዓፋድም ደንበኞች በአካባቢና ማህበራዊ ዘለቄታዊነት ላይ ያላቸው አቋም የሚገልፁ ዘገባዎችን እንዲያቀርቡ ያበረታታል (ዓፋድ 2004 ዓ.ም፤ የአፈፃፀም መስፈርት1፣ አንቀፅ 34)፡፡

ኢንቬስት ሊያደርጉባቸው በሚችሉባቸው አገሮች ውስጥ ስላለው የሙስና ሁኔታ ራሳቸውን የሚያስተምሩ ኢንቬስተሮች፣ ግልፀኝነትን የሚያራምዱ፣ በማንኛውም የሙስና ተግባራት ውስጥ መሣተፍን የሚያግዱ፣ በቅንጅት አስተዳደር ክንውኖችን የሚከተሉና የሚተገብሩ ኢንቬስተሮች በእርሻ መሬት ላይ በሚያደርጉት ኢንቬስትመንቶች ላይ ሙስና የሚጋረጥባቸውን አደጋዎች በሚገባ በመቆጣጠር ረገድ ብዙ ርቀት ሊሄዱ ይችላሉ፡፡

ሣጥን 11፡- የግልፀኝነትና የሙስና መቆጣጠሪያ ዝርዝር

- ✓ በመሬት ላይ በሚደረጉ ኢንቬስትመንቶች ጋር ተያይዞ የሚፈፀም ሙስና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ጐጂ ነው፡፡ በሙስና ድረጊቶች በመሳተፍ፣ ኢንቬስተሮችን በወንጀል ድርጊቶች ተጠያቂነትና ለከፍተኛ ፕሮጀክት ወጭ ሊዳርጋቸው ይችላል፡፡
- ✓ ሙስና የሚጋርጠውን አደጋ ለማስተናገደ ኢንቬስተሮች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-
  - o በአገር ውስጥ ኢንቬስትመንት ሊደረግ በታሰበበት አካባቢ ሙስና የሚገኝበትን ደረጃ ማወቅ፣ እና
  - o ግልለፀኝነትና `ለሙስና ምንም ትዕግስት አይኖርም' የሚል አቋም የሚያራምዱ መምሪያዎችንና አሰራሮችን መንደፍና መተግበር፣ እንደዚሁም ኢንቬስት የሚያደርጉባቸው ፕሮጀክቶች ተመሣሣዩን እንዲያደርጉ መገፋፋት አለባቸው፡፡
- ✓ ሙስና ፈፅሞ እንዳይኖር ለማድረግ የሚነደፉ ፓሊሲዎች (መመሪያዎች፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቶችን በመቀየስ፣ አስገዳጅነት የሚኖራቸው የቁጥጥር መርህ ግብሮችን ጨምሮ፣ በመጠቀም እንዲተገበሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የግልፀኝነት አሰራር መኖር ህዝቡ በፕሮጀክቱ ላይ ተቃውሞ ሊየነሳ የሚችልበትን አጋጣሚ ያስንሳዋል፡፡ የግልፀኝነት መታጣት ደግሞ ተቃራኒውን ውጤት ሊያመጣ ይችላል፡፡
- ✓ ግልፀኝነት ባለድርሻ አካላትን የማሣተፍ፣ የማማከርና ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙነት የመመስረት ሂደት አስፈላጊ አካል መሆን አለበት፡፡
- ✓ ኢንቬስተሮች ከግብይይት ጋር የሚገናኝ መረጃ በሙሉ፣ ጥቅም ላይ ቢውል ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ከሚባል በስተቀር፣ ለህዝቡ የሚደርስ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
- ✓ ውሎች፣ በተለይም ሰፋፊ መሬቶችን የሚመለከቱት፣ የግድ በሚስጥር መያዝ ያለባቸውን ሳይጨምር ህዝቡ እንዲያውቃቸው መደረግ አለበት፡፡

[18] ምሳሌ በዴንማርክ የዳኒሽ ካምፓኒ በየዓመቱ ሪፖረት እንዲያቀርብ ይደረጋል፤ የሰብዓዊ መብት አያያዝ ከአየር ንብርት ለውጥ ጋር በተያያዘ፡፡ የደንማርክን መንግስት 2014፡6 ማየት ይቻላል፡፡

# 6

# የምግብ ዋስትና፣ ሰብዓዊ መብቶች፣ አካባቢ እና ዘለቄታዊነት

## የወካይ ምልክቶች አጠቃቀም

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

በርካታ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች መኖር ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በኢንቬስትመንቱ መግፋት እንደሌለበት ሊያነሳሰው ይገባል፡፡

### መካከለኛ የአደጋ መንስኤዎች

ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በተገቢ ዝግጅት ምዕራፍ ላይ ፕሮጀክቱን በድጋሚ በመፈተሽና አደጋዎችን የማቃለያ መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# 6. የምግብ ዋስትና፣ሰብዓዊ መብቶች፣አካባቢና ዘለቄታዊነት

መመሪያዎቹ ለኢንቬስተሮች፣ ለኦፕሬተሮችና በመሬት ላይ የተመሰረቱ የግብርና ኢንቨስትመንቶች በሚካሄዱበት አካባቢ ለሚገኙ ነዋሪዎች በርካታ ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ፡፡ በዚህ መዕራፍ ውስጥም ተገቢ ጥረትና የአደጋ ቁጥጥር ከእነዚያ ጉዳዮች ውስጥ ለሦስቱ ለምግብ ዋስትና፣ ሰብአዊ መብቶችና ለአካባቢ ጥበቃ የሚኖራቸውን እንድምታዎች ተብራርተዋል፡፡

## ሀ. የምግብ ዋስትና

### 1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

የምግብ ዋስትናን ለሁሉም ማረጋገጥ የመመሪያዎቹ ዓላማ ነው፡፡ በህትመቱ መቅድም ውስጥ እንደተገለፀው በመመሪያዎቹ ትኩረት የተሰጠው የምግብ ዋስትናን ለሁሉም ማረጋገጥ፣ ለሚለው መሰረታዊ ግብ ስኬታማነትና በቂ ምግብ የማግኘት መብትን በሂደት ማረጋገጥ የሚቻልበትን መንገድ ለማመልከት ነው፡፡

መመሪያዎቹ፣ "ኃላፊነት የተላበሱ የመንግሥትና የግል ኢንቨስትመንቶች የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል አስፈላጊ መሆናቸውን" (አንቀፅ 12.1) እና ኃላፊነት የተላበሱ ኢንቨስትመንቶችም ለዚሁ ስኬት የበኩላቸውን ጥረት በንቃት መወጣት እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ (12.4)፡፡ በአብዛኛው የዓለም ክፍል ውስጥ የትናንሽ እርሻ ባለይዞታዎች የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ ለማድረግ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ በመሆኑ፣ ለእነሱ ድጋፍ መስጠት ስለሚኖረው ጠቀሜታ በመመሪያዎቹ ትኩረት ተሰጥቶታል(12.2)፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ኢንቬስትመንቶቻቸው "ለምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ለኢንቬስተሮች ማሳሰብያ ተሰጥቷል" (12.12፡መርህ 1)፡፡ ከዚህም ባሻገር የዓለም አቀፉ ኢካኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት፣ አንቀፅ 11፣ በቂ ምግብ ማግኘት ሰብአዊ መብት መሆኑን ያትታል፡፡ ታድያ ይህንን ስምምነት በራስ ፈቃድ መጣስ ለኢንቬስተሮች አደጋ ሊኖረው ይችላል፡፡

### 2. አደጋው ምንድ ነው?

በሚገባ የተቀረፁ የግብርና ኢንቨስትመንቶች፣ የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ማሻሻል ይችላሉ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በዘፈቀደ የተነደፉ ፕሮጀክቶች በተለይም ትናንሽ ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የምግብ ፍጆታ ምንጭ የሆናቸውን መሬት የሚያሳጧቸው ከሆነ የሚኖራቸው ውጤት ከዚህ በተቃራኒ ሊሆን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ፣ ፕሮጀክቱ የዓርብቶ አደር ማህበረሰቦች በወቅታዊነት በጋራ የሚጠቀሙባቸውን ቦታዎች ወይም የአካባቢው ነዋሪዎች፣ ብዙ ጊዜ ሴቶች፣ እንደ ለውዝ ወይም ፍራፍሬዎች ያሉትን ግንባታ-ነክ ያልኑ የደን ውጤቶች የሚሰበስቡባቸውን ደናማ የጋራ የተፈጥሮ መብቶች መገኛ የሆኑ ስፍራዎችን የማይዝ ከሆነ በምግብ

ዋስትና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ተፅዕኖዎች በብዙ መንስኤዎች ሊከስቱ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ፣ ለአካባቢው ኗሪዎች አዳዲስ ሰብሎችን ማስተዋወቅ፣ የምግብ ሰብሎችን ለገበያ ተብለው በሚመረቱ ሰብሎች መተካት፣ የዓሣ ሀብት፣ የደኖች ወይም የውሀ አቅርቦትን መቀነስና ምግብ ለውጭ ገበያ ወደ መላክ በማዘንበል ሣብያ የምግብ ዋጋ ጭማሪ መከሰትን ይጨምራል (ሰሞላርና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም፣ ዴ ሹተር 2001 ዓ.ም፡3)

የአካባቢ ነዋሪዎችን የምግብ ወይም የውሃ አቅርቦትን ሥጋት ላይ የሚጥል በመሬት ላይ የተመሰረተ ኢንቨስትመንት ጠንካራ ተቃውሞ የሚያነሳሳ በመሆኑ ኢንቬስትመንቱን ለከፍተኛ አደጋ ሊዳርገው ይችላል (መንዴን ፕሮጀክት፣2006 ዓ.ም፡6-7)፡፡ በተጨማሪም ለውጭ ገበያ ብለው ምግብ የሚያመርቱ ኢንቬስተሮች፣ ፕሮጀክታቸው (ምናልባትም ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በማበር) በምግብ ዋስትና ላይ ስጋት ማሳደር ከቻለ፣ እገዳ ሊጣልባቸው ይቻላል፡፡ አንድ ኢንቬስትመንት ለምግብ መግዢያነት የሚሆን ክፍያ መፍጠር ከቻለ፣ በምግብ አቅርቦት ላይ አወንታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ዳሩ ግን የግብርና ስራ የሰው ኀይል የሚፈልገው በወቅታዊነት ስለሆነ ክፍያዎቹ ለኢንቬስትመንቱ ፕሮጀክቱ ከተላለፈው መሬት ላይ ለህይወታቸው ማቆያ ከእርሻ በፊት ያገኙ የነበረውን የምግብ ፍጆታ ሙሉ በሙሉ ሊተካ የሚችል ምግብ መግዛት አያስችልም (ሚርዛና ሌሎች 2006 ዓ.ም፡27-28)፡፡ ይህን መሰል ሁኔታ ደግሞ በተለይም ብዙ ጊዜ የቤተሰብ ምግብ የማቅረብ ኃላፊነት ተሸካሚ ለሆኑት ሴቶች ጎጂ ሊሆን ይችላል፡፡ አስተማማኝ ዘለቄታዊነት ያለው ፕሮጀክትም እንኳን ቢሆን ተጠቃሚዎችን ብቻ ሣይሆን ተጎጂዎችንም ጭምር ሊፈጥር ይችላላ፡፡

## 3. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና ማቃለል ይቻላል?

ከምግብ ዋስትና ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዩች፣ በአካባቢው ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን መለያ የሆነውና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የማስወገጃ መንገዶችን የሚጠቀመው የአጠቃላይ አካባቢና ማህበረሰባዊ ተፅዕኖ ግምገማ (አማተግ) አካል ተደርገው መውሰድ አለባቸው፡፡ የፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ከፍተኛ የሚሆን ከሆነ ኢንቬስትመንቱ መቀጠል አይኖርበትም (ስሞለርና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም ፡ 16)፡፡ በአሁኑ ግዜ ዓፋድ ፕሮጀክቱ የሚካሄደው የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠበት አገር ውስጥ ከሆነ፣ ማንኛውም ኢንቬስትመንት ከታሰበው ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የምግብ ዋስትና የመነሻ ዳሰሳ ጥናት እንዲኖር ወይም ቀደም ብሎ መደረግ ያለበት መሆኑን ይጠይቃል(ዓፋድ፣2006 ዓ.ም)፡፡ የግብርና ኢንቬስትመንቶች የምግብ ዋሰትናን የሚጐዳ ነገር በፍፁም ማድረግ የላባቸውም፡፡ አንዱ ስልት ደግሞ የአካባቢው ገበሬዎች ህይወታቸውን ለማቆያ የሚጠቀሙባቸውን የእርሻ ማሳዎቻቸው በይዞታ ስር የሚቆዩ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ፣ በቤተሰብ አኗኗር ላይ መመሰቃቀልን የሚያስከትል ወይም የዚያን አይነቱን አጋጣሚ ማሳነስ በሚችል መልኩ፤ ማለትም በቅርበት ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ቁራሽ መሬት በአማራጭነት መስጠት ነው፡፡ ሌላኛው መንገድ በፕሮጀክቱ ተመርቶ ወደ ውጪ በሚላከው ምግብ ሳቢያ በአካባቢው ለሚገኙ ገበያዎች በሚቀርበው የምግብ መጠን ወይም ዋጋ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው አለመቻሉን የዳሰሳ ጥናት ማድረግ ነው(ዴ ሹተር፤2001 ዓ.ም)፡፡

ምክንያታዊ ኢንቬስተሮች፣ የተሻሻለ የምግብ ዋስትና መኖር ያለበት ስለመሆኑ በመመሪያቹ በተገለፀው መሰረት በተለይም የምግብ ዋስትናቸውን ባላረጋገጡ ክልልሎች ውስጥ፣ ምክንያታዊ ኢንቬስተሮች "ጉዳት አታድርስ" ከሚለው መርህ ባሻገር መሄድ ይችላሉ (አንቀፅ 12.4)፡፡ ስልቶች የምግብ ፍጆታ በተሻለ ደረጃ መኖሩን፣ ማግኘትን፣ አስተማማኝ አቅርቦት ወይም አጠቃቀም መኖርን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ከስልቶቹ ውስጥ የተወሰኑት የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

- ፕሮጀክቱ በሚካሄድበት ስፍራ ወይም አቅራቢያ፣ ለአካባቢው ነዋሪች የምግብ ፍጆታ ማምረቻነት የሚውል መሬት መተው (ባዘማስ፣መስፈርት 6ለ)፤
- የአካባቢው ገበሬዎች የእርሻዎቻቸውን ምርታማነት ማሻሻል እንዲችሉ ዘለቄታዊነት ስለሚኖረው የግብርና ስራ ስልጠናና ሌሎች ሙያዊ ድጋፎችን መስጠት፤
- በአካባቢው የሚገኙ ገበያዎችን ተደራሽነት ማሳደግ፤
- ገበያዎች ለገበሬዎች ከፍተኛ ተደራሽነት እንዲኖራቸው ለማመቻቸት የገጠር መሰረተ ልማቶችን ማሻሻል፤
- በአመጋገብ ስርዓት ላይ ለአካባቢው ነዋሪዎች ስልጠና መስጠት፤

- ለአካባቢው ገበሬዎች እሴት የተጨመረባቸው የምግብ ተዋፅኦች አቅራቦት እንዲኖር ማድረግ (ባዝማሥ፣ መስፈርት 6ለ)፤
- ውጫዊ አንቀሳቃሽ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ማዋል(ምዕራፍ 2ን ይመልከቱ)፤ ወይም መሬት በአካባቢው ገበሬዎች ስር ሊቆዩ የሚችልበትን አሰራር መከተልና፣ በቤተሰብ የሚያዙ ትናንሽ እርሻዎች፣ በተለይም ከፍተኛ የሰው ኃይል በሚያስፈልገባቸው ቦታዎች በስፋት የሚካሄዱ እርሻዎች ይልቅ አብዛኛውን ግዜ የበለጠ ምርታማ ናቸው የሚለውን አስተሳሰብ ማራመድ፤[19]
- የአካባቢው ገበሬዎች የብድር አገልግሎት በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ማድረግ፤

"ምርታማነትን በማሣደግና የአካባቢውን ገበሬዎች ተጠቃሚ በማድረግ የአካባቢውን የምግብ ዋስትና ማሻሻል የሚችሉና፤ እግረ መንገዳቸውንም በገጠር አካባቢዎች የገቢያቸውን አለመመጣጠን ማስወገድ የሚችሉት (ዴሹተር፤ 2001 ዓ.ም፡8-9) የግብርና ኢንቬስትመንቶች፣ ከምግብ ዋስትና ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን አደጋዎችን በአግባቡ ማስተናገድ የሚችሉቱ ናቸው፡፡

ሣጥን 12፡-
የምግብ ዋስትና
መስፈርት ዝርዝር

የግብርና ኢንቬስትመንቶች፣ ፕሮጀክቱ ለህይወታቸው ማቆያ የሚሆናቸውን ምግብ ያመርቱበት የነበረውን መሬት እንዲያጡ ካደረጋቸው በአካባቢዉ ነዋሪዎች የምግብ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ ይችላሉ፡፡ ይህ ክስተትም ጠንካራ ተቃውሞ ወደማንሳት ሊገፋፋቸውና ብሎም ኢንቬስትመንቱን ለብርቱ አደጋ ሊያጋልጠው ይችላል፡፡

- ✓ አደጋዎችን የመለየትና በአግባቡ የማስተናገድ ስራ፣ የአማተግ የሆነው በአካባቢው ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን የመለያ አጠቃላይ ሂደት ውስጥ መካተት አለበት፡፡
- ✓ ምክንያታዊ ኢንቬስተሮች "ጉዳት አታደርስ" ከሚለው መርህ በላይ በመሄድ፣ በምግብ መገኘት፣ አስተማማኝ በሆነ አቅራቦት ወይም የምግብ አጠቃቀምን ለማሻሻል የሚረዱ ስልቶችን በመጠቀም የምግብ ዋስትናን ማሳደግ ይችላሉ፡፡

# ለ. ሰብዓዊ መብቶች

## 1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

መመሪያዎቹ ኢንቬስተሮችና የንግድ ተቋማት ሰብአዊ መብቶችን የማክበርና ጥሰት እንዳይደርስ የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑንና በእነዚህ መብቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖቻችን መለየት፣ መገምገምና ብሎም መፍትሄ መስጠት ያለባቸው መሆኑን ይጠቁማሉ (አንቀፅ 3.2) ፡፡ አንድ ኢንቨስትመንት ኃላፊነት የተላበሰ ነው ሊባል የሚችለው "ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብርና ጉዳትም የማያደርስ" ሲሆን ነው (አንቀፅ 12.4)፡፡

በአጠቃላይ አነጋገር፣ ሰብአዊ መብቶች በርካታ መብቶችን፡- ማለትም የዜግነት፣ ባህላዊ፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊና ማህበራዊ መብቶች ያሉትን ያካትታሉ፡፡ ምንም እንኳን መመሪያዎቹ ተግባራዊነት ያላቸው የሰብዓዊ መብቶችን በተሟላ መልኩ የማያቀርቡ ቢሆንም፣ ምልከታ የተደረገባቸው አለም አቀፋዊ ስምምነቶች፣ የሚከተሉት ጭምር፣ ቀርበዋል፡-

- የዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ (አንቀፅ 1.2)

[19] ዲ.ስሁተር፤ 2009 8-9 ይበልጥ ትኩረት የሚሻው የሴቶች መሬት ይዞታቸውን ሲያጡ የሚደርሰው ተጽእኖ ላይ ይሆናል፡፡

- ነፃ በሆኑ አገሮች ውስጥ የነባር ተወላጆችንና ጐሣን መሰረት ያደረጉ ህዝቦችን የሚመለከተው የዓለድ ስምምነት (አንቀፅ 9.3)፣
- የብዝሀ ሀብት ስምምነት (አንቀፅ 9.3)፤ [20]
- የነባር ተወላጆች ህዝቦችን መብት በተመለከተ የተባበሩት መንግስታት ድንጋጌ (አንቀፅ 9.3)፣
- በአጠቃላይ አነጋገር ለኢንቬስተሮች የላቀ አስፈላጊነት ያላቸው የሰብአዊ መብቶች ማዕቀፍ፣ ንግድና ሰብዓዊ መብቶችን (በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ዘግየት ብሎ የተመለከቱት) የሚመለከቱት የተባበሩት መንግስታት አበይት መርሆዎች ናቸው፡፡

## 2. አደጋው ምንድን ነው?

ፕሮጀክቱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ከደረሰ ለኢንቬስተሮች በከፊል አደጋ የሚሆነው ህጋዊ ወይም ይባስ ብሎ በወንጀል ድርጊት ተጠያቂነትን ሊያስከትልባቸው የሚችል መሆኑ ነው፡-

“ ከህጋዊነት አንጻር የብዙ ሃገራት ህጎች በወንጀል ድርጊት ተሳትፎን አጥብቀው ይከለክላሉ፡፡ የተወሰኑት ሃገራት የንግድ ድርጅቶች በወንጀል ህግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ደንግገዋል፡፡ በተለይም የፍትሐብሄር ክስ የሚመሠረተው አንድ ድርጅት አድርሷል የተባለውን ጉዳት መሰረት በማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ግን እንደ ሰብአዊ መብት ጥሰት ተደርጎ ባይቀርብም፡፡ በአመዛኙ የአለም አቀፍ የወንጀል ህግ የሚያመለክተው አንድ አካል የወንጀል ድርጊት ተባባሪ ነው ለማለት ሆን ብሎ በቀጥታ ለወንጀሉ ፈጻሚዎች ድጋፍ ሲያደርግና ሲያበረታታ ይህም በወንጀሉ አፈጻጸም ላይ የጎላ አስተዋጽኦ ሲኖረው ነው፡፡(OHCHR, 2011: 20).

በዚህ መምሪያ ውስጥ እንደተዳሰሱት ሌሎች ጉዳዩች ሁሉ፣ በሰብአዊ መብቶች ላይ በሚደርሱ ጥሰቶች ሣቢያ ሊቀሰቀስ የሚችል ተቃውሞ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ኪሣራ ሊያስከትል ይችላል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች መብቶች ከተሟሉና፣ በተለይም ይህ ክስተት ለጉስቁልና፣ ለመፈናቀል አለበለዚያም አካላዊ ወይም የገንዘብ ጉዳት ከደረሰባቸው፤ በፕሮጀክት የገንዘብ አቅም ላይ ሊደርስ የሚችለው ውድቀት ከፍተኛ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ እንደዚሁም በስብአዊ መብቶች ላይ የሚፈፀም ጥሰት፣ ፕሮጀክቶች የተወሰኑትን የሸቀጣ ሸቀጦች ዘለቄታዊነት ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት (ሸዘማአሥ፡ 2005 ዓ.ም፣ መርህ 4)የቀጣይነት ማረጋገጫ ከማግኘት ሊያግዳቸው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሰብአዊ መብቶች በመላ የማይነጣጠሉ፤ የተቆራኙና የሚደጋገፉ መሆናቸውን ማስታወሱ ጠቃሚ የሚሆን ሲሆን፣ ኢንቬስተሮችም አንዱን ከሌላው ነጥለው መመልከት አይኖርባቸውም፡፡

ምንም እንኳን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅ መሬት የማግኘት ሰብአዊ መብት የሌለ ቢሆንም፣ ለነባር ህዝቦች በዓለድ ስምምነት፣ ውስጥ ከተቀሰው ሌላ፡ የሌለ ቢሆንም በቂ ምግብና መጠለያ የማግኘት መብቶችን እውን የማድረግ መሰረታዊ አካል ተደርጐ መወሰድ አለበት፡፡ መሬት ነክ ጉዳዮች አብዛኛውን ግዜ የሚሰተናገዱት በብሔራዊ ሕግ ነው፡፡ ሆኖም ቢያንስ ቢያንስ ሁለት አስፈላጊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ህግ መሳሪያዎች መሬትንም ይመለከታሉ፡፡ በቂ ምግብ የማግኘት መብትን በተመለከተ የዓለም አቀፉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት(ኢማባመስ)፡- እና በገጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች መብቶችን የሚመለከተው (ተመለየች፣1971 ዓ.ም) ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ አድሎአዊነቶችን በሙሉ የማስወገድ ስምምነት (ሴአበማስ) ናቸው፡፡ የተመ የንግድና የሰብአዊ መብቶች አበይት መርሆዎች የመሬት መብትን እውቅና የማይሰጡ ወይም የማያካትቱ ቢሆንም፡ የሚከተለውን ያትታሉ፡-

የንግድ ድርጅቶች የሰብአዊ መብቶች የማክበር ኃላፊነት ሲባል በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው ሰብአዊ መብቶች ማለትም በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች እና በአለም የሥራ ድርጅት መሠረታዊ መርሆዎች እና የሥራ ቦታ መብቶች ድንጋጌ (አንቀጽ 4) ውስጥ የተገለጹትን መሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች የተመለከቱትን መርሆዎችን ማክበር ይመለከታል፡፡ ”

[20] የስነምህዳር ስምምነት የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ባይሆንም በይልጥ ነባር ህዝቦች በመመሪያው ላይ ግን የተመለከተው ነው፡፡

በመሬት መብቶችና በሰብአዊ መብቶች መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ጥልቀት ያለው ዳሰሳ ማድረግ ከዚህ መምሪያ አድማስ ውጪ ነው፡፡21 በአጭሩ ግን አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች ሲባል የዓለም አቀፉን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እና ሁለት ማስፈፀሚያ ስምምነቶችን ይዟል፡- እነሱም የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች (አሰመስ) እና የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት (የኢማባመስ) ናቸው፡፡ ህዝባዊና ፓለቲካዊ የዓህፓመስ "ቁሳዊና መንፈሳዊ መብትን የመጠቀም መብት፣ ሚዛናዊ መስተንግዶ ማግኘትና በፓለቲካ ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ማድረግ"፡፡[21] (የካስተን የሰብአዊ መብቶች ተቋምና ሌሎች፣ 2002 ዓ.ም፣3) እና ሃሣብን በነፃ የመግለጽ መብትን፣ በማህበር የመደራጀትንና የመሰብሰብ መብቶችን ይይዛል፡፡ በኘሮጀክት ላይ የሚቀሰቀሱ ተቃውሞዎች ከታፈኑና ተቃዋሚዎችም ዛቻ ከደረሳቸው ወይም ከታሰሩ፣ ኦኘሬተሮቹ ራሳቸውን በእነዚህ የመብት ጥሰቶች ውስጥ ተዘፍቀው ሊያገኙት ይችላሉ፡፡

በዓኢማገመሥ ስር ጥበቃ የሚደርግላቸው መብቶች በርካታ የሠራተኛ መብቶችንና እንዲያውም በባህላዊ ህይወት እርካታ የማግኘትና የመሳተፍ ነፃነትንና አጥጋቢ የሆነ ኑሮ ደረጃ የመምራት፣ መጠለያና በቂ ምግብ የማግኘት መብትን ጭምር ያካትታል፡፡ የግሉ ዘርፍ የንግድ ተቋማትም እነዚህን መብቶች የማክበር ግዴታ አለባቸው (የካስተን የሰብአዊ መብቶች ማዕከል ህግና ሌሎች፣ 2009 ዓ.ም፡3) ፡፡

ለማጠቃለል ያህል፣ የመሬት በኢንቬስተሮች በመያዝ ሳቢያ፣ በተለይም መንግስት በካሣ ወይም ያለካሳ ክፍያ ነዋሪዎችን በማፈናቀል መሬት ለኢንቬስተሮች በሚያስተላልፍባቸው አካባቢዎች፣ የሚከሰቱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ማለትም በምግብና በቂ መጠለያ የማግኘት መብቶች ላይ የሚደርስ ጥሰት ጭምር፣ ኢንቬስተሮችን ለበርካታ አደጋዎች ያጋልጧቸዋል፡፡ በዚያ መንገድ በሚወስዱ ይዞታዎች ሳብያ ተሳታፊ የሚሆኑ የንግድ ተቋማት ባለቤቶች ለአስከፊ አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ ይኸውም "በዚያ ሰበብ የሚቀሰቀሱ ተቃውሞዎች እና የሕግ ክርክሮች በጥቅሞቻቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ፣ የመልካም ስምና ህግ-ነክ ጉዳት ያስከትሉባቸዋል (IHRB፡ 40)፡፡ በአህጉራዊ የሰብአዊ መብት ፍርድ ቤቶች ሙግት ውስጥ መግባት የጉዳቶቹ ሌሎች ገፅታዎች ናቸው፡፡

ሣጥን 13፡-
የመሬት ይዞታ
መብቶች የአደጋ
መንስኤዎች

**ከፍተኛ አደጋ**

- መሬትን አስመልክቶ ሊፈቱ ያልቻሉ ብዛት ያላቸው ቆየት ያሉና በቅርብ ግዜ የተፈጠሩ ክርክሮች ወይም የባለይዞታነት ጥያቄዎች አሉ፣ አብዛኛውን ግዜ ሊከሰት የሚችለው መሬት በሚያዝበት፣ በሚቀላቀልበት፣ ወይም ቀጣይነት ያለው 'ብራውን ፊልድ' ኢንቬስትመንት (መሬት ለሽያጭ በማይውልበት ወይም ለሌሎች የንግድ ጠቀሜታዎች በሚውልበት የ 'ግሪን ፊልድ' በተቃራኒው የሚደረግበት ሁኔታ ሲኖር ነው፡፡
- መንግስት መሬቱን ቀደም ባለ ግዜ ወይ በማስለቀቅ፣ አልያም ኘሮጀክቱ መሬቱ ለልማት ስራ ለማዋል መንግስት መሬቱን እንዲለቀቅ በመፈለጉ ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች ተፈናቅለዋል፡፡
- የኘሮጀክቱ ቀረፃ የአካባቢው ነዋሪዎች የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን በከፍተኛ መጠን እንዲያስተላልፍ የሚጠይቅ በመሆኑ ሳብያ ሰዎች ያለፈቃዳቸው ወይም በፍቃደኝነትም ሊሆን ይችላል፣ ሌላ ቦታ እንዲሰፍሩ ተደርገዋል፡፡
- ኦኘሬተሩ ወይም ቀጥተኛው ኢንቬስተር የሚከተሉትን ነገሮች ያላደረገና ወደፊትም የማያደርግ ይሆናል፡-*
    - o አሣታፊ የሆነ የባለድርሻ አካላት የመለያ ስራ፣
    - o በመሬት ላይ የሚደርስ ተፅዕኖ ግምገማ (ምናልባትም የተሟላ የአማተግ አካል ተደርጐ) ፣
    - o ከማህበረሰቡ ጋር ተከታታይ ምክክሮች

**መካከለኛ አደጋ**

- - በኘሮጀክቱ የተያዘው የመሬት መጠን በኘሮጀክቱ መላ የቆይታ ግዜ ውስጥ ለምርት ስራ ያስፈልጋል ከሚባለው በላይ ከሆነ ኘሮጀክቱ ድብቅ አጀንዳ ቢኖረው ነው የማል ጥርጣሬ ሊያሳድር ይችላል፡፡
- - ኘሮጀክቱ የሚካሄደው የመሬት ይዞታ መብቶች ተመዝግበው ባልተያዙበት ወይም/ እና የሚስተናገዱበትም በኢ-መደበኛ ህግ በመሆኑ መብቶች ያሏቸውን ባለይዞታዎች ለማወቅ የመለያ ስራ ገና መስራት ያለበት ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡
- - ሊካሄድ የታሰበው ኘሮጀክት የአማተግ፣ በመሬት ይዞታ፣ በፆታ፣ በምግብ ዋስትናና በሰብአዊ መብች ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ተፅዕኖዎች ግምገማ ጭምር፣ በገልተኛ አካል ገና አልተጠናቀቀም፡፡
- - በገለልተኛ የአማተግ በተጠቆመው መሰረት ኘሮጀክቱ ላይ ክለሳ ያልተደረገ ከሆነ፣ የአማተግ በመሬት መብቶች፣ በምግብ ዋስትና፣ በፆታና በሰብአዊ መብቶች ላይ ከበድ ያሉ ጉዳቶች መድረሳቸው የማይቀር መሆኑን ሊያሳይ ይችላል፡፡

21 ለበለጠና ጥልቀት ላለው የመሬት መጠቀም መብት ምልከታ ኮቱላ(2014) እና ዊክሪ እና ካላሃን (2010) ማየት ይቻላል፡፡

## 3. ጉዳትን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖች ምክንያት የሚከሰቱ አደጋዎች (በዚህ መምሪያ ውስጥ በመላ እንደተገለፀው ሁሉ) የአጠቃላይ የተገቢ ዝግጅት ሂደት አካል ተደርገው ሊስተናገዱ ይችላሉ። ይኸውም የአጠቃላይ የአካባቢያዊ ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ (አማተግ) ከተቻለ በሰብአዊ መብቶች ላይ በተጨባጭ እየደረሱ ያሉና ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን በመገምገምና ተፅዕኖዎቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዳ እቅድ ማስቀመጥ ይኖርበታል። እንደዚያ ማድረግ ካልተቻለ ኢንቬስትመንቱ በጣም አደገኛ እንደሆነ መወሰድ አለበት(ተመሰመከመቢ፣ 2003 ዓ.ም፡18-21፣ USAID፣ 2007 ዓ.ም ለ፡17)። በእርግጥ ለአንድ ኢንቬስተር የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃን በመላ የንግድ እንቅስቃሴዎቹ ውስጥ ሊያካትትና እነደዚሁም ኢንቬስት የሚያደርግባቸው ሌሎች የንግድ ስራዎችም ተመሣሣይ አቋም እንዲይዙ ቢገፋፉ ብልህነት ይሆናል። ይኸውም በተመሰመከመቢ (2003 ዓ.ም) መሰረት፣ ሂደቱ የንግድ ተቋሙ ሰብዓዊ መብቶችን ለማክበር ያለውን ቁርጠኝነት የሚያንፀባርቁ የውስጥ ፓሊሲዎችን በመቅረፅና ለህዝብ ይፋ በማድረግ ነው።

ይህ ከንውን የንግድ ተቋሙ የሚያካሂዳቸው ኢንቬስትሜንቶች የሰብአዊ መብቶች ጥሰትን የሚደርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ወደሚያስችል የሰብአዊ መብቶች ቀረፃና ትግበራ ተገቢ ጥረት መሸጋገር ይኖርበታል። ፖሊሲውም ቀጣይነት ያለው የቁጥጥርና መረጃ አያያዝ፣ እና ብዙ ግዜ ደግሞ ኢንቬስትመንቱ ያደረሰውን ተፅዕኖ ይፋ ማድረግንና እንደዚሁም በኢንቬስትመንቱ መላ  የቆይታ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ፣ ቅድመ ትኩረት ያልተሰጣቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ማስተናገድ የሚቻልበትን መንገድ ጭምር ማካተት አለበት (ተመሰመከመቢ፣ 2003 ዓ.ም፡24)። ኢንቬስተሮች ኢንቬስት (ገንዘባቸውን ያፈሰሱባቸው የንግድ ተቋማት ወይም ፕሮጀክቶች ላይ የሰብዐዊ መብቶች ረገጣ ስለማድረሣቸው በመያድቶችና በሌሎች ዘገባዎች የሚቀርቡ ማናቸውንም ውንጀላዎች ኢንቬስተሮቹ ከፍተኛ አትኩሮት በመስጠት ቁጥጥርና ምርመራ ማድረግ፣ እውነት ሆኖ ከተገኘ ደግሞ የእርምት ርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።

በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚደርሱ ጥሰቶችን ለይቶ ማወቅ፣ መገምገም፣ ማስወገድ ወይም መፍትሄ መስጠት ውስብሰብና አሰቸጋሪ ስራ ነው። ስለዚህ ብዙ ግዜ በዚህ ሂደት ውስጥ እገዛ ማድረግ የሚችሉ ባለሙያዎችን መጠቀም ኢንቬስተሮችን ሊያስፈልጋቸው ይችል ይሆናል (ተመሰመከመቢ፣ 2003 ዓ.ም፣ USAID፣ 2007 ዓ.ም፣ UNGC፣ 2006 ዓ.ም)።

እንደዚሁም ሁሉ፣ በመመሪያዎቹ (አንቀፅ 3.2 ውሰጥ) እንደተገለፀው፣ በቂ የቅሬታ አፈታት ስርአቶች እንዲኖሩ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

የንግድ ተቋማትንና ሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱት አበይት መርሆች እንደሚያመለክቱት፣ የንግድ ተቋማቱ በሰብአዊ መብቶች ላይ ራሳቸው ለሚያደርሷቸው ወይም (ለመድረሳቸው አባሪ ለሚሆንባቸው ጉዳዮች ምላሽ መስጠት የሚችሉ አሰራሮች እንዲኖሩ መቀየስና ጉዳቶቹም በህጋዊ መንግድና በግልፅ ሊተገበሩ ከሚችሉ የቀሬታ አፈታት መርሆዎች ጋር በማጣመር፣ በግላቸው ወይም ከሌሎች ጋር በመተባበር ተገቢ መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው (ተመሰመከመቢ፣ 2003 ዓ.ም፡- መርህ 25 እና አንቀፅ 32፤ USAID፣ 2007 ዓ.ም ለ50-51)። እንደዚያ ያሉት ስርዓቶች በምዕራፍ 4 ውስጥ ተዳሰዋል።

ሳጥን 14፡-
የሰብዓዊ መብቶች መቆጣጠሪያ ዝርዝር

> አንድ ፕሮጀክት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ሲያደርስ፣ ለኢንቬስተሮች፣ አደጋ የሚሆነው ነገር፣ በከፊል የሚመነጨው በፍትሃብሔር ወይም በወንጀል ተጠያቂ ሊደርጋቸው ስለሚችልና በከፊል ደግሞ፣ እንደዚያ ያሉ ጥሰቶች የአካባቢውን ነዋሪዎች ለተቃውሞ ሊያነሳሱ ስለሚችሉ ነው። የመሬት መያዝ ኢንቬስተሮችንና ኦፕሬተሮችን ለከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ያጋልጣቸዋል።
>
> - ✓ ሰብአዊ መብቶች ላይ በሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ሳቢያ የሚከሰቱ ጉዳቶች፣ በሰብአዊ መብቶች ላይ በተጨባጭ የደረሱና ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን መገምገም ያለበትና፣ ከተቻለ ደግሞ ተፅዕኖዎቹን ወደ ማስወገጃ ወይም ማቅለያ እቅድ ዝግጅት የሚያመራው የአማተግ አካል ተደርገው መስተናገድ አለባቸው። እንደዚያ ማድረግ ካልተቻለ ግን ኢንቬስተሩ በኢንቬስትመንቱ መግፋት የለበትም።
> - ✓ ኢንቬስተሮች የሰብአዊ መብቶችን አጠባበቅን በንግድ ስራዎቻቸው በመላ ውስጥ ማካተትና ኢንቬስት የሚያደርጉላቸው የንግድ ተቋማትም እንደዚያ እንዲያደርጉ ግፊት ማድረግ አለባቸው።

# ሐ. አካባቢና ዘለቄታዊነት

## 1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

በመመሪያዎቹ (አንቀፅ 12.4 እና 12.12) እንደተመለከተው ሁሉ፡ ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስትሜንት ባህሪያት ውስጥ አንደኛው በአካባቢ ሁኔታ ላይ ጉዳት የማያደርስ መሆኑ ነው፡፡መንግስታትም “መሬትን፣ የዓሣ ሀብትንና ደኖችን በዘላቂነት መጠቀምና አካባቢን መጠበቅ የሚቻልበትን ዘዴ ማስተዋወቅ እንዳለባቸው” በመመሪያዎቹ ምክር ተሰጥቷል(አንቀፅ 11.2)፡- በተጨማሪም መመመሪያዎቹ ትናንሽ ይዞታዎች ያላቸው ሰዎች አካባቢን ጠብቆ በማቆየት ረገድ ጠቃሚ ሚና መጫወት የሚችሉ መሆኑን የሚያስገዝንቡ ሲሆን (12.2)፣ መንግስታትም የአየር-ንብረት ለውጥን ያገናዘቡ የመሬት ይዞታ ፓሊሲዎችን እንዲያራምዳና እንደዚሁም በአየር ንብረት ለውጥ መንስኤነት የሚፈጠሩ ክስተቶችን የማቃለያ ስልቶች ሲቀየሱ ተጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖችን በሙሉ በምክክሮችና በትግበራ ላይም ማካተት እንዳለባቸው ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል (ምዕራፍ 23)፡፡

## 2. አደጋው ምንድ ነው?

በአካባቢ ሁኔታ ላይ ሊደርስ በሚችል ጉዳት ሣቢያ ኢንቨስተሮችን ሁለት ትልልቅ ጉዳቶች ያጋጥማቸዋል፡ ፡ አንደኛው በዚሁ መምሪያ ውስጥ ከሌሎች ርዕሶች ጋር ተያይዞ እንደተዳሰሰው ሁሉ፣ በአካባቢ ሁኔታ ላይ ጉዳት መድረስ የሚችል ከሆነ ወይም በተጨባጭ መንግስታት፣ ኢንቬስተሮች፣ ደንበኞችና ለሎች ጭምር በቀላሉ የኢንቬስትመንቱን የገንዘብ አቅም አጣብቂኝ ውስጥ ሊከቱ የሚችሉ የአፀፋ እርምጃዎችን ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ሁለተኛው፣ በአካባቢው ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች መደረጋቸውን ለሚጠይቁ ህጐች ተገዥ አለመሆን፣ ኦፕሬተሮችንና ኢንቬስተሮችን በፍተሐብሔር ወይም በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ከዚህም ጉልህ ሚና የተነሣ በዋከሪና ካልሃን (2002 ዓ.ም ፡7)መሰረት፣ በአካባቢ ሁኔታ ላይ የሚደርስ ጉዳት ሊደርስ ከቻለ ኢንቬስትመንቱ በሚገባ ሊተገበር መቻሉ ላይ ጉልህ አደጋ ይጋርጥበታል፡፡

በማደግ ላይ ከሚገኙ አገሮች ውስጥ አብላጫዎቹ በብዙ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች እንዲያደርጉ ይጠይቃቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የእነዚህ ህጐች አፈፃፀምና የተደረጉት ግምገማዎች የጥራት ደረጃ አንዳንድ ጊዜ ደካማ የነበረ ከመሆኑም በላይ ከግምገማዎቹ ውስጥ ለህዝብ ግልፅ ተደርገው የነበሩት አነስተኛ ቁጥር የላቸው ናቸው (ስሞለረና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም፡25)፡፡ ዳሩ ግን ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው አካባቢ-ነክ መስፈርቶችን በግብርና ኢንቬስትመንቶች ውስጥ ማካተት ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በዓለም-አቀፍ ደረጃ በስፋት መግባባት የተደረሰበት ነገር ነው፡፡ (ዴ ሹተር፣2001 ዓ.ም፡9) አንዳንድ ኢንቬስተሮችና አበዳሪዎች ቀጣይነት ያላቸው አካባቢ-ነክ ክንውኖችን ገንዘብ በእርዳታ ወይም በብድር መስጫነት እንደ ቅድመ-ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡፡ ለምሳሌ ዓገድ፣ EIO እና ባንኮች የኢኳተር መርሆችን የሚከተሉ፡- ዓፋድ፣ EIO እና ባንኮች የግድ መሟላት ያለባቸው አካባቢ-ነክ መስፈርቶች አሏቸው፣ እነዚም ብዙ ግዜ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች መደረግንና ብሎም በግምገማዎቹ ውጤቶች ላይ ተመስርተው መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎችን ጭምር ያካትታሉ(ዓገድ፣2004 ዓ.ም፤ EIB 2005 ዓ.ም፣ የኢኳቶር መርህዎች፣ 2005 ዓ.ም፤ EIB 2005 ዓ.ም፣ )፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አካባቢያዊ ዘለቄታዊነትን ማስጠበቅ በዕርሻ መሬት ላይ የሚደረግ ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስትመንት መመሪያ ዋነኛው አካል ነው (UNGC፤ 2006 ዓ.ም)፡፡ ፈራሚዎችም የኢንቬስትመንት ሥራ አስኪያጆችና ኦፕሬተሮች ጠንካራ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎችን እንዲያደርጉና ተገቢ የቁጥጥርና የማቃለያ እርምጃዎች መውሰድ የሚገባቸው መሆኑን ለመጠየቅ ስምምነት ላይ ደርሰዋል (መምሪያ 1)፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የሸቀጣ ሸቀጦች የማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት ብዙ ግዜ በጣም ጥብቅ የሆኑ የአካባቢ አጠባበቅ ክንውኖች መሟላትን እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል፡፡ ለምሳሌ፣ የዘዘዘማአሥ ማረጋገጫ የሚሰጣቸው ፕሮጀክቶች አካባቢውን የሚጎዳ ምንም ነገር የማያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ ረዘም-ያለ የክንውኖች ዝርዝር ይጠቁማል (መርህ፡- 4.2-4.6፤5.1-5.16) ፡፡

በአካባቢ ነዋሪዎች “የውሃ አቅርቦቶች ሥርጭት ላይ የሚፈጠሩ ተግዳሮች በተለይ አስጊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይኸውም በተጎጂ ማህበረተሰቦች ላይ ሊደርስ ከሚችለው ጉልህ የሆነ ማህበራዊ ተፅዕኖ ባሻገር ከውሃ ጋር

ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዩች ዋና የአቅርቦት ሰንሰለት መቋረጥና ምናልባትም የስራ ፈቃድ መነጠቅ ለንግድ ተቋማት ከፍተኛ ወጪዎች ውስጥ ከመዘፈቅ አንስቶ እስከ ተቋማቱ መዘጋት የሚደርስ ከፍተኛ ጉዳት” ሊያጋጥም ይችላል (የኢንተርፊይዝ ማዕከል፣ 2004 ዓ.ም፡- 4-5) ፡፡

መጠቀሱ አስፈላጊ ላይሆን ቢችልም እንኳን፣ የግብርና ፕሮጀክቶች ያለበቂ የውሃ አቅርቦት ቀጣይነት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ከማህበረሰቦች ጋር በውሃ ሰብብ የሚፈጠሩ ክርክሮች የፕሮጀክቶች ትግበራዎች እንዲጓተቱ ስለሚያደርጉ ከፍተኛ ዋጋ ያስከፍላሉ (የመንዴን ፕሮጀክት፣ 2005 ዓ.ም፤22) ፡፡ ከዚህ ባለፈም፣ የመጠጥ ውሃ ማግኘት ሰብአዊ መብት በመሆኑ፣ ፕሮጀክቶች መብት በመፃረር የተንቀሳቀሱ ከሆነ የፕሮጀክቱ ባለቤቶች የሆኑት ኢንቬስተሮች ሰብዓዊ መብቶችን በሚዳስሰው ክፍል ውስጥ ለተጠቀሱት አደጋዎች ራሣቸውን ያጋልጣሉ፡፡[22]

እንደዚሁም ኢንቬስተሮች ደኖችን፣ ረግረጋማ ስፍራዎችን እና ከፍተኛ እንክብባቤ በሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ፕሮጀክቶችን በጥርጣሬ መመልከት አለባቸው፡፡ አልፎ አልፎም ህገወጥ መጠለያዎችን በመስራት ሳቢያ የደኖችን መመንጠር ያስከተሉ በርካታ የግብርና ኢንቬስትመንት ፕሮጀክት ምሳሌዎች አሉ፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ከተፈፀሙት የደን ምንጠራዎች ውስጥ ቢያንስ ቢያንስ ግማሽ ያህሉ ለግብርና ንግድ ስራ መሆኑን እንዳንድ ጥናቶች አሳይተዋል (ላውሡን፣2006 ዓ.ም) ፡፡

በአጭሩ ከአካባቢ ተጐጂነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳቶች ከገንዘብ አንፃር የኢንቬስትመንቱን ስኬታማነት ከፍተኛ አደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡

ሳጥን 15፡- አካባቢና የዘለቄታዊነት አደጋ መንስኤዎች

**ከፍተኛ አደጋ**

- የአማተግ በአንገብጋቢ ሁኔታ ሊቃለሉ የማይችሉ አሉታዊ አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ሊያሳዩ ይችላል፡፡

**መካከለኛ አደጋ**

- ፕሮጀክቱ የሚካሄድበት ስፍራ ሰዎች ያሉበት ወይም እንክብካቤ የሚያስፈልገው እና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው አካባቢ ላይ ነው፡፡
- ሊካሄድ የታሰበው ፕሮጀክት በመሬት ይዞታ ለምግብ ዋስትናና በሰብአዊ መብቶች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተፅዕኖዎች የሚያካትት በገለልተኛ አካል የሚደረግ የአማተግ ገና አልተጠናቀቀም፡፡
- የአማተግ በአካባቢ ላይ የጎላ-አሉታዊ ተፅእኖዎች ሊደርሱ የሚችሉ መሆኑን ያሳያል፤ ግን ደግሞ በአግባቡ ሊተገበር ከቻለ እነዚያን ውጤቶት ማቃለል የሚችልባቸውን መንገዶች ያካትታል፡፡

## 3. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

አደጋን በቅጡ ለማስተናገድ ይቻል ዘንድ ኢንቬስተሮች ጠንካራ የአካባቢ አያያዝ ፓሊሲዎችን በከፍተኛ መጠን በመቀየስ ላይ ይገኛሉ፡፡ በግብርናው መስክ የሚሰማሩ ኢንቬስተሮች በአካባቢ ሁኔታ ላይ በሚደርስ ጉዳት መንስኤ የሚያጋጥሙ ጉዳቶችን ለማስተናገድ ተመራጩ ዘዴ ደረጃቸው ከፍ ያለ አካባቢ-ነክ መስፈርቶችን መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን ይገነዘባሉ (የመንዴን ፕሮጀክት፣ 2006 ዓ.ም፡2)፡፡ እንደዚያ ያሉ ደረጃዎችን የጠበቁ መስፈርቶችን መጠቀም በበኩሉ ውጤታማ የሆኑ የአካባቢ ተፅዕኖ የግምገማ ጥናቶችን፣ በህግ አስገዳጅነትም ይሆን/አይሁን ማካሄድን የግድ ይላል (የመንዴን ፕሮጀክት፣ 2005 ዓ.ም፡22)፡፡ እንደዚያ ያሉ ግምገማዎች በዚሁ መምሪያ ውስጥ ሌላ ስፍራ እንደተገለፀው ሁሉ፣ አብዛኛውን ግዜ የአጠቃላይ የማህበረሰብ የመለያ ስራ፣ የአማተግ፣ ከማህበረሰቡ ጋር የሚደረጉ ምክክሮች እና የአሉታዊ ተፅዕኖ የማቃለያ ሂደት አካል መሆን አለባቸው፡፡

[22] በተወሰኑ ሀገሮች የሰብዓዊ መብት ከውኃ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ መርህ አዘጋጅተዋል ምሳሌ የጀርመን ፡፡ የልማት ትብብር (2012) መመልከት ይቻላል፡፡

አንዳንድ ሀገሮች አካባቢያዊ ክንውኖች ከሁኔታው ጋር መጣጠም ያለባቸው መሆኑን የሚጠይቁ ህጎች በተሟላ መልኩ የሌላቸው ሲሆን፣ በአንፃሩ ህጎቹ ያላቸው ሀገሮች ደግሞ በሚገባ ላይተገብሯቸው ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደዚሁ የአማተግዎች መኖርን የሚጠይቁ ህጎች በግብርና ፕሮጀክቶች ላይ ላይተገበሩ ይችላሉ (ስሞለርና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም፡5)፡፡ እንደነዚያ ባሉ ሁኔታዎች፣ ኢንቬስተሮች በህግ ከሚጠየቀው ባሻገር እንዲያደርጉ ኦፐሬተሮችን መገፋፋት ይኖርባቸዋል፡፡

አካባቢውን በሚጐዱ ድርጊቶች ሳብያ ተጐጂነት እንዳይኖር ለማድረግ በቅርብ በግሉ ዘርፍ እንደ ዊልማት፣ ዩኒሬቨር፣ ካጊል እና ኮንግራ ያሉ በብዙ አገሮች የሚንቀሳቀሱ የንግድ ተቋማት `ምንም የደን ምንጣሮ አይኖርም' በሚል ቁርጠኝነት ላይ ተመስርቶ የተከናወነ ተግባር እንደ አብነት ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ ዊልማት የሚባለው የዓለም ትልቁ የዘንባባ ዘይት አምራች ኩባንያ ማንኛውንም የደን ምንጣሮ ድርጊትን፣ በመስክ ላይ የሚካሄድ የልማት ሰራን እና የአካባቢውን ማህበረሰቦች ለብዝበዛ የሚዳርጉ ክንውኖች በሙሉ በ2007 ዓ.ም መገባደጃ ላይ በሁሉም የስራ ቦታዎቹ ለማስወገድ ቃል ገብቷል (ዊልማት፣ 2005ዓ.ም)፡፡

የአካባቢ የተፅእኖ ግምገማዎችን በከፍተኛ ጥራት ለማካሄድ የሚረዱ ዘርፈ-ብዙ መምሪያዎችና የደረጃ መለኪያዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የተወሰኑቱ እንደ የዓፋድ የአካባቢያዊ፣ የጤናና የደህንነት መምሪያዎችን የባዘማሥ መርህዎችን (7-11) ደጋፊ መምሪያዎችን፣ የአለም ባንክ የአካባቢያዊ ጤናማነትና የደህንነት መምሪያዎች (ክፍል 1) ፣ የምግድ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ቁጥጥር መምሪያዎች እና የአገዳ ተክሎችና አመታዊ ሰብሎች መምሪያዎችን (ሙሉ በሙሉም ባይሆን) ይጨምራሉ፡፡

የመጨረሻው ዓላማ ጉዳትን የማቃለል እቅድ ያለው የአጠቃላይ አማተግ አካል የሆነ በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ለመቆጣጠር የሚረዳ እቅድ መንደፍና መተግበር ነው፡፡ ምክክርና ግልፀኝነትን በሚመለከቱ ምክክሮች ውስጥ እንደተዳሰሰው ሁሉ፣ ምርጥ ክንውኖች የአማተግንና በዚያ ላይ ተመስርቶ የሚዘጋጀውን እቅድ ለህዝቡ ይፋ ማድረግን ይደግፋሉ (ዊልማር፣ ፣2005 ዓ.ም)፡፡ እንደዚሁም የአማተግ ውጤት ፕሮጀክቱ ስኬታማ እንደሚሆን መደረግም እንዳለበት ማሳየት እንደዚያ ያለው ውጤት ደግሞ ኢንቬስትመነቶች በአካባቢው ላይ ምንም አይነት ጉዳት ማድረስ አይኖርባቸውም ከሚለው የመመሪያዎቹ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር ጋር የሚጣጣም ነው፡፡

ሳጥን 16፡-
አካባቢና ዘለቄታዊነት መቆጣጠሪያ ዝርዝር

በአካባቢ ሁኔታ ላይ ሊደርስ በሚችል ጉዳት ሣቢያ ኢንቬስተሮች ሁለት ጉልህ የሆኑ አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል፡፡ የመጀመሪያ፣ የዚያን ዓይነቱ ጉዳት በፕሮጀክቱ ላይ የባለድርሻ አካላትን ተቃውሞ ሊያስነሳ ስለሚችል ነው፡፡ ሁለተኛው፣ በአካባቢ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች እንዳያደርጉ የሚጠይቁ ህጐችን አለማክበር ኦፕሬተሮችንና ኢንቬስተሮችን በፍትሃ-ብሄር ወይም በወንጀል ተጠያቂ ሊደርጋቸው ይችላል፡፡

- ✓ ኢንቨስተሮች በፕሮጀክቱ ለመግፋት ከመወሰናቸው በፊት፣ ስኬታማ የሆኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማዎች፤ በህግ ባይጠየቅም፣ የአማተግ አካል ተደርገው እንዲካሄዱ በመጠየቅ አደጋውን በሚገባ መቆጣጠር ይችላሉ፡፡
- ✓ የአካባቢያዊ ተፅዕኖ ግምገማ የመጨረሻው ውጤት በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለማስተናገድ የሚገኝ ዕቅድ ለመንደፍ መሆን አለበት፡፡ እቅዱም ፕሮጀክቶች ሊያደርሱ የሚችሉትን ጒጂ አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ኦፕሬተሩ፣እንዴት መከላከል፣ መቀነስ፣ ማቃለል እንደሚችል ማስቀመጥ አለበት፡፡
- ✓ የአማተግ ውጤቶች ፕሮጀክቱም ስኬታማ መሆን እንደሚችልና ኢንቬስትመነቱም መቀጠል እንዳለበት ሊጠቁሙ ይችላሉ፡፡
- ✓ የአማተግ `እውነተኛነት ' ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ገለልተኛ በሆነ ሶስተኛ ወገን መካሄድ አለበት፡፡

# 7

## አንገብጋቢ የትግበራ ፈተናዎች

## የወካይ ምልክቶች አጠቃቀም

### የከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች

በርካታ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች መኖር ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በኢንቬስትመንቱ መግፋት እንደሌለበት ሊያነሳሰው ይገባል፡፡

### መካከለኛ የአደጋ መንስኤዎች

ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቬስተር በተገቢ ትጋት ዝግጅት ምዕራፍ ላይ ፕሮጀክቱን በድጋሚ በመፈተሽና አደጋዎችን የማቃለያ መንገድ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

# 7. አንገብጋቢ የትግበራ ፈተናዎች

ቀደም ብሎ የቀረቡት ክፍሎች በግልፅ እንደሚያሳዩት፣ ኃላፊነት የተላበሱ የግብርና ኢንቬስትመንቶች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ወገኖች በሙሉ ተጠቃሚ ማድረግ የሚችሉ ቢሆንም፣ እንደዚህ በቀላሉ ስኬታማ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም፡፡ ይህ ምዕራፍ በተግባር ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሁለት ለየት-ያሉ ፈተናዎች ዙሪያ በአካባቢ ነዋሪዎች የአቅም ግንባታና ቁጥጥር ዙሪያና ከዚያም ለእነዚህ ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ ስልቶችን ይጠቁማል፡፡

## ሀ. የአቅም ግንባታ

### 1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

መመሪያዎቹ በተለያዩ ክፍሎች ውስጥ፤ የአንድ አካባቢ ማህበረሰቦች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በመሬት ላይ በሚደረጉ ኢንቬስትመንቶች ሣቢያ የሚከሰቱ ተፅዕኖችን መቆጣጠርና ማቃለል እንዲችሉ መርዳት ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ መንግስትም፡- "ድሪዎቹ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት መብቶቻቸውን መጠቀም እንዲችሉና ግዴታዎቻቸውን በተሟላ መልኩ ማሟላት እንዲችሉ" (አንቀጽ 7.5) ድጋፍ እንዲያደርጉና "በመሬት፣ በዓሣ ሀብትና ደኖች ላይ የሚሰሩ አካላት ሰብአዊ፣ አካላዊ፣ ገንዘብ-ነክና በሌሎችም በቂ አቅም ያላቸው መሆኑን እንዲያረጋግጡ ያበረታታሉ (አንቀፅ 8.10)፡፡

መመሪያዎቹ እንደዚሁም ሁሉም ባለድርሻ አካላት በልማዳዊ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ስርዐቶች የሚገለገሉ ማህበረሰቦችንና ነባር ተወላጅ ማህበረሰቦች "የመሬት ባለቤትነት ሰርዓቶቻቸውን በተመለከተ አባላቶቻቸው በውሳኔ አሰጣጥና አስተዳደር ጉዳዮች በሙሉ ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ አቅማቸውን በማሳደግ" ረገድ እንዲረዷቸው (አንቀፅ 9.2) እና ማህበረሰቦቹ የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን በሚወስኑ ህጎችና ፖሊሲዎች ቀረፃ ላይ በንቃት መሣተፍ እንዲችሉ የህግና የሙያ እገዛ እንዲያደርግላቸው ይገፋፋሉ (አንቀፅ 9.10)፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ልማዳዊ የመሬት ይዞታ መብቶቻቸው ህጋዊ እውቅና እንዲሰጣቸው ማህበረሰቦቹና ተሣታፊዎቹ በሚያደርጓቸው ጥረቶች መንግስታት ሙያዊና ህጋዊ ድጋፍ እንዲሰጧቸው መመሪዎቹ ያበረታታሉ፡፡

ኢንቬስተሮች የአካባቢውን ማህበረሰብ አቅም መገንባት ያለባቸው መሆኑን መርህዎቹ አበክረው ያሳስባሉ (መርህ 2.4) ፡፡

### 2. አደጋው ምንድን ነው?

በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በቂ አቅም የሌላቸው ከሆነ ለግብርና ፕሮጀክቶች በሶስት መንገዶች አሳሳቢ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው፣ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ በርካታ ማህበረሰቦች የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን በሚገባ ለማስከበር ከኦፕሬተሮች ጋር በአግባቡ መስራት የማይችሉ በመሆኑ ለፕሮጀክቶች

ድጋፍ የመስጠት አቅማቸው አናሳ ሊሆን ይችላል (ስሞለር እና ሌሎች፣2006 ዓ.ም፡14)፡፡ ሁለተኛው ፕሮጀክቱ በከፊል ከውጪ በሚገኙ ምርቶች ላይ ጥገኛ በሚሆንባቸው አካባቢዎች፤ ትንናሽ ይዞታዎች ያሏቸው የአካባቢው ማህበረሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የእርሻ ውጤቶችን በበቂ መጠን ማቅረብ ሊሣናቸው ይችል ይሆናል፡፡ ሶስተኛው ማህበረሰቦቹ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ሙሉ በሙሉ ማቅረብ የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 3. ጉዳትን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

የግብርና ኢንቬስትመንቶች ማህበረሰቦቹንና ኦፕሬተሩን ጭምር ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል አቅም በማህበረሰቦቹ ውስጥ እንዲገነባ አጋጣሚውን ይፈጥሩላቸዋል፡፡ ብዙዎቹ ማህብረሰቦች፤ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ በተወሰኑት ወይም በሁሉም መስኮች እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡- (1) የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን ለማወቅና ለመጠበቅ እንደዚሁም በማህበረሰብ እድገት እቅድ አወጣጥና በሚሰሩ ሰራዎች ላይ ተገቢውን ነገር በስፋት ለማድረግ፣ (2) በኢንቬስትመንት ሂደት ላይና ከፕሮጀክት ኦፕሬተሩ ጋር በሚገባ ለመስራት እና (3) እንደ የውጭ አንቀሳቃሽ ዘዴዎች ወይም በቀጥታኛ የስራ ቅጥር ባሉት በአጋርነት-መልክ በተቀናጁ አሰራሮች አማካይነት በፕሮጀክቱ በራሱ ተሣታፊ መሆናቸው፡፡ የዚህ አይነቱ ዕገዛ ይደረግ ዘንድ፣ ኦፕሪተሮቹ ከማህበረሰቡ አባላት ጋር በቀጥታ ወይም በአካባቢው ካሉ ህዝባዊ ድርጅቶች ጋር እንዲሰሩ ኢንቬስተሮቹ ሊያበረታታቸው ይችላሉ (AFD, 2014:48)፡፡

ማህበረሰቦች (በመመሪያዎቹ እንደተገለፀው) የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን እንዲያሰጠብቁና በማህበሰረብ እድገት እንቅስቃሴዎች በአጠቃላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ የመርዳት ኃላፊነት የመንግስት ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ሆኖም፣ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ኢንቬስተሮችም የአካባቢውን ማህበረሰቦች ለመረዳት በሚደረጉ ጥረቶች ድጋፍ ቢያደርጉ ራሳቸውንም ተጠቃሚ ሊደርጋቸው ይችላል፡፡ አንዱ ስልት ደግሞ ልማዳዊ የመሬት መብቶች ያሏቸውን ባለይዞታዎች ወይም ልማዳዊ የባለይዞታነት መብቶቻቸው ህጋዊ እውቅናና ጥበቃ የሌላቸውን፣ ሴቶችን ጭምር፣ መብቶቻቸውን ህጋዊ ማድረግ እንዲችሉ መርዳት ነው፡፡ በአካባቢው እንቅስቃሴ የሚያደርገው የንግድ ተቋም እንደዚሁ የአካባቢው ነባር ተወላጆች የባለይዞታነት መብቶቻቸው ተመዝግበው እንዲያዙ ለማድረግ አወንታዊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል (አንቀፅ 9.8)፡፡ እንደዛ መደረጉ ደግሞ፣ መብቶቹ ካሏቸው ነዋሪዎች ጋር ጤናማ ግንኙነቶችን ለመመስረትና የመሬት ይዞታ መብቶች ያሏቸው በትክክል እንዲታወቁ ለማድረግ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና በመሬት ይዞታ መብቶች ላይ ወደፊት ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችን ከወዲሁ ለማስወገድ ብሎም ከረጅም ግዜ አንፃር ኦፕሬተሩ፣ ኢንቬስተሩና ማህበረሰቡ ሁሉም በጋራ ተጠቃሚ መሆን ያስችላቸው ይሆናል፡፡

ማህበረሰቦቹ በኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ አመርቂ በሆነ መልኩ መሳተፍ እንዲችሉ አቅማቸውን በማሳደግ ረገድ መርዳቱ ለኢንቬስተሮቹም ጠቃሚ ይሆናል፡፡ እውቀት ያላቸው ማህበረሰቦች በማህበረሰብ የመለያ ስራ፣ በምክክሮች፣ በድርድሮች እና በቅሬታዎች አፈታት እና ከፕሮጀክት ኦፕሬተሩ ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት ለመመስረት የተሻለ እድል ይኖራቸዋል፡፡ ለምሣሌ ያህል፣ የማህበረሰቡ አባላት ስልጠና ማግኘትና በሂደቱም ትርጉም ባለው መልኩ ተሣትፎ ማድረግ ከቻሉ የማህበረሰብ መለያ ስራ በራሱ የአቅም መገንቢያ መንገድ ሊሆን ይችላል (USAID፣ 2007 ዓ.ም ለ፡34)፡፡አለበለዚያም አንድ ኢንቬስተር (በምዕራፍ 3 ውስጥ ተገልፃ እንደነበረው ሁሉ) ማህበረሰቡ ነፃ የህግ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ወይም የሰለጠኑ ኢ-መደበኛ የህግ ባለሙያዎች እርዳታ እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላል፡፡

ኢንቬስተሮች የአካባቢው ማህበረሰቦች የመንደር ባለአደራ ኮሚቴዎችን፣ የህብረት ስራ ማህበራትን ወይም የአጠቃላዩን ማህበረሰብ ጥቅሞች በግብይይት ላይ ማስጠበቅ የሚችሉ ሌሎች ማህበራትን ለማቋቋም የሚያደርጓቸውን ጥረቶችንም መደገፍ ይችላሉ፡፡ ተወካዩቻቸው ሀቀኛ ከሆነ፣ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎች በማንኛውም የክፍያ ሂደት ወይም በካሳ ክፍያ ላይ በንቃት ተሳታፊ መሆን የሚያስችላቸውን እና ፍትሀዊ የሆነ ድርሻ ማግኘት የሚችሉበትን እድል ሊፈጥሩላቸው ይችላሉ፡፡ እንደዚሁም ሁሉ ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙነት ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ሊያመቻችላቸው ይችላሉ (USAID፣ 2007 ዓ.ም ለ፡45)፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች እንቅስቃሴ የሚያደርጉት የንግድ ተቋማት ቀጣይነት ያለው የስራ ማረጋገጫ ማግኘት ከፈለጉ በአቅም ግንባታ ስራ ላይ መሣተፍን እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የባዘማስ

መስፈርት 5.ለ ላይ እንደተቀመጠ በ"ድህነት በተንሰራፋባቸው ክልሎች ውስጥ በባዩፊውል ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ነባር ማህበረሰቦችን እና ለአደጋ የተጋለጡ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያረጉና የሚያበረታቱ ለየት ያሉ እርምጃዎች መቀየስና መተግበር ይኖርባቸዋል" ይላል፡፡ የአፈፃፀም መስፈርት 5ለ.2 ይህንን ግዴታ ለመወጣት የስልጠና መኖር አስፈላጊ መሆኑን ያጠናክራል፡፡

## የትግበራ ፈተናዎች

የዚህ አይነቱን አደጋ የመቆጣጠሪያ ሶስትኛው ስልት የማህበረሰቡ አባላት በፕሮጀክቱ ክንውኖች ላይ ቀጥተኛ ተሣታፊ መሆን ይችሉ ዘንድ ስልጠና እንዲያገኙ በኢንቬስተሩ ወይም በኦፕሬተሩ የሚደረግ እርዳታ ነው፡፡ እንደዚህ ለማድረግ ደግሞ፣ አንደኛው መንገድ የሚሆነው ቀጣይነት ያለው መሻሻል የሚመጣበት ሂደት አካል ተደርጎ ጥሬ እቃዎችን ለሚያቀርቡ የትናንሽ ባለይዞታዎች፡- ለሴቶችና ወንዶች ጭምር ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ምርታቸው በመጠንም ሆነ በጥራት ተሻሽሎ እራሳቸውም ሆኑ ፕሮጀክቱ ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ መርዳት ነው (ወዘዘዘማአስ፤ 2005 ዓ.ም፡- መስፈርት 4.8፤ USAID፣ 2007 ዓ.ም ለ፡40)፡፡

እንደዚሁም ሁሉ ኢንቬስተሮች የስልጠና መርሀግብሮችን በመንደፍ ኦፐሬትሮች ሰራተኞችን ክህሎቶችና ልምድ እያገኙ ሲሄዱ፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ውስጥ፣ ወደ አመራር ቦታዎች ማሳደግ እንዲችሉ ሊያበረታቷቸው ይችላሉ(ሚርዛ እና ሌሎች፣ 2006 ዓ.ም፡24)፡፡ በእርሻ ቦታ ላይ የሚደረግ ኃላፊነት የተላበሰ ኢንቨስትመንት መምሪያ ኢንቬስተሮች ለሰራተኞች የሚሰጥ ስልጠና ለትግበራ አስፈላጊ የሆነ እርምጃ አድርገው መውሰድ ያለባቸው መሆኑን ያመለክታል (UNGC፣ 2006 ዓ.ም)፡፡ በአካባቢው ስልጠና መስጠትና የአካባቢ ባለሙያዎችን መቅጠር እንደዚሁ ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙነቶችን ለማጠናከር ሊረዳ ይችላል፡፡

በዚህ መምሪያ ውስጥ እንደተዳሰሱት ሌሎች ርዕሶች ሁሉ ኢንቬስተሮች በአቅም ግንባታ መርሀ ግብሮች ውስጥ ሴቶች የሚታቀፉ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ የወዘዘዘማአስ መስፈርት 40፣ በተመሣሣይ መልኩ ሴቶች የክህሎቶች ስልጠና ማግኘት እንዳለባቸው እና የሚሰጠው ስልጠናም ፆታዊ አድሎአዊነትን ለማስወገድ መርዳት ያለበት መሆኑን ያትታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ በ USAID(2007 ዓ.ም ለ፡19) እንደተገለፀው፡- "ሴቶችን ለመቅጠር እና ለማሰልጠን፣ አለበለዚያም ድጋፍ በመስጠት፣ ሴቶችን ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ ስምምነቶች ውስጥ (በሴት ገበሬዎች የተመሰረቱ ድርጅቶች ያሉትን) እንዲካተቱ ጥረቶች መደረግ አለባቸው"፡፡

ሳጥን 17፡-
የአከባቢን ማህበረሰብ የአቅም ግንበታ መቆጣጠሪያ ዝርዝር

ከአካባቢው ያለው አቅም በቂ ካልሆነ የግብርና ፕሮጀክቶችን በሶስት መንገዶች ስጋት ላይ ይጥላል፡- (1) የመሬት ይዞታ መብቶቻቸውን በሚገባ ማስከበርና ከኢንቬስተሮች ጋር በአግባቡ መስራት የሚችሉ ማህበረሰቦች ፕሮጀክትን የመደገፍ አቅማቸው አናሳ ሊሆን ይችላል፡፡ (2) ፕሮጀክቱ በከፊል ከውጪ በሚገኙ ምርቶች ላይ ጥገኛ በሆነባቸው ቦታዎች፣ በአካባቢው ያሉ ባለትናንሽ ይዞታዎች ባለመብቶች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የእርሻ ውጤቶችን በበቂ መጠን ማቅረብ አይችሉም፡፡ (3) ማህበረሰቦቹ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል ሙሉ በሙሉ ማቅረብ ሊያግታቸው ይችል ይሆናል፡፡

- ✓ ኢንቬስተሮች ማህበረተሰቦቹ በኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ አምርቂ በሆነ መልኩ መሳተፍ እንዲችሉ ለመረዳት የሙያና የገንዘብ ድጋፍ ሊያደርጉባቸው ይችላሉ፡፡ እውቀት ያላቸው ማህበረሰቦች በማህበረሰቡ የመለያ ስራ፣ በምክክሮች፣ በድርድሮችና በቅሬታዎች አፈታትና ከፕሮጀክቱ ጋር ቀጣይነት ያለው መስተጋብር ለመፍጠር የተሻለ እድል ሊኖራቸው ይችላል፡፡
- ✓ ኦፕሬተሮች ለ'አውት ግሮወርስ' ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ሰብሎችን በከፍተኛ መጠን ማምረት እንዲችሉ የግብርና ኤክስቴንሽ አገልግሎት፣ ዘርና ሌሎች ግብዐቶች፣ የመስኖ መሳሪያዎች በማቅረብ አቅማቸውን እንዲገነቡ ለማድረግ ኦፕሬተሩን ማበረታታት አለባቸው፡፡
- ✓ ሰራተኞች ክህሎቶችና ልምድ እያገኙ ሲሄዱ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ውስጥ ወደ አመራር ቦታዎች መሸጋገር እንዲችሉ ሰራተኞቹ ስልጠና እንዲያገኙ ኦፕሬተሮች ደጋፍ ማድረግ ይችላሉ፡፡

# ለ. ቁጥጥር

## 1. መመሪያዎቹ ምን ይላሉ?

መመሪያዎቹ የመሬት ይዞታ መብቶችን ሊጐዱ የሚችሉ መጠነ ሰፊ የሆኑ ኢንቬስትመንቶችን ተፅዕኖ መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን በአፅንኦት ያስገነዝባሉ፡፡ መንግስታትም በአገሮቻቸው ውስጥ የሚካሄዱ ኢንቬስትመንቶች ተፅዕኖ በአጠቃላይ የመቆጣጠር ቀደምት ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ወገኖችም ቢሆኑ የተወሰኑ ፕሮጀክቶችን ተፅዕኖዎች የመከታተል ሀላፊነት አለባቸው፡፡ መንግስታት እና ተጎጂ የሆኑ ወገኖች በመሬት ይዞታ መብቶች ላይ በስፋት በሚደረጉ ግብይቶች፣ በአጋርነት ላይ የተመሰረቱ ስምምነቶች ጭምር፣ አተገባበር ውጤቶቻቸውን በተመለከተ ስኬታማ የሆኑ ክትትሎች እንዲኖሩ ለማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይኖርባቸዋል (አንቀፅ 12.14)፡፡ ይህ ሀሳብ፣ ሁሉም ወገኖች፣ የንግድ ተቋማት ጭምር፣ ሙስናን ለመዋጋት የሚቀረጹ መመሪያዎችን አተገባበር መቆጣጠር እንዳለባቸው የሚያስገነዝበውን ሌላኛውን ክፍል የተሟላ እንዲሆን ያደርጉታል፡፡ (አንቀፅ 6.8፣ 6.9 እና 11.7፣ እና መርህ ቁጥር 10)

## 3. አደጋው ምንድን ነው?

ይህ ሙያዊ መምሪያ፣ አንድ ፕሮጀክት የሚካሄድበት አካባቢ ነዋሪዎችን የመሬትና ሌሎች መብቶቻቸው ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ፕሮጀክቶች ለገንዘብ ኪሣራ መጋለጣቸው አይቀሬ ሊሆን መቻሉን ያጠናክራል፡፡ ስለዚህ የፕሮጀክቱ አመራሮች እንደነዚያ ያሉ ተፅዕኖዎችን በአግባቡ መቆጣጠር መቻል/ አለመቻላቸውን አስመልክቶ ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለተጎጂነት ጉልህ መንስኤ ይሆናል፡፡

የቁጥጥር ዘዴዎች በቂ አለመሆን ለበርካታ አሉታዊ ውጤቶች ሊዳርግ ይችላል፡፡ ለምሣሌ ያህል፡-

- ማህበረሰቡን አሳታፊ የሆነ እቅድ ካለመቀየሱ የተነሳ ከማህበረሰቦች ጋር የሚኖረው ግንኙነት ውጤት አልባ መሆን፤
- በአማተግ የሚጠቆሙ እርምጃዎች አተገባበር ደካማ በመሆኑ ሳቢያ በእቅድ ውስጥ የተመለከተው ጉዳት መከሰቱ የማይቀር መሆኑ፣
- ኦፕሬተሮች ለስምምነቶች ተገዥ መሆን ባለመቻላቸው ወይም ለማህበረሰቡ ቃል የተገቡ ጥቅማ ጥቅሞች ባለመስጠታቸው ሣቢያ የሚቀሰቀስ የማህበረሰብ ተቃውሞ (AFD፣ 2006 ዓ.ም፡28) ፤ እና
- የንግድ ተቋማቱ በመመሪያዎቹ የሚጠየቁ ነገሮችን ለሟሟላት በተጨባጭ ምን ጥረት እያደረጉ እንደሆነና እነዚያ ክንውኖች በሚደረጉባቸው ማህበረሰቦች ላይ እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ኢንቬስትመንቶች የፋይናንስ አፈፃፀም ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ ሊኖራቸው እንደሚችል ለውስጥ ወይም ለውጭ ደንበኞች ማሳወቅ አለመቻል ነው፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ በግብዓቶች እጥረት እና በሌሎች ተግዳሮቶች መኖር መንግስታት፣ ሕጐቻቸው ጠንካራ ቁጥጥር እንዲኖር በሚጠይቁባቸው ቦታዎች እንኳን ሳይቀር፣ ኢንቬስትመንቶቹ በግብርና ላይ ስላላቸው ተፅዕኖ ደካማ የቁጥጥር ስራ እንዲያካሂዱ ያስገድዷቸዋል (ሚርዛ 2006 ዓ.ም ፡ 2.13)፡፡ ምንም እንኳን መንግስታት መመሪየዎቹን በህጐቻቸው እና በአፈፃጸም ድንጋጌዎቻቸው ውስጥ በማካተታቸው ይህ ሁኔታ ቀስ በቀስ በመለወጥ ላይ የሚገኝ ቢሆንም፤ ኦፕሬተሮች ከማህበረሰቡ ጋር በመሆን፤ በራሳቸው የቁጥጥር መርሀግብሮች መሰረት (የአጠቃላዩ የአደጋ ቁጥጥር ሂደት አካል በማድረግ) እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ኢንቬስተሮቹ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## 4. አደጋን እንዴት መቆጣጠርና መቀነስ ይቻላል?

ኢንቬስተሩ ከቁጥጥር ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ጉዳቶችን ለማስተናገድ ሊወስድ የሚችላቸው እርምጃዎች በዚህ መምሪያ ውስጥ ሌላ ቦታ በምክረ ሃሣብነት ከተጠቆሙት ክንውኖች ጋር ከሞላጐደል ተመሳሳይ ናቸው፡፡ አንደኛ፣ ኦፕሬተሮች በምክክር ሂደት ከማህበረሰቡ ጋር በሚያደርጉት ውይይት ላይ 'ቁጥጥር' አንዱ የመወያያ እርእስ መሆን አለበት፡፡ የፕሮጀክቱን አተገባበርና ተፅዕኖ በግዜ ሂደት የሚቆጣጠር ኮሚቴ ማቋቋም ብልህነት ይሆናል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት፡- የአካባቢ-በቀል ህዝባዊ ድርድቶች ተወካዩች ጭምር፣ በኮሚቴው ውስጥ ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡ ሁለተኛ፣ ስኬታማ ቁጥጥር ለማድረግ ፕሮጀክቱ የሚመራባቸው ወይም ከፕሮጀክቱ ጋር የሚያያዙ ውሎች በሙሉ ሁሉም ወገኖች የገቧቸውን ቃልኪዳኖችና ኃላፊነቶቻቸውን በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው (AFD፣ 2006 ዓ.ም፡47)፡፡ ለምሣሌ ስምምነቱ ማህበረሰቦች የሚገኛዋቸው ጥቅሞች መጠን እና የተግባራዊነት ግዜ ሰሌዳ እና ፣ እንደዚሁም ደግሞ ሳይፈፀም ቢቀር ሊከተሉ የሚችሉ ቅጣቶችን በዝርዝር የሚያስቀምጥ 'ሐረግ' ሊይዝ ይችላል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች የውሎቹ ቁጥጥር የማድረግ ሐላፊነት ማን እንደሆነና ቁጥጥሩ እንዴት እንደሚካሄድ ግልፅ የሚያደርግ ሐረግም ሊይዙ ይችላሉ፡፡ሦስተኛ፡ ስለ ግልፀኝነትና ሙስና በሚያትተው ምዕራፍ ጋር በሚጣጣም መልኩ የሁሉም ውሎች የፕሮጀክቱ ያልሆኑ ንብረቶች አማተገዎች እና ሌሎች አግባብነት ያሏቸው ሰነዶች ለማህበረሰቡና ለአጠቃላዩ ህዝብ መድረስ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ኢንቬስተሮች እና ኦፕሬተሮች የመመሪያዎቹን አተገባበር በተመለከተ ያላቸውን የአፈፃፀም ሪፖርት በግልፅ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ እንደዚያ መደረጉ ደግሞ የግልፀኝነት አሰራርን በማጐልበት ብቻ ሳይሆን ለስኬታማ ቁጥጥርም ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይቻላል፡፡ አራተኛ፣ አማተግ እራሱ ቁጥጥር የሚካሄድበትን መንገድ ማመላከት አለበት፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በበኩሉ በመሬት ይዞታ፣ በፆታ፣ በምግብ ዋስትና፣ በሰብዓዊ መብቶች እና በአካባቢ ሁኔታ ላይ የሚደርሱ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች በማቃለያ እቅዱ መሰረት እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በትላልቅ ፕሮጀክቶች ከፍተኛ ተጨባጭነት እንዲኖር ለማድረግ፣ ለቁጥጥር ስራው ነፃ የሆነ ሦስተኛ ወገን ማሳተፍ ተመራጭ ሊሆን ይችላል(USAID፤ 2007 ዓ.ም ለ፡50)፡፡ በመጨረሻም መንግስታት ፕሮጀክቱን የመቆጣጠር አዝማሚያ በሚያሳዩበት ቦታ፣ ኢንቬስተሮች ለአስፈላጊ መረጃ እና ለፕሮጀክቱ ስፍራ በተወሰነ ገዜ ተደራሽ እንዲሆኑ በማድረግ ከእነርሱ ጋር መተባበር አለባቸው፡፡

ሳጥን 18፡-
የቁጥጥር መስፈርት ዝርዝር

> ማህበራዊና በአካባቢ ላይ በሚደርሱ አስከፊ ተፅዕኖዎች ሣቢያ የሚከሰቱ ጉዳቶችን ለማሣነስ በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የሚካሄድ ስኬታማ ቁጥጥር በራሱ አደጋን የመቆጣጠሪያ ጠቃሚ ስልት ነው፤
>
> - ✓ በምክክር ሂደት ስለ ቁጥጥር መወያየትና በፕሮጀክት ቁጥጥር ማህበረሰቡን ማካተት፤
> - ✓ ሁሉም ወገኖች የሚገቧቸውን ቃልኪዳኖች ሀላፊነቶቻቸውን በግልፅ የሚያስቀምጡ ውሎችን መጠቀም፤
> - ✓ የሚፈፀሙ ውሎችን፣ የአማተግዎችንና ፕሮጀክት-ነክ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ ህዝቡ እንዲያውቅ ማድረግ፤
> - ✓ በአማተማ የማቃለያ እቅድ ውስጥ ለየት ያሉ የቁጥጥር ዘዴ ማካተት፤
> - ✓ መንግስት ቁጥጥር ሲያደርግ መተባበር፣

# የቁልፍ መልዕክቶች ማጠቃለያ

ይህ ሙያዊ መምሪያ የታለመው ኢንቬስተሮች በኃላፊነት ስሜት እና በትጋት በመንቀሳቀስ በእርሻ መሬት ላይ ማህበራዊ ተገቢነትና ዘለቂታዊ የገንዘብ አቅም ያላቸው ኢንቬስትመንቶችን ስኬታማ በሆነ መልኩ ማድረግ እንዲችሉ ለመርዳት ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እንከን የለሽ ነው ሊባል የሚችል ፕሮጀክት እንኳን የተወሰኑ ክፍሎችን ጥቅም መጉዳቱና ብሎም ትችት ማስነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ ቢሆንም ኢንቬስትሜንቶቻቸውን ከመመሪያዎቹ መርሆዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ የሚገመግሙ ፣ የሚቀርፁ፣ የሚተገብሩ እና የሚቆጣጠሩ ኢንቬስተሮች ግባቸውን ለመምታት የተሻለ እድል ይኖራቸዋል፡፡ የዚህ መምሪያ ቁልፍ መልዕክቶች እንደሚከተው ተጠቃለዋል፡፡

1. በእርሻ መሬት ላይ የሚደረጉ ኢቬስትመንቶች፤ ኢንቬስትመንቶቹ በማካሄድባቸው አካባቢ በሚኖሩ ኗሪዎች ላይ የጎላ ተፅዕኖ፡- አወንታዊና አሉታዊ ጭምር ሊኖራቸው ይችላል፡፡ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ፕሮጀክቶች የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መብቶቻቸውን እንዲያጡና በመሬታቸውም ሆነ በውሃና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች መጠቀም እንዳይችሉ አድርገዋቸዋል፡፡

2. ምንም እንኳን እነዚህ መመሪያዎች የሚያነጣጥሩት በዋነኝነት መንግስታት ላይ ቢሆም፣ የንግድ ተቋማትንም እግረ መንገዳቸውን ይዳስሳሉ፡፡ ኢንቬስተሮች ከመመሪያዎቹ ጋር በሚስማማ መልኩ መንቀሳቀስ ከቻሉ፣ በአብዛኛዎቹ በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ውስጥ በእርሻ መሬት ላይ ኢንቬስት ከማድረግ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ መጠነ ሰፊ ገንዘብ ነክ፣ የህጋዊነት፣ የአተገባበር እና የመልካም ስም ጉዳቶችን ለማስተናገድ እንዲችሉ ሊረዳቸው ይችላል፡፡

3. በፕሮጀክቱ ቀረፃ መዕራፍ ላይ፣ ኦፕሬተሮች የትናንሽ ባለይዞታዎችንና የአካባቢው ነዋሪዎችን የመሬት መብቶችን መተላለፍ የማይጠይቁ የፕሮጀክት ሞዴሎችን ማጤን ይኖርባቸዋል፡ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ኢንቬስተሮች የመሬት ማስለቀቅንና የሰዎችን መፈናቀል የሚያስከትሉ ፕሮጀክቶችን ማስወገድ አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ የአደጋ መጠንን ለመቀነስ የሚረዳ ጠቃሚ ስልት፣ በሰዎች ፍቃደኝነትም ይሁን ያለፍቃዳቸው የሚካሄድ ማንኛውንም አይነት የሰፈራ መርሃግብር ማስወገድ ነው፡፡

4. አንድ ኢንቬስተር፣ ሊደረግ ለታሰበው ኢንቬስትሜንት ከፍተኛ የአደጋ መንስኤዎች ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለማወቅ ቅድመ-ትግበራ ትንተና ማካሄድ አለበት፡፡ ግን ደግሞ ብዙ ጊዜ ኢንቬስትመንቱ ከፍተኛ አደጋ ያዘለ መሆኑን ሊያሳይም ይችላል፡፡

5. አንድ ሊካሄድ የታሰበ ኢንቬስትመንት ተገቢ ቅድመ-ትግበራ ትንተና የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል

   - አሣታፊ የሆነ የመሬት ይዞታ መብቶች መደበኛ፣ ልማዳዊና ኢ-መደበኛ መብቶች ጭምር፤ ያላቸውን ባልይዞታዎች በመላ የመለያ ስራ፣ እና
   - በመሬት መብቶች፣ በኑሮ ሁኔታዋቾች፣ በሰብአዊ መብቶች፣ በምግብ ዋስትና እና በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ የሚያሣይና፤ እና አሉታዊ ተፅእኖዎቹ የት፣ መቼ እና እንዴት እንደሚቃለሉ የሚገልፅ፣ ወይም ፕሮጀክቱ ቢቀጥል በጣም አደገኛ መሆኑን የሚያመለክት የተሟላ የአካባቢያዊና የማህበራዊ ሁኔታ የተፅዕኖ ግምገማ ናቸው፡፡

6. አጥጋቢ የሆነ፣ ተከታታይነት ያለው ምክክር እና የአካባቢውን ነዋሪ ይሁንታ የማያካትቱ ፕሮጀክቶች፣ ይህንን ከሚያደርጉት በበለጠ ለከፍተኛ ወጪዎች መዳረጋቸው አይቀሬ ሊሆን ይችላል፡፡ ያለበቂ የምክክርና የተሳትፎ ሂደት፣ የመሬት መብት ባለይዞታዎችን መለየት፣ ተፅዕኖዎችን መገምገም ወይም ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ቀጣይነት ያለው ውጤታማ ግንኙነትን መመስረት ፈፅሞ አይቻልም ሊባል ባይችልም እንኳን፣ አስቸጋሪ እንደሚሆን ግን አያጠራጥርም፡፡ ስለዚህም፣ ሁሉም ፕሮጀክቶች ወደ ስኬታማ ስምምነት ወይም ተጎጂ የሚሆኑ የባለድርሻ አካላት ነቅእፈ የሚያመራ ሁሉን አቀፍና ባህላዊ ተገቢነት ያለው የምክክርና የተሳትፎ ሂደት ማካተት አለባቸው፡፡

7 ኢንቬስተሮች ከመሬትና ከሌሎች ጉዳዩች ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ማንኛቸውም ክርክሮች ሚዛናዊ የሆነ ምላሽ መስጠት የሚችሉ መምሪያዎችን መንደፍና መተግበር፤ ወይም በሁሉም የባለድርሻ አካላት ስምምነት የተደረሰበትና ባህልን ያገናዘበ የቅሬታ አፈታት ስርዐት መቀየስ አለባቸው፡ እንደዚሁም መደበኛ የክርክር አፈታት ስርዓቶችን ሊደግፍ የሚችል ስርዓት መቀየስም አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

8 ኢንቬስተሮች ለሙስና ተግባራት ምንም አይነት ትዕግስት የማይኖራቸው ፓሊሲዎችን መንደፍና የንግድ ምስጢራዊነት የማይኖራቸውን ኘሮጀክት-ነክ መረጃዎችን በሙሉ ግልፅ መደረግ ያለባቸው መሆኑንና ግልፀኝነትን በላቀ ደረጃ የሚጠይቁ ፓሊሲዎችን መከተልና ለተግባራዊነትም ግፊት ማድረግ አለባቸው፡፡

9 የአካባቢ ማህበረሰቦች የግብርና ኢንቬስትመንቶች የሚፈልጉትን ለማቅረብና በኢንቬስትመንቶችም ተሳታፊ መሆን እንዲችሉ አቅማቸውን ለመገንባት የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍ ኢንቬስተሮችንም ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡

10 በማህበራዊና አካባቢ ሁኔታ ላይ በሚደርሱ አስከፊ የሆኑ ተፅዕኖዎች መንስኤ የሚከሰቱ ጉዳቶችን ለመቀነስ በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ ስኬታማ ቁጥጥር ማድረግ በራሱ የአደጋ መቆጣጠሪያ አንዱ ስልት ነው፡፡

ይህ መምሪያ ቀጣይነት ያለው የመሻሻል ሂደት አካል ተደርጐ መታየት አለበት፡፡ ለኢንቬስተሮችም ሆነ ለኦኘሬተሮች  በስራ ተሞክሮ ላይ በመመስረት ምርጥ የሆኑ አሰራሮችን መቀየስና በጊዜ ሂደትም እንዲሻሻሉ በሚደረግ ሂደት መሣተፍ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንደዚሁም መመሪያዎቹ ተቀባይነት እንዲኖራቸው እና ኃላፊነት የተሞላበት ኢንቬስትመንት በከተላቸው አሰራሮች መሰረት እንቅስቃሴዎች እንዲደረጉ መንግስታትን ቢገፋፉ ሁሉም በእኩልነት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት መድረክ ሊፈጠር ስለሚችል እነሱም ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በታዳጊ ሀገሮች ውስጥ መሬት ላይ የተመሰረቱ ኢንቬስትመንቶች ስኬታማ የመሆን ከፍተኛ እድል ሊኖራቸው የሚችለው፣ ኢንቬስተሩ፣ የአካባቢው ማህበረሰቦች እና መንግስት እያንዳንዳቸው ተጠቃሚ መሆን ሲችሉ ነው፡፡ በመሆኑም መመሪያዎቹ የሚያጠነጥኑት ሁሉንም ወገኖች ተጠቃሚ መሆን በሚያስችላቸው የእንቅስቃሴ ማዕቀፍ ዙሪያ ሲሆን፤ ይህ ሙያዊ መምሪያ ለማሳየት የሚጥረው የዚህ አይነቱን ውጤት ስኬታማ ለማድረግ ኢንቨስተሮች የበኩላቸውን ሚና መጫወት እንዲችሉ ለመርዳት ነው፡፡

# የግርጌ ማስታወሻዎች

1. `የኢኳተር' መርሆዎች (2005 ዓ.ም) አደጋዎችን ከከፍተኛው እስከ ዝቅተኛው ያሉትን በሦስት ክፍሎች ተንትኖ ይመድባቸዋል፡፡ ትንተናው ለአንዳንድ ኢንቬስተሮች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ መርህ 1 ን ይመልከቱ፡፡

2. ምንም እንኳን መመሪያዎቹ የሚያነጣጥሩት ደኖችና የዓሣ ሀብት ብዙ ቢሆንም፣ ይህ መምሪያ የሚያተኩረው በእርሻ መሬት ላይ በሚደረግ ኢንቬስትመንቶች ላይ ነው፡፡ የሙያ መምሪያ መንግሥታት የግብርና ኢንቬስትመንት ላይ ለሚያደርጉት ቁጥጥር እገዛ የሚያደርግ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ የሚመለከተው የህግ ባለሙያዎችን ነው፡፡ የታተሙ መምሪያዎች፣ የመመሪያዎቹ የአተገባበር ሁኔታዎችን፣ የዓሣ ሀብት፣ ደኖች፣ ፆታንና ነቅእፈ ጭምርን ይዳስሳሉ፡፡

3. የተባበሩት መንግሥታት ንግድና ሰብአዊ መብቶችን አስመልክቶ በተቀበላቸው የተመ መሰረታዊ መርሆዎችና በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት በአንድ ድምፅ በ2003 ዓ.ም በተቀበለው እንደተንፀባረቀው (OHCHR፣ 2001 ዓ.ም) ፡፡

4. ስለትናንሽ የእርሻ ይዞታ ሰፊ ገለፃ ለማግኘት፣ HLPE፣ 2005 ዓ. ምን ይመለከታል፡፡

5. የኢኳቶር መርሆዎች የሚያገለግሉት ከተወሰነ መጠን በላይ ባለው ገንዘብ የሚደረጉ ግብይይቶችን ብቻ የሚመለከት መሆኑን

6. አንድ ጥናት ኢንቬስተሮች አካባቢ ላይ የተመሰረተ የአደጋ ዳሰሳ መረጃ ማግኘት እንዳለባቸው፣ ወይም እንዲኖር መጠየቅ ያለባቸው መሆኑን ይጠቁማል (Munden project; 2013:21)፡፡

7. በፅንሰ-ሃሣብ ደረጃ፣ የአማተግ ስምምነት ከመፈረሙ በፊት መደረጉ ተመራጭ ቢሆንም፣ የአማተግ በመሬት-መብቶች፣የምግብ ዋስትና በሰብአዊ መብቶች ወይም በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን ካሳየ ፕሮጀክቱ ሊሰረዝ ይችላል የሚል መግባባት ካለ፣ የአማተግ ውል ከተፈፀመ በኋላም ሊደረግ ይችላል (Smaller etal;2014:29) ፡፡

8. UNIDROIT, FAO and IFAD, 2015. UNIDROIT/FAO/IFAD/ የእረሻው ውል የህግ መምሪያ፣ ሮም፣ http://www.fao.org/3/a-i4756e.pdf

9. በርካታ ጥናቶች እንዳሳዩት፡- የገንዘብ ካሳ በቀላሉ ወንዶችና የአካባቢዉ ባለሥልጣኖች በተለይም ደግሞ የጎሳ መሪዎችን ዋነኛ ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡ ለምሣሌ King and Bugri, 2013 ን ይመክቱ፡፡

10. የመሬት ዋጋ ግምትን በተመለከተ ስፋት ያለው ጥናቶች ይገኛሉ፡፡ ቴንጋ እና ሌሎችም፣ 2012 ይመልከቱ፡፡

11. እንዲሁም የመሬት መብትን በሚጐዳ ፓሊሲዎች ተጐጂ ሊሆኑ ከሚችሉት ማንኛውም ሰዎች ጋር ምክክር ማድረግን የሚጠይቁትን በአንቀፅ 8.6 ላይ ያሉትንና መመሪያዎችን ይመልከቱ፣ ከነባር ማህበረሰቦችና ልማዳዊ የመሬት መብቶች ካሏቸው ጋርም አንቀፅ 9.9 የሚጠይቁትን ይመልከቱ፡፡

12. ሴቶችን የማካተት ስልቶች ላይ የተሰራ ዳሰሳ ለማግኘት Knight et. al., 2012ን ይመልከቱ።

13. ቀደም ብሎ ከቀረበው ዝርዝር ውስጥ አብላጫው የተወሰደው ከUSAID, 2015፡28-29 ነው።

14. ስኬታማ የሆኑ መደበኛ ያልሆኑ የቅሬታ አፈታት መንግዶች መለያዎች በተመለከተ የተሟላ ዝርዝር ለማግኘት OHCHR, 2011: Principle/መርህ 31 ን ይመልከቱ።

15. ለፓለቲካ ከተጋለጡ ሰዎች ጋር በመመሳጠር የሚደርሱ ጉዳቶችን በተመለከተ፣ the Federal Financial Institutions Examination Council Publication (undated); ይመልከቱ።

16. የዓገድ የአፈፃፀም መለኪያ 1፣ አንቀፅ 29፣ ይፋ መደረግ የሚገባው መረጃ የትኛው እንደሆነ ያብራራል፤ እንዲሁም RSPO, 2013, Section 1.2.1 ን ይመልከቱ። AATIF በአንቀጽ 16 ገፅ 5 ተመሣሣይ መሥፈርት ያስቀምጣል።

17. ከባለድርሻ አካላት ጋር እንደዚያ ያሉ ግንኙነቶችን ጠብቆ ማቆየት ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ፣ ዓገድ የአፈፃፀም መለኪያዎች ለተጐጂ ወገኖች ቢያነስ ቢያንስ በየአመቱ በቀጣይነት ሪፓርት እንዲቀርብ ይጠይቃል፤ የዓገድ የአፈፃፀም መለኪያ 1፣ አንቀፅ 36 ን ይመልከቱ።

18. ለምሣለ ያህል፣ ዴንማርክ፣ የዴንሽ ኩባንያዎች ሰበአዊ መብቶችን ለመጠበቅና በአየር ጠባይ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ለመቀነስ ስለሚያደርጓቸው ጥረቶች በየዓመቱ ሪፓርት እንዲያደርጉ ይጠይቃሉ። Government of Denmark, 2014:6 ን ይመልከቱ።

19. De Schutter, 2009 8-9: ቀደም ብሎ በጉልህ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ ዋጋው ጨምሯል ተብሎ ለሚገመት መሬት ላይ የመጠቀም እድላቸውን ሊያጡ በሚችሉ ሴቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎች እንዳያርሱባቸው ለመከላከል ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

20. የብዝሀ-ህይወትን የሚመለከተው ስምምነት የሰብአዊ መብቶች መሣሪያ ባይሆንም፣ ነባር ህዝቦችን አስመልክቶ የተጠቀሰው በተለይም ለመመሪያዎቹ አግባብነት አለው።

21. የመሬትን መብቶች እንደሰብአዊ መብት በሚለው ላይ የበለጠ ሰፋ ያለ ትንተና ለማግኘት Cottula, 2014 and Wickeri and Kalhan, 2010 ን ይመልከቱ።

22. የአንዳንድ ኢንቬስተሮች ትውልድ አገሮች፣ እንደጀርመን ያሉ፣ ውሃ ማግኘት ሰብአዊ መብት መሆኑን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ መርሆዎችን አጽፈዋል German Federal Ministry for Economic Cooperation and Development (BMZ), 2012 ን ይመልከቱ።

german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

Implemented by
giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

ይህ መመሪያ በሀገራት፤ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሲቪክ ማህበራት፤ በግሉ ዘርፍ፤ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት፤ የግብርና ምርምር ተቋማት እና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሰፊ ምክክር በማካሄድ ተዘጋጅቶ እ.እ.አ ግንቦት ወር 2012 በዓለም የምግብ ኮሚቴ የጸደቀ መመሪያ ሲሆን ይህ ከእንግሊዝኛ ወደ አማራኛ ትርጉም ነው፡፡

የግብርና ኢንቬስትመንቶች ድህነት ከታዳጊ አገሮች የገጠር አካባቢዎች ለማስወገድ ከሚረዱ እጅጉን ስኬታማ ከሆኑት መንገዶች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ በአገር አቀፍ የምግብ ዋስትና ማእቀፍ ውስጥ የመሬት፣ የአሳ ሀብት እና የደን ይዞታ መብት በኃላፊነት ማስተዳደርን የተመለከቱ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ መመሪያዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ መንቀሳቀስ፣ ኢንቬስተሮችን በመሬት ላይ ኢንቬስት ከማድረግ ጋር በሚከሰቱ በርካታ የፋይናንስ፣ ህጋዊ፣ የአሰራርና የመልካም ስም አደጋዎችን በተሻለ ደረጃ ለመረዳትና ለመቆጣጠር ሊረዳቸው ይችላል፡፡ ኢንቬስትመንቶቻቸውን በመመሪያዎቹ መሰረት የሚያቅዱና ሥራ ላይ የሚያውሉ ሁሉ ኢንቬስትመንት ነክ አደጋን፣ ለመቀነስና አደጋን ያገናዘብ ሚዛናዊ ትርፍ ለማግኘት የተሻለ እድል ይኖራቸዋል፡፡

እንደነዚህ ያሉ ኢንቬስትመንቶች ስኬታማ መሆን የሚችሉት እያንዳንዱ፡- ኢንቬስተሩ ፣ የአካባቢው ማህበረሰብና መንግስት ተጠቃሚ መሆን ከቻሉ ነው፡፡ መመሪያዎቹም ይህን ሁሉም አሸናፊ መሆን የሚያስችላቸው ማዕቀፍ ያመለክታሉ፡፡ ይህ ሙያዊ መምሪያ የታለመው ኢንቬስተሮች ተገቢ ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ በእርሻ መሬት ላይ የማህበራዊ ኃላፊነትና የገንዘብ ዘለቄታዊነት ያላቸው ኢንቬስትመንቶችን እውን ማድረግ እንዲችሉ ለመርዳት ነው፡፡



ISBN 978-92-5-131436-4
9 789251 314364
I5147AM/1/05.19